ራዕይ

መንፈሳዊ መጽሔት

በዓመት አራት ጊዜ የሚታተም ትምህርታዊ ሥነ ጽሑፍ

አሳታሚ ፡- ማኅበረ በኵር

የመ. ሣ. ቍጥር - 23956 ኮድ 1000
የስልክ ቍጥር - 500450, 161660
አዲስ አበባ

የባንክ ሒሳብ ፡-
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ፥ ቍጥር 1011

ዋና አዘጋጅ - ጸጋዬ ደምሴ
ም/ዋና አዘጋጅ - ሠርፀ ፅጌል ጽዮን

ይህ መጽሔት ለማኅበረ በኵር መሥራችና አስባሳቢ፥ ለሥራ መጽሔትም የመጀመሪያው ዋና አዘጋጅ ለነበሩ ለአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ መታሰቢያ እንዲሆን ተወስኗል።

ከአሳሳቾች ተጠንቀቁ!

በሥራ መጽሔት ስም ገንዘብ የሚለምኑና የሚቀበሉ ግለሰቦችና ቡድኖች መኖራቸው ይወራልና፥ ከአታላዮች እንድትጠነቀቁ እናሳስባለን። የኛ አባሎች የማኅበራችን መታወቂያ አላቸው።

መልካም ዜና!!

ኦርቶዶክሳዊ ትምህርተ ክርስትና፥ በመላላክ በነጻ ይሰጣል እንደገና።

ለመማር ይፈልጋሉን?

ሙሉ ስምዎን፥ የመ.ሣ. ቍጥርዎን፥ ገልጸው ይጻፉልን።

የእኛ አድራሻ የመ.ሣ.ቍ. 56307፥ አዲስ አበባ ነው።

ማ ው ጫ

	ርእስ	ገጽ
ርእሰ አንቀጽ ፡- በፍጡር የሚታመን ርጉም ነው፤	. . . . .	1
መሠረተ እምነት ፡- ቤተ ክርስቲያን	.	2
ታላላቅ መንፈሳዊያን ቃላት ፡- ቅዱስ ቍርባን	. . . . .	8
የቤተሰብ አመሠራረትና አመራር ፡- የፍታሔና ቤተሰቡ	. . . . .	10
አለቃ ነቅዐ ጥበብና አገልግሎታቸው	.	13
ክርስትና በኢትዮጵያ	. . . . .	21
ነህምያና የሐድሶ አገልግሎቱ	. . .	25
ጥያቄ አለኝ፥ ይመለስልኝ	. . . .	27
ክርስቲያናዊ ምግባ	. . . . .	29
ከዓለመ መጻሕፍት	. . . . .	

ማስታወቂያ

ሥጦ ሔቱን ከአዲስ አበባ ማግኘት የማትችሉና በአድራሻችሁ እንዲላክላችሁ የምትፈልጉ ሁሉ የመጽሔቱን ዋጋና በፊኮማንዱ የሚላክበትን የፖስታ ወጪ በማከል ሙሉ አድራሻችሁን ከሚገልጽ ደብዳቤ ጋር ብትልኩልን እንደታዘዝነው እንፈጽማለን።

የሚቻል ከሆነ በአብያተ ክርስቲያናት በኩል ጥያቄው በደብዳቤ ቢደርሰን የተሻለ ይሆናል።

መጽሔቱን በማሠራጨት ጌታን ማገልገል ለምትፈልጉ ሁሉ እያንዳንዱ እትም (ቁጥር) 50 መጽሔት የሚይዝ እሽግ ሆኖ ስለተዘጋጀ እያንዳንዱን እሽግ ለሚገዛ 20% (ከመቶ ሃያ) ቅናሽ ስለሚደረግ ለአሳታሚው ድርጅት የሚከፈለውን 80% (ከመቶ ሰማንያውን) ብቻ፥ በፖስታ ቤት በኩል የሐዋላውን ክፍላችሁ በትድሚያ ብትልኩልን የምትፈልጉትን ያህል የምንልክላችሁ መሆኑን በትሕትና እንገልጻለን።

በፍጡር የሚታመን ሰው ርጉም ነው !!!

በቤተ ልሔም ዘይሁዳ መንጋቸውን በትጋት እየጠበቁ ለነበሩ እረኞች ከጌታ መልአክ የተነገራቸው ቃል «የምሥራች!» የሚል ነበር። ወትሮ የመልአክ መገለጥ ያሰፈራ ነበርና እረኞቹ መልአኩን ሲያዩ ፈሩ፤ መልአኩ ግን ለመርዶ፥ ወይም ለመቅሠፍት ሳይሆን ለሕዝብ ሁሉ የሚነገር የምሥራች ይዞ የመጣ ነበር። ከብዙ ሠራዊተ መላእክት ጋርም ባንድነት ባስተጋቡት የዕርቅና የሰላም ዐዋጅ እንደገለጹት «ሰላም በምድር» ሆኗልና ከእንግዲህ ጠብና መለያየት ሰለማይኖር ፍርሃት ማክተሙን ሲነግራቸው መልአኩ «አትፍሩ» አላቸው፤ (ሉቃ. 2፥8-14)።

ለምሥራቹ ቃል መሠረት የሆነውን ነጥብ መልአኩ ሲተነትን፥ «ተወልደ ለክሙ ... መድኀኒ ዘውእቱ ክርስቶስ እግዚእ ቡሩክ፤ ጌታ፥ ክርስቶስ የሆነው አዳኝ ተወልዶላችኋል» ብሏቸዋል። ለሕዝብ ሁሉ የሚሆነው ይህ የምሥራች ቃል የተለያዩ ሰዎችን ጆሮ ይስባል፤ በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ ጤናቸው ለተታወሰባቸው በሽተኞች፥ መድኃኒት ፍለጋ ሲንከራተቱ ለኖሩም ሁሉ [illegible] ነው።

በቤተ ልሔም የተወለደው ሕፃን፥ ምድራችን ባለፈው ጊዜ ካፈራቻቸውና ወደፊትም ከምታፈራቸው የአዳም ልጆች ሁሉ የተለየ ነው፤ ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) አይደለም። ስሙ እንደሚያመለክተው «ኢየሱስ፥ እግዚአብሔር ያድናል» በሚል ስያሜ ይታወቃል። (ማቴ. 1፥21፤ ሉቃ. 1፥31) እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጸበትን ረቂቅና ድንቅ ምስጢርን የተቆላና የማዳን እርግጠኛ ኃይል ያለው ፍቱን የሆነ «እግዚአብሔር መድኃኒት» ነው፤ ስሙ ሆኖ የተገኘውን ባሕርዩን ያመለክታልና።

እግዚአብሔር - ሰው በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም እንዲድን በምክረ ሥላሴ ሲወሰን፤

1ኛ. የሰው እምነትና አለኝታ (ተስፋ) በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እንዲያርፍ፤

2ኛ. በዚህም ምክንያት የሚቀርበው አምልኮ፥ ስግደት፥ ምስጋናና ክብር፥ ከእግዚአብሔር ሳይወጣ ተጠቃሎ ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲሆን፤

ታቅዶ መሆኑ ሊስተዋል ይገባል፤ ሁሉ ከእርሱ እንደሆነ፥ አሁንም ሁሉ በእርሱ ሆኖ፥ በመጨረሻም ደግሞ ሁሉ ለእርሱ ሊሆን የታቀደበት መለኮታዊ ምስጢር በውስጡ አለበት፤ (ሮሜ 11፥36፤ ኤፌ. 1፥10)።

የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ኤጲፋንዮስም በሃይማኖተ አበው፥ የሰው ደኅንነት እግዚአብሔር - ሰው በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የሆነበትን ምክንያት እንደሚከተለው አመስጥሮ ገልጾታል። «ወእኮ ተስፋኑ በሰብእ አላ በእግዚአብሔር፥ እስመ ጽሑፍ ዘይብል ርጉም ዘይሴፈው ካልአ ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ። ዘያሴፎ ዘከማሁ ሳብአ ይከውን ከመ ኳሄላ። ወናሁ ተከሥተ ለነ እስመ እግዚእነ ክርስቶስ ኢኮነ ብእሴ ዕሩቀ እመለኮት ከመ ኩሉ ሰብእ እለ ዘከርናሆሙ ቅድመ ... ወኢኮነ ተስፋ መድኃኒትነ በሰብእ፤ ወኢክህለ ሰብእ ያድኅነነ እምአዳም እስከ ተፍጻሜተ ዓለም፤ አላ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ዘተሠገወ ከመ ኢይኩን ተስፋነ በሰብእ ወኢንኩን ርጉማነ፤ ወዳዕሙ ተስፋነ በእግዚአብሔር ሕያው። ... ወሕይወትነኒ ኢኮነ በሰብእ፥ ወኢእምነትነ በሰብእ፤ እስመ ይቤ መጽሐፍ ይኩን ርጉመ ዘይትአመን በእጓለ እመሕያው። ...» እያለ በግእዝ የተብራራው ወደ አማርኛ ሲተረጐም እንደዚህ የሚል ነው።

«ብቻውን እግዚአብሔርን ካልሆነ በቀር ሌላውን ተስፋ የሚያደርግ ቢኖር የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና፥ ተስፋችን በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አይደለም። እንደ እርሱ ያለውን ዕሩቅ ብእሲ አለኝታው የሚያደርግ ሰው እንደ ፍሬ አልባ ደረቅ የበረሃ እንጨት ይሆናል። የምንታመንበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ቀደም ሲል እንደ ጠቀስናቸው እንደ ማናቸውም ሰዎች ሁሉ ከመለኮት የተራቁተ ሰው አለመሆኑ ግልጽ ሆኖልናል።

እኛን ስለማዳን የተነገረው ተስፋም በሰው አልተከናወነም፤ ከአዳም ጀምሮ እስከ ተፍጻሜተ ዓለም እኛን ያድን ዘንድ የሚቻለው ሌላ ባልተገኘ ነበር። አለኝታችን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሰው እንዳይሆንና እንዳንረገም እግዚአብሔር የሆነው ሥግው ቃል አዳነን። ... እንግዲህ መዳናችንም ሆነ እምነታችን በሰው ላይ ያረፈ አልሆነም፤ መጽሐፍ በሰው የሚታመን የተረገመ ይሁን ብሏልና፤ (ኤር. 17፥5-8)። ... ከአዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ማንም ማን ሊያድነን አልቻለም፤ አለኝታችን በሰው ላይ ያረፈ ቢሆን ኖሮ ከንቱና የማያድን በሆነ ነበር። ስለዚህም አምላክ ጽድቅ ራሱ ሰው ሆኖ አዳነን። ... እንግዲያውስ እኛ፥ ጌታችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምንታመን፥ የምንታመንበትም ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ያይደለ፥ ነገር ግን ያለ ጥርጥር ሰው የሆነ እግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ለሰው ሁሉ ታወቀ፥ ግልጽ ሆነ» ብሏል።

እንደዚህ ያለ ጥልቅና አስደናቂ ምስጢርን ይዞ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ላይ የተመሠረተው መሠረተ እምነታችን በተረት መጻሕፍት በመቀበሩ ድኅነት በፍጡራን ይገኛል የሚለው፥ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንደ እንጉዳይ በቅሎ ይታያል። ‹ያለ ዐዋቂ ሳሚ› እንደሚባለው ዓይነት የሆኑ የተረት መምህራን ከፍጡራን ድኅነት እንደሚገኝ አስመስለው በሰበኩት ባዕድ ወንጌል ምክንያት ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን ከእርግማን በታች አውለዋቸዋል።

ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን ጥበብና ብርታት በመታመን፥ የእግዚአብሔርን እውነት ለመሸፈን በረጅም ዓመታት ውስጥ ከመናፍስት የተበተነውን ዐዚም በቅርጠኝነት ለመጠራረግ፥ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣሣውን ክፉ ልብ በማፈራረስ የሰውን አእምሮና ፈቃድ ሁሉ ለቤተ ልሔሙ ሕፃን ለመድኃኔ ዓለም ለማስገዛት እንግርክ ዘንድ እንነሣ፤ (2ቆሮ. 10፥3-6)።

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን።

ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን

የቤተ ክርስቲያን ምንነት የሚጠናበት ትምህርት

አለታ ነቅዐ-ጥበብ ለፍካሬ መጻሕፍት አርድእት ከሰጡት
አስተምህሮ በከፊል የተወሰደ።

መግቢያ

በግእዝና በአግርኛ «ቤተ ክርስቲያን» የምንለውን ቃል ትርጕሙን በጥሬ ቃሉ እንረዳው ብንል የክርስቲያን ቤት ማለት ስለሆነ፥ የክርስቲያን መኖሪያ ቤትን፥ የክርስቲያን መሥሪያ ቤትን፥ የክርስቲያን የአምልኮ ቤትንና ስፍራን የሚያመለክት ትርጕም አለው። ነገር ግን «ኤክሌስያ» የሚለው የግሪክ ቃል ወደ ግእዝ፥ ወይም ወደ አግርኛ በሚመለስበት ጊዜ «ቤተ ክርስቲያን» ተብሎ የተተረጐመ በመሆኑ መሠረታዊ ዕሳቤው ከቦታና ከሕንጻ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። «ቤተ እስራኤል የእስራኤል ዝርያ፥ የእስራኤል ነገድ፥ ቤቲ ሌዊ - የሌዊ ነገድ፥ ቤተ አሮን፥ የአሮን ቤተሰብ» (መዝ. 134፥19-20) በሚለው ዓይነት የገባ ስለሆነ፥ የክርስቲያን ጉባኤን፥ ግኅበረ ክርስቲያንን ይገልጻል፤ (ሥራ ቁ. 12 ገጽ 241 ቁ. 17 ገጽ 8)።

ጥንታውያን ግሪኮች «ኤክሌስያን» ለዓለማዊው ጉዳይ ሲጠቀሙበት «ለመምረጥና ለመመረጥ ብቁ የሆኑ ዜጎችን ወይም የኅበረተሰብ ክፍሎችን፤ በፖለቲካ፥ በፍልስፍና፥ በግኅበራዊ ጉዳዮች ለመወያየት፥ ለመከራከር የሚሰበሰቡ ምርጥ ግኅበረ ሰብእን (ጉባኤ ሊቃውንትን) ለመግለጥ ይጠቀሙበት ነበር። እንደዚሁም «ኤክሌስያ» በመንፈሳዊው ዓለም ያለው ትርጉም «የተመረጠች፥ የተጠራችና የተለየች ጉባኤ» ወይም «ጉባኤ ምእመናንን» ከማመልከት የተለየ ትርጉም የለውም።

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የሚለው የግእዝና የተለመደ የአግርኛ ቃል «ኤክሌስያ» የሚለውን የግሪኩን ቃል ተክቶ የገባ እንደመሆኑ መጠን ትርጕሙ «ጉባኤ ክርስቲያን» ማለት ከሆነ፥ የምእመናንን ስብስብ እንጂ ሕንጻንና ቦታን አያመለክትም ማለት ነው። በቤት ወይም በዋሻ ውስጥ፥ በዛፍ ሥር፥ ወይም በሜዳ ላይ ቢሰበሰቡም ራሳቸውን ስብሰባቹን ምእመናንን ብቻ የሚወክል ቃል ነው።

እንደ ግሪኩ ኤክሌስያ የዕብራይስጡም «ካሃል» ተመሳሳይ ትርጉም እንዳለው ታውቋል። ከአሕዛብ ምድር መካከል ለእርሱ ሕዝብ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣትን፥ የጠራትንና የለያትን ግኅበረ እስራኤልን ይገልጻል፤ ዘጸ. 19፥5-6፤ ዘዳ. 7፥6-8።

1. ኤክሌስያ በዘመነ አበው

አዳምና ሔዋን ለሰይጣን በመታዘዝ ባደረጉት ምርጫ ምክንያት ተሳስተው ከመደቀና ኃጢአት ከተቈጠረባቸው በኋላ ልጃቸው አቤልና ከ7ኛው ትውልዳቸው ሄኖክ፥ ከ10ኛው ትውልዳቸውም ኖኅ ዘእግዚአብሔር ራት ምክሳ እንዳገኙ፥ እግዚአብሔርን በማገልገል ቤተ-ክለጠው እምነታቸውም የጽድቅ ወራሽ እንደሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተዘግቧል። ዘፍ. 4፥2-5፤ 5፥22-24፤ 6፥8-9፤ ዕብ. 11፥4-7።

ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ከአሕዛብ ምድር መካከል ለእርሱ ሕዝብ የሚሆንለትን ቤተሰብ መረጠ፥ ጠራና ለየ። እርሱም አብርሃምና ዘሩ ነበር። ዘፍ. 12፥1-9፤ ዘዳ. 10፥12-22።

2. የኤክሌስያ ዋና ተስፋ

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ቃል የገባላቸው ብዙ በረከት ቢኖርም ዋናው ተስፋ «ጽድቅ በእምነት» ነው፤ መግለጫውም መለየት (መቀደስ)፥ እምልኮ፥ መታዘዝና መመስከር ነበረ። ዘፍ. 15፥6፤ ዘጸ. 19፥5-6፤ ሮሜ 4፥1-3፤ 8፥29-30፤ 1ጴጥ. 2፥9-10።

3. ኤክሌስያ በዘመነ ሕግ

አሕዛብ ምድር የሚባረኩበት ዘር እስኪመጣ ድረስ ኤክሌስያ በሕግ የምጠት አስተዳደር ሥር ተደረገች። ሐዋ. 7፥38፤ ገላ. 3፥23-25

4. ኤክሌስያ በሐዲስ ኪዳን፤ በዘመነ ሐዋርያት፤

ለዮና ልጅ ስምዖን «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ መሆኑን ያስተውልና ያምን ዘንድ እግዚአብሔር ገለጸለትና ሾሰከረ። ስለዚህም «ጴጥሮስ» ተባለ፤ «ጴጥራ» በሆነችው ዐለት ላይ የቆመ፥ የተመሠረተ ማለት ነው። «አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ» በሚለው በጴጥሮስ ምስክርነት (ጴጥራ) ላይ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚያንጽ «ወዲበ ዛቲ ኩሪሕ (ጴጥራ) አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ፥» ሲል ተስፋ ሰጠ። በዋንኛዋ ትርጓሜ ወንጌል «ወኩሪ ሕሰ ሃይማኖተ ጴጥሮስ፤ ዘተብህለ በእፈ ጴጥሮስ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፤ እስመ ይቤ ወዲበ ዛቲ ኩሪሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ ከመ ዘይቤ ወዲበዛቲ ሃይማኖትከ። ቤተ ክርስቲያኔን እንጽባታለሁ ያላት ዐለት በጴጥሮስ አንደበት፥ አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ ተብላ የተነገረችው ሃይማኖተ ጴጥሮስ ናት» ይባላል። ማቴ. 16፥18።

5. ኤክሌስያ በዘመነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አረዳድ (ግንዛቤ)፤

በኒቅያ የእምነት መግለጫ (ጸሎተ ሃይማኖት) ውስጥ አራተኛው ተአምኖት «ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዜሐዋርያት፤ ከሁሉ በላይ በሆነችው፤ ሐዋርያት በሰበሰቧት በእንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን (መናር) እናምናለን» የሚል ነው። ለዚህ ጥልቅ ምሥጢርን ለያዘ መንፈሳዊና ሰማያዊ አባባል በዘመናችን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ሥጋዊና ምድራዊ ትርጉም ነው። «ቤተ ክርስቲያን» ከሁሉ በላይ መሆንዋና «አንዲት» መባልዋ ከምዅራበ አረሚና ከምዅራበ አይሁድ በላይ ስለሆነችና በወርቅ፥ በብር፥ በጭቃ፥ ብትገነባ፥ በእስክንድርያ ወይም በሌላ አገር ብትታነጽ በጻድቃን፥ በሰማዕታት ... ስም ብትሠራ ያው ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ነው» የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል። ቅዳ አንድምታ ትርጉም።

ዳሩ ግን ኤክሌስያ ወይም ቤተ ክርስቲያን በሚል ሰያሜ የተገለጠችው ጉባኤ ምእመናን ራስ ለሆነላት ለክርስቶስ አካሉ ናት፤ እርሷንም እግዚአብሔር ሊቃናት፥ ሥልጣናት፥ ኃይላት፥ አጋዕዝትና መናብርት በመባል ከሚጠሩት የመላእክት ምድቦች ሁሉ በላይ አስተምዅታል፤ ሰማይንና ምድርን የሞላች የክርስቶስ ሙላቱ ናት። እንግዲያውስ «አንዲትና ከሁሉ በላይ» ያሰኛት ይህ ጥልቅ ምስጢር መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ሊቁ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተላከውን (ኤፌ. 1፥20-23) የጳውሎስ መልእክት «... ዅሉን እሥልጣኑ እመታን፥ መአንበር በየማኑ ውስተ ሰማያት፥ መልዕልተ ዅሉ መላእክት፥ መመኳንንት፥ መጎይላት፥ መአጋዕዝት፥ መኵሉ ስም ዘይሰመይ መአኮ በዝ ዓለም ባሕቲቱ፥

ወባሕቱ በዘይመጽእኒ ዓለም። ወኵሉ አግረረ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ፤ ወኪያሁ ዘውእቱ መልዕልተ ኵሉ ረሰዮ ርእሰ ለቤተ ክርስቲያን፥ እንተ ይእቲ ሥጋሁ ...፤» የሚለውን በተረጐመበት ድርሳን እንዲህ ብሎ አብራርቶ ገልጾታል።

«... ክርስቶስን ባስነሣበት ሥልጣን በክብር ወደ እርሱ አቀረበን ማለት ነው። ወደ እርሱ ማቅረብ ብቻ አልበቃውም፤ ከእርሱ ጋር በዕሪናው (በቀኙ) በዙፋኑ ላይ እስኪያስቀምጠን ድረስ ወደ እርሱ ከማቅረብ የሚልቅ ሥራን ሠራ እንጂ፤ ... ክርስቶስን ወዲት እንዳወጣው አስተውል፤ ከፍጡራን ሁሉ፥ ከመላእክትም ሁሉ በላይ አደረገው። ... ስለዚህም ሁሉን ከሥልጣኑ በታች አስገዛለት፤ ከሁሉ የሚልቀውን እርሱንም (ክርስቶስን) ለቤተ ክርስቲያን ራስ አደረገው። ... እርሷ (ቤተ ክርስቲያን) ሁለንተና አካሉ እንደ መሆኗ መጠን፥ ቤተ ክርስቲያንን ከላይ ሆኖ ወደ ላይ እርሱ ወዳለበት በጥበብ እንደሳባትና እንዴት ወዳለ የመጨረሻ ከፍታ እንዳወጣት አስተውል። ... ከእኛ የተወሰደውን ሥጋም በዚያ መለኮታዊ ዙፋን ላይ አስቀመጠው። ቤተ ክርስቲያን በመባል የምንጠራውን እኛንም እርሱ ራሳችን ሆኖ እርሱ ወዳለበት ሳበን፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት በዚያ ስፍራ አካል የተባልነው እኛ እንኖራለንና» ፫.አ።

እንግዲያውስ የቤተ ክርስቲያን እንዴት መሳል የአንዱ የክርስቶስ አካል ሆና በእርሱ መጠቃለሏን የሚያስረዳ ሲሆን፥ (ሮሜ 12፥4-5፤ 1ቆሮ. 12፥12-13፤ 27፤ ኤፌ. 1፥10፤ 4፥4) «ከሁሉ በላይ» ናት ማለቷም ራሷ ለሆነው ለክርስቶስ አካሉ ሆና በማናቸውም ምድብ ከሚጠሩ መላእክት ሁሉ በላይ በሆነ በመለኮታዊ ዙፋን ላይ መቀመጫና ሁሉ ከእግሯ ሥር በመሆናቸው ነው (ኤፌ 2፥6-7)። የመሰብሰቢያ ሕንጻ በመርቅ ወይም በብር ወይም በምንም ዓይነት ሌላ ነገር ቢሠራ በእግዚአብሔር ቀኝ አይቀመጥም፤ እርሱ ከሰማይና ከምድር ጋር ያልፋል። ማቴ. 24፥35፤ ዕብ. 12፥27።

. ሐዋርያው፥ ጳውሎስ ሠራዊተ መላእክት ሁሉ ከእግሩ ሥር ለተደረጉለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ለሆነው ለክርስቶስ የአካሉ ክፍል ከሆኑት ምእመናን መካከል እርሱ አንዱ ሆኖ እንደሚኖር ሲያረጋግጥ፤ «ወኢተአምሩኑ ከመ መላእክተ ጥቀ ንኡንን ጎድጉሰ ዘዝ ዓለም። በዚህ ዓለም ጉዳይ ዳኝነት ከመስጠት በላይ የሆነ ሥልጣን እንዳልን፤ መላእክትን እንኳ እንድንገዛ አታውቁምን?» (1ቆር. 6፥3) ብሏል። አንዳንድ የዋህ ምእመናን ታዲያ መላእክትን የመገዛት ሥልጣናችን ለምን አሁን ሲሠራ አይታይም? ይላሉ። እያንዳንዳቸው እንዴን መልእክ ጠርተው ሊያዙት ይሻሉ። ልብ እናድርግ እያንዳንዱ ምእመን በአካል ውስጥ በሚኖረው አንድ መለያልይ (ብልት) ውስጥ እንደ አንድ ትንሽ የሥጋ ቁራጭ ነው። እንደ እርሱ ካሉ ብዙ ምእመናን ጋር ተገጣጥሞ አንድ ጡንቻ ቢወጣው፤ ብዙ ጡንቻዎች ተገጣጥመው አንድ ብልት ይሆናሉ፤ ብዙ ብልቶችም ተዋደደው አንድ አካል ይሆናሉ። እነርሱን አዋሕዶ የያዘው ራስ አለ፤ ሥልጣኑ እዚያ ስለሆነ፤ ትእዛዝ የሚወጣው ከዚያ ራስ ከሆነው ከእርሱ ነው። ሆኖም መላእክት የምንገዛው ለራስ ብቻ እንጂ ነው፤ ለአካሉ አንገዛም አይሉም፤ ለአካሉ ጭምር ይገዛሉ እንጂ። አካል የሌለው ራስ የለምና። አካል መላእክትን የሚገዛው ከራስ ጋር ሆኖ፥ በራስ አማካይነት ነው፤ ከራስ የተቈረጠ፥ (የተለየ) ቁራጭ ከሆነ እንኳን የማዘዝና የመግዛት ሥልጣን ሊኖረው ይቅርና ሕይወትም እንኳ የለውም። «ወዘእንበሌየ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ፥ ወኢምንተኒ .. ያለ እኔ ምንም መሥራት አትችሉም» (ዮሐ. 15፥5) ብሏልና፤ የምእመናን ሥልጣን፥ ችሎታ፥ በየግላቸው ሳይሆን አዋሕዶ በያዛቸው በክርስቶስና በክርስቶስ በኩል ነው።

6. ቤተ ክርስቲያን አንዲት መሆንዋ

ቤተ ክርስቲያን በየአጥቢያው፥ በየአውራጃው፥ በየሀገሩ የአምልኮ ቅርንጫፎችና አመራር ሰጭ ድርጅቶች ቢኖሯትም «ፍጹም አንዲት ትሆን ዘንድ» እግዚአብሔር ተጠንቅቆላታል ኤፌ. 4፥2-6።

ምእመናን ለአምልኮ፥ ለጥቢቃ፥ ለመግበት ምንም በየአጥቢያው ቢደራጁም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው «የግትታየው ቤተ ክርስቲያን» እንዲት ናት። አንዲት የሆነች እርሷ በመላው ዓለም ያሉትን ሕያዋን ቅዱሳንና በሰማይ ያሉትን ያንቀላፉ፥ ከሥጋቸው የተለዩ ቅዱሳንን አካል በመሆንዋ ውስጥ ያቀፈች ስትሆን ሰማይንና ምድርን የሞላች ናት።

6.1 በተለያዩ ምሳሌዎች እንድነታ ተገልጿል፤

6.1.ሀ የክርስቶስ ሙሽሪት ተብላለች፤

ክቡርና ቅዱስ በሆነ ጋብቻ የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት መጣመር ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ተዋሕዶ ምሳሌ ሆኖ ተነግሯል (ኤፌ. 1፥22-23፤ 5፥22-33)። ስለሆነም በምድር የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶችና የአምልኮ ስፍራዎች ቢኖሩም ዳግም የተወለዱትን ሁሉ አሰባስባ የያዘችው የቅዱሳን ጉባኤ አንዲትና እንዲት ብቻ ናት።

6.1.ለ ብዙ ብልቶችን በያዘ ከአንድ ራስ ጋር በተዋደደ አንድ አካል ተመስላለች፤ ማንኛውም ሕይወታዊ አካል ከተወነሰበት ጊዜ ጀምሮ በዕድገት፥ በመፋፋትና በመጠንከር ሂደት ላይ እንደሚገኝ የአካልነቷ እድገት ሙሉና ፍጹም እስኪሆን ድረስ በመቀጠል ላይ ይገኛል። ሮሜ 12፥4-8፤ 1ቆሮ. 12፥4-31፤ ኤፌ. 4፥11-16፤ 25።

6.1.ሐ በብዙ ድንጋዮች መገንባት ህላዌን ባገኘች በአንድ ሕንጻ ተመስላለች። ኤፌ. 2፥19-22፤ 1ጴጥ. 2፥5።

6.2 ቤተ ክርስቲያን በአንድ መስካሪ ብቻ ታነጸች። በጴጥሮስ ምስክርነት ላይ ሊገነባት (ሊያንጻት) ጌታ ቃል መግባቱ ይታወቃል። (ማቴ. 16፥18) ስለዚህም፤

6.2.ሀ ሐዋርያት የጴጥሮስን ምስክርነት አስተጋቡ፤ እንደዚሁም «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» አሉና መሰከሩ። ዮሐ. 6፥68-69፤ 20፥30-31፤ 1ዮሐ. 5፥20።

6.2.ለ በበዓለ ሃምሳ በጴጥሮስ ምስክርነት ቤተ ክርስቲያን በአይሁድ ክርስቲያኖች መካከል ተቋቋመች፤ ታነጸች። ሐዋ. 2፥5-42፤ 4፥1-4፤ 6፥7።

6.2.ሐ ደግሞ የአይሁድና የአሕዛብ ደም ባላቸው ክርስቲያን ሰማርያውያን መካከል ቤተ ክርስቲያን በጴጥሮስ ምስክርነት ተቋቋመች ታነጸች። ሐዋ. 8፥14-25።

6.2.መ አውንም በጴጥሮስ ስብከት በአሕዛብ ክርስቲያኖች መካከል ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመች። ሐዋ. 10 እና 11፤ እንዲሁም 18፥22።

እንደ ወይን ሐረጎች እየተሳሳቡ ዓለምን የሞሏት በአንዱ በጴጥሮስ ምስክርነት የታነጹት እነዚሁ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

7. የአጥቢያና የክልል አብያተ ክርስቲያናት፤

ሐዋርያት ገና በአገልግሎት ላይ በነበሩበት ዘመን በየከተማውና በሰዎች መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የአጥቢያና የክልል አብያተ ክርስቲያናት ተቋቁመው ነበር። ጥቂቶቹም፤

- በአንጾኪያ (የሶርያ ክፍል በሆነችው) ሐዋ. 11፥25-26፤ 13፥1-4፤ 15፥35፤ 18፥22
- በክንክራኦስ፥ ሮሜ 16፥1
- በተሰሎንቄ፥ 2ተሰ. 1፥1
- በቆሮንቶስ፥ 2ቆሮ. 1፥1
- በፊልጵስዩስ፥ ፊል. 4፥15
- በኤፌሶንና በሌሎች ስድስት ከተማዎች፥ ራእ. 1፥11
- በጵርስቅላና በአቂላ ቤት፤ ሮሜ 16፥5፤ 1ቆሮ. 16፥19
- በንምፋን ቤት፤ ቈላ. 4፥15
- በፊልሞና ቤት፤ ፊልሞና 2

8. የቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ (አፍአዊ) አንድነት ጥበቃ፤

መሠረታዊ የእምነት አስተምህሮ የሚቀየስበት አጠቃላይ መመሪያ የሚመነጭበት ሲናዶስ በኢያሩሳሌም ተቋቁሞ፥ በሐዋርያት ይመራ እንደነበረ ታውቋል። በዚያም ያዕቆብ፥ እጉው ለእግዚእነ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ዋና ሹሞች መይም (አዕማድ) ነበሩ፤ (ሐዋ. 15፥13፤ 22፤ ገላ. 2፥2፤ 6-9)። ያ ሲናዶስ ለቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ (አፍአዊ) አንድነት ታላቅ ምልክት ሆኖ እንደነበረ ከሚከተሉት ነጥቦች መረዳት ይቻላል።

8.1 ሐዋርያትን እንደ አስፈላጊነቱ ለሥራ የሚያንቀሳቅሳቸውና ሪፖርት የሚቀበላቸው ይህ ሲኖዶስ ነበረ። ሐሥ. 8፥14፤ 11፥22-30፤ ገላ. 2፥2፤ 10።

8.2 መንፈስ ቅዱስም የሚያታየውን አንድነት እንደሚጠብቅ ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን ድርጅታዊ አንድነትም ይጠብቅ ነበረ። አንደኛውም የአንድነቱ መጠበቂያ የአስተምህሮ ምንጭ አንድ እንዲሆን ከማድረጉ ላይ ነበረ። «ይህ በጌታ የተነገረ፣ የሰሙትም ለእኛ ያጸኑት፥ እግዚአብሔርም በድንቅና በተአምራት የጸጋ ሰጦታዎችንም በማደል የመሰከረለት ...» ተብሏል። ዕብ. 2፥3-4። ቀጥሎም «ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ፥ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ» (2ጢሞ. 2፥2) በተባለው መንገድ አስተምህሮው ከአንድ ምንጭ ወደ ብዙ አማጫዎች እንዲፈስ ተደርጓል።

8.3 እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት በተለያየ መንገድ ቢጠራም ከዚህ ሲኖዶስ ውጪ እንዳይሆኑ የሚያደርግበት አሠራር ታይቷል። ጌታ በቀጥታ ሳውልን ለሐዋርያነት ጠራውና ሾመው፥ (ሐሥ. 9፥15-16) ሊያደርግ የሚገባውን ግን ሐናንያ ከተባለ ከአንድ ደቀ መዝሙር (ከሐዋርያት በታች ያለ እንጂ ራሱ ሐዋርያ ካልሆነ) እንዲማር አዘዘው። (9፥6፤ 10-18)።

እንደዚሁም ሳውል ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን የተሰጠውን ራእይና ጸጋ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በሲኖዶስ መሪዎች አስመርምሮ ማረጋገጫ መቀበል ነበረበት። ሳውል ይህን ታሪክ ሲተርክ እንዲህ አለ፡ «ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ፥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው። ...የተሰጠኝንም ጸጋ ዐውቀው፥ ... እኛ ወደ አሕዛብ፥ እነርሱም ወደተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን» (ገላ. 2፥2፤ 9) ብሏል። በእግዚአብሔር ዘንድ ለድርጅታዊ አንድነትም ይህን የመሰለ ጥበቃ እንዳለ ይታያል።

8.4 በታለ እግዚአብሔር አተረጓጐምና በመሠረታዊ አስተምህሮ ሊኖር ከሚገባው ተመሳሳይነት ሌላ በመሠረታዊ የአመራር መርሕ ድርጅታዊ አንድነት ይኖር ዘንድ በየከተማው የተቋቋሙትን አብያተ ክርስቲያናት፥ በአውራጃዎችና በጠቅላይ ግዛቶች በማደራጀትና በማቈራኘት ለመሥራት እንዲያመች፤

8.4.ሀ ሐዋርያት ራሳቸው በየአጥቢያው እየተገኙ አስተዳዳሪዎችን (ሽማግሌዎችን ወይም ቀሳውስትን) ይሾሙ ነበር። ሐሥ. 14፥23።

8.4.ለ ለአውራጃዎችና ከሲኖዶሱ በታች ላሉ ጠቅላይ ቢሮዎች ተገቢ ኀላፊዎችን ይመድቡ ነበር። በቲቶ 1፥5 እንደሚነበበው፤ «...የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም ... ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ» በማለት ጳውሎስ ለቲቶ ጽፏል።

- ሐዋርያው ጳውሎስ ቲቶን በቀርጤስ ሾመ
- ቲቶ በበኩሉ ከእርሱ በታች በየከተማው ልሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን መሾም ነበረበት።
- የሚሾሙት ሽማግሌዎች የተመደቡባቸውን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ማስተዳደር ነበረባቸው።

እንግዲህ ከሲኖዶሱ በታች የሦስት ግለት የጳውሎስ፥ የቲቶ፥ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ቢሮዎች ይታዩናል። ተመሳሳይ ሐሳብም በ1ጢሞ. 1፥3-4፤ 3፥1-11፤ 5፥1-2፤ 17፤ 22 ይገኛል።

8.5 እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ሌሎችም ሐዋርያት ወይም እነርሱ የሾሟቸው አገልጋዮች በጠቅላይ ቢሮዎች በመሪነትና በአስተዳዳሪነት ተመድበው ይሠሩ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ፍንጭ ይሰጣል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ይረጋገጣል።

8.5.1 በሲኖዶሱ ውስጥ ዋና የነበረው ቅዱስ ጴጥሮስ መደቡ በእንጾኪያ ሆኖ፤ በጳንጦስ፥ በገላትያ፥ በቀጰዶቅያ፥ በእስያ፥ በቢታንያ በጠቅላላው በአካባቢው የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናትን ያስተዳድር ነበር። ስለሆነም በእነዚህ አካባቢዎች በሥሩ የነበሩትን የቤተ ክርስቲያን እረኞች (ኤጲስ ቆጳሳትን) የመክርና የመምራት ኀላፊነት ነበረው። 1ጴጥ. 5፥1-4፤ 12፤ 2ጴጥ. 1፥12፤ 3፥1-3።

8.5.2 ከዚህም በኋላ ለሮሜ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ሆኖ እንደነበረ ዐቃብያ ቤተ ክርስቲያን ተጽፎአል።

8.5.3 ጢሞቴዎስ በጳውሎስ ተሾሞ የእስያን አብያተ ክርስቲያናት ሲመራ በኤፌሶን ይቀመጥ እንደነበረ ታውቋል። 1ጢሞ. 1፥3-4። ከእርሱ በኋላም ወንጌላዊ ዮሐንስ በኤፌሶን ተመድቦ እንደሠራ ይተረካል። (ራእ. 1፥4-5) በመልእክቶቹም (2ዮሐ. 7-12፤ 3ዮሐ. 1-14) ያሉት ሐሳቦች ይህንኑ ሳይጠቁሙ አይቀሩም።

8.5.4 ግርቆስ የተባለው ወንጌላዊ ወደ ግብጽ መጥቶ እንደሰበከና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንን እንዳቋቋመ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል። ግርቆስን ወደ ግብጽ የላከው የትኛው ሐዋርያ እንደሆነ አልታወቀም። ምናልባት ግርቆስና አጐቱ በርናባስ ከጳውሎስ ከተለዩ በኋላ፥ ወደ ቆጵሮስ ዘልቀው ነበርና ግርቆስ ከዚያ በመነሣትና ታላቁን ባሕር በማቋረጥ ወደ እስክንድርያ ተሻግሮ ይሆናል። (ሐዋ. 15፥36-39)። ወይም፥ እንደ ልጁ የሚቈጥረው ጴጥሮስ ግርቆስን ወደዚያው ልኮት ይሆናል። (1ጴጥ. 5፥13)። ወይም፥ በሮሜ እስር ቤት የነበረው ጳውሎስ ሊጠይቀው ወደ እርሱ ሲመጣ ግርቆስን ወደዚያው ልኮት ይሆናል። ቈላ. 4፥10-11፤ 2ጢሞ. 4፥11፤ ፊል. 24።

9. ከዘመነ ሐዋርያት በኋላ የመናብርት ትውፊት መቀጠል፤

ከሐዋርያት በኋላም ቤተ ክርስቲያን «አሐቲ ቅድስት፥ ጉባኤ ዘሐዋርያት» መባሏ በመንፈሳዊው አንድነት ብቻ የሚታወቅ ሳይሆን በድርጅታዊ አንድነትም ይገለጽ ዘንድ ጥረት መደረጉ ቀጥሎ ነበር። ለምእመናን ጥበቃና መግቦት እንዲሁም ለወንጌል ሥርጭት አመቺነት ይኖረው ዘንድ የአንዱ ሲኖዶስ መኖርና መቀጠል እንደተጠበቀ፥ ከሐዋርያት የተገኘው የመናብርተ ሊቃነ ኤጲስ ቆጳሳት (ሊቀ ጳጳሳት፥ በኋላ ፓትርያርክ እየተባለ የተጠራው መንበር) ህልውናቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጎ ነበር።

1) ሮም ለምዕራቡ ክፍለ ዓለም መንበረ ሊቀ ጳጳሳት

2) እስክንድርያ ለደቡቡ ክፍለ ዓለም መንበረ ሊቀ ጳጳሳት

3) አንጾኪያ ለምሥራቁ ክፍለ ዓለም መንበረ ሊቀ ጳጳሳት

4) ኤፌሶን በኋላ ቁስጥንጥንያ ለሰሜኑ ክፍለ ዓለም መንበረ ሊቀ ጳጳሳት መሆናቸው ከዘመን ወደ ዘመን ዕውቅና እያገኘ መጣ። ችግር ባጋጠመ ቁጥር የእነዚህ መናብርት ተወካዮች ሲኖዶሱን ወክለው አመቺ በሆነው ስፍራ እየተሰበሰቡ ጉዳዮችን ይመረምሩና ይወስኑ ነበር። በዚህም መሠረት፤

- በ325 ዓ.ም. በኒቅያ 318 አበው ተሰብስበው የአርዮስን ትምህርት መርምረው አወገዙት፥ ለዩት።
- በ381 ዓ.ም. በቍስጥንጥንያ 150 አበው ተሰብስበው የመቅዶንዮስን ትምህርት ከመረመሩ በኋላ አወገዙት።
- በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን 200 አበው ተሰብስበው የንስጥሮስን ትምህርት ከመረመሩ በኋላ አወገዙት።
- በ451 ዓ.ም. ቍስጥንጥንያ አጠገብ በምትገኘው በኬልቄዶን 636 አበው ተሰብስበው የአውጣኪንና የጓደኞቹን ትምህርት ከመረመሩ በኋላ ባለመስማማት ተለያዩ።

10. የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፤

በመንፈሳዊው ቅዱስ ግርቆስ ተቋቁሞ በሲኖዶሱ ዕውቅና አግኝቶ በቈየው በእስክንድርያ በዓለ መንበር 20ኛው ሊቀ ጳጳሳት ከነበረው ከቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፥ ድጋፍና በተቀበለው በፍሬምናጦስ (ዐቢይ አቡነ ሰላማ ከተቴ ዑደታ) የመንፈስ ቅዱስ፥ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ተቋቋመች። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ሆና በዚህ ዐይታ ከተቋቋመች በኋላ በአንዳንድ ችግር ምክንያት እየተቋረጠ ከሚቀጥል በስተቀር

በመንበረ ማርቆስነት ከምትታወቀው ከአስክንድርያ ጳጳስ እየተላከላት ቆየች፥ በመጨረሻም በ1951 ዓ.ም. በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ስምምነት የራሷን መንበረ ሊቀ ጳጳስና በጓላም መንበረ ፓትርያርክ አቋቁማ ራሷን ታስተዳድራለች።

11. ቤተ ክርስቲያን ለመባል ያላት ብቃት

በታሪኳ ውስጥ በሂደት የተከሠቱትን በተለይም ከአባ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በአስተምህሮዋ ውስጥ የበቀሉባትን የትምህርት ዐረሞች በመመልከት ለአንዳንድ ሰዎች «ቤተ ክርስቲያን» የመባሏ ሁኔታ ቢያጠራጥራቸውም ቤተ ክርስቲያን የመባል ብቃቷ እንደተጠበቀ ሆኖ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከሚባሉት መካከል እንዲቁ እርሷ ናት። ይህንንም ለማለት ከበቂ በላይ የሆኑ ምክንያቶች አሉ።

11.1 ምሉዕና ፍጹም የሆነ «ትምህርተ ሥላሴ» አላት። በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ መሆን ታምናለች።

11.2 ሕፀፅና ነቅዕ የሌለበት «ትምህርተ ሥጋዌ» አላት። ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ በተለየ አካሉ ፍጹም ሰው ሆኖ ወገናቹን ለመቤዠት መሞቱን፥ መነሣቱንና በክብር ወደ ሰማይ ማረጉን ታምናለች፥ የዳግም ምጽአቱንም ተስፋ ትሰብካለች።

11.3 ለወንጌል ሥርጭት፥ ለአምልኮ፥ ምእመናንን ለመጠበቅና ለመመገብ አመቺነት ያላቸውን የአጥቢያና የክልል አብያተ ክርስቲያናትን አቋቁማለች። በውስጣቸውም እንደ እግዚአብሔር ቃል፤

- ኤጲስ ቆጶሳት፥ ቀሳውስትና ዲያቆናት ተመድበዋል፤
- ሥርዓተ ጥምቀት ይከናወንባቸዋል፤
- ምስጢረ ቍርባን ይፈጸምባቸዋል።

11.4 ቀኖና መጻሕፍት አላት፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት **አሰትንፋሰ እግዚአብሔር** እንደሆኑ ታምናለች። በ1980 ዓ.ም. **በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በኩል ባሳተመችው መጽሐፍ ቅዱስ**፤

የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት	39
የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት	27
ዲዮትሮካኖኒካል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት	15
	በድምሩ 81

መሆናቸውን ገልጻለች።

11.5 የቤተ ክርስቲያን ችግር

ከጥንት ከመነሻው በመሠረታዊ አስተምህሮዋ ውስጥ ያልነበሩ በረጂሙ የታሪኳ ዘመናት ውስጥ የበቀሉ የትምህርት ዐረሞች ይታያሉ። እነዚህን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለመዘርዘር ከስፍራና ከጊዜ አንጻር አይቻልም። ዳሩ ግን በዚህ በመጨረሻው ክፉ ዘመን በተባለው ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ፍጹማን እንዳልሆኑ እናውቃለን። በሐዋርያት ዘመን በነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥም እንኳ ክፉ ነገር ተገኝቶ ነበር፤ የቆሮንቶስና የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰባቱን የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ መለስ ብለን እንቃኝ።

12.1 የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን (ራእ. 2፥1-7)፤

የቀደመውን ፍቅሩን በመተው ተነቅፎአል፤ «ፍቅር» ጐደለው ማለት ሁሉን ዐጣ ማለት ነበረ፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና (1ዮሐ. 4፥8)። ፍቅርን ማጣት የመቅረዝን መወገድ የሚጋብዝ ጉድለት ነበር። ስለዚህም «ንስሐ ግባ» ተባለ። መቅረዝንም (ቤተ ክርስቲያንንም) የሚያስወግድ እግዚአብሔር እንጂ ሰው እንዳልሆነ ተገለጸ። በታሪክ የመንበረ ሊቀ ጳጳስና ደረጃ እንዲያገኝ ሲኖዶስ የፈቀደለት የስልቅ (የባግዳድ) ቤተ ክርስቲያን ከመቅረዙ ተወግዷል፤ ነገር ግን ምንም በሙስሊሞች ብትከበብ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያ (መቅረዝ) አሁንም አለ።

12.2 የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን (ራእ. 2፥12-17)፤

በዚህ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ጉድለቶች በግልጥ ተጠቅሰዋል።

- «በሰይጣን ዙፋን ሥር ነህ» ተብሏል፤ የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ያመለከ መስሎት በልዩ ልዩ ቅዱሳን ስም የሚጠሩ የሙታን ነፍሳትንና የተለያዩ መናፍስትን አምልኮ ይሆን? የእግዚአብሔር ያልሆኑ ስሞችን (አስማትን) በመድገም ከሰይጣን ጋር ተቈራኝቶ ይሆን? ። የአቴቴ፥ የጨሌ፥ የቦረንትቾ፥ የጥንቆላ፥ የሟርት መናፍስት «ከብቶቼ ናቸው፥ ተጨአቸው ተብለዋል» እየተባለ በውስጡ ሠልጥነውበት ይሆን?
- የበለዓምን ትምህርት የተቀበሉ ከእንተ ጋር አሉ ተብሏል። በለዓም ለባላቅ ባቀረበው ምክር የእግዚአብሔር ሕዝብ በብዓል ፈጎር በዓል እንዲጥፉ፥ የዝሙረ በዓሉን ጠበል-ጠዲቅ እንዲቀምሱ፥ ብዓል ፈጎር በሚሞገስበት ማኅሌት እንዲካፈሉ፥ ከሞዓባውያንና ከሞዓባውያት ጋር እንዲያመነዝሩ ያደረገ ሰው ነበረ። በጴርጋሞንም የእግዚአብሔር ሕዝብ በተከለከለ አምልኮ፥ ጋብቻና ንክኪ እንዲረክስ ያደረገ በለዓምን የመሰለ ክፉ አስተማሪ ተገኝቶ ይሆናል።
- የኒቆላውያንን ትምህርት የሚጠብቁ ካንተ ጋር አሉ ተብሏል። «ክቡር አውሰቦ በኵለሄ፥ ወለምስካቦሙኒ አልቦቱ ሥእበት ፡- መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር፥ መኝታውም ንጹህ ይሁን» (ዕብ. 13፥4) የተባለለትን ሥርዓት ነቅፈውና ጋብቻን እንደ ርኵስ ቈጥረው (1ጢሞ. 4፥1-3) ባልተፈቀደ መንገድ በመሄድ ቅድስናን የሚያረክስ ሥርዓትን መሥርተው ይሆናል።

ይህም ሁሉ ሆኖ የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን በጌታ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ነበረ፤ የንስሐ ዕድልም ተሰጥቶት ነበረ።

12.3. የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን (ራእ. 2፥18-29)፤

የትያጥሮን ማኅበረ ምእመናን እጅግ በከፋ ርኵሰት ተወቅሷል።

- በኤልዛቤል መንፈስ በምትሠራ ነቢይት ይመራ ነበር።
- ሴትነትን ተላብሳ በተገለጠችው በኤልዛቤል መንፈስ አሳብችነት ሥጋዊና መንፈሳዊ አመንዝራነት በትያጥሮን ምእመናን መካከል ተስፋፍቶ ነበር። ከአመንዝራዋ ነቢይት የተመለሱ ሥጋዊና መንፈሳዊ ልጆቿ በማኅበረ ምእመናን መካከል ሠልጥነው ይገኙ ነበር።
- የሰይጣንን ሥራ ዐውቆ ለመጥፍና ለመተው የሚቻለው በጥልቀት ሲለማዱት ነውና እስክምንጠላው ድረስ ርኵሰትን እንለማመድ የሚለው የነቢይቷ ትምህርት የትያጥሮንን ማኅበረ ምእመናን አበላሽቶ ነበር።
- ይህም ሁሉ ሆኖ የትያጥሮን ማኅበረ ምእመናን በጌታ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ነበረ። በውስጡም በነቢይቷ ሥራ ያልተባበሩ፥ ትምህርቷንም ያልተቀበሉ ትሩፋን ምእመናን እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ጸንተው እንዲቆዩ ተመከሩ። ተባባሪዎቿ ግን ከቅጣት በፊት ንስሐ እንዲገቡ ዕድል ተሰጥቷቸው ነበር።

12.4. የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን (ራእ. 3፥1-6)፤

- ማኅበረ ምእመናኑ በሕያው ስም ቢጠራም ሞቷል፤ እንደ ሕያዋን አይኖርም። አይሠራም። (ኤፌ. 2፥1-2፤ ያዕ. 2፥26፤ ይሁዳ 12ፀ13።)
- በማኅበረ ምእመናኑ ላይ ወቀሳን ያመጣ በጎ ሥራን አለመሥራቱ ብቻ አልነበረም፤ መንፈሳዊ ልብስን የሚያበላሽ ርኵሰትም ይሠራ ነበር እንጂ።

ይህም ሆኖ በጌታ ዘንድ የሰርዴስ ማኅበረ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ነበረ፤ የንስሐ ዕድልም ተሰጥቶት ነበር። ያልረከሱ ትሩፋን አባላትም በውስጡ ነበሩ።

12.5. የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን (ራእ. 3፥14-22)፤

- ምንም ሳይኖረው ያለው መስሎ ይታያል፤ ወይም ያለውን ጥቂት ነገር ብዙ አስመስሎ ይቈጥራል። ጌታ ግን ምንም የለህም፥ እኔ ልስጥህ ብሎታል። አለኝ የሚለው መልካም ነገር ምንም ባይኖረውም በጌታ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ተብሏል።
- ስለምወድህ እገሥጽሃለሁና፥ ንስሐ ግባ ብሎታል።
- ድኅ ስለሆንክ ወርቅ ልስጥህ

- ራቁትህን ስለሆንክ ላልብስህ
- ዕውር ስለሆንክ ዓይንህን ላክምህ፥ ልኳልህ ተብሏል።

12.6 የሰምርኔስና የፊልድልፍያ አብያተ ክርስቲያናት፤ ራእ. 2፥8-11፤ 3፥7-13።

እነዚህ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ከመቀሳ ተርፈዋል። ስለ እነርሱ በዚህ ስፍራ ምንም አንልም።

13. ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መፍትሔው

ጉድለት የተገኘባቸው፥ የረከሱ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከላይ እንደተመለከትነው ከጌታ የተሰጣቸው ምክር «ንስሐ መግባት» ነው።

ጉድለትና ርኵሰት በተገኙባቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል እየኖሩ ራሳቸውን የጠበቁትና የሳቱትን መመለስ ያልቻሉት ትሩፋን (ቅሬታዎች) ምእመናንም ጌታ እስኪመጣ ድረስ ከየቤተ ክርስቲያናቸው ሳይወጡና ሳይናወጡ እንዲቆዩ ታዘዋል። ከዚህ የተለየ ሊወሰድ የሚገባ ርምጃ አልተጠቈመም።

14. የአብያተ ክርስቲያናት ደረጃ (ራእ. 1፥12-13፤ 20)

ከአብያተ ክርስቲያናት መካከል ራሳቸውን ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት የሚያስበልጡ፥ ከሌሎቹ ይልቅ ወደ ጌታ የቀረቡ የሚመስላቸው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቀድሞ እንደነበሩ፥ ዛሬም ይኖራሉ። ምናልባትም በሰምርኔስና በፊላዴልፍያ አብያተ ክርስቲያናት ስፍራ ራሳቸውን አስቀምጠው ከሌሎች ይልቅ ለጌታ ያላቸውን ቅርበት የሚለኩና የደረጃቸውን ታላቅነትም የሚናገሩ አይታጡም። ወደ እግዚአብሔር ቃል ስንመለከት ግን ሁኔታው ከሰው አስተሳሰብ እጅግ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን።

14.1 ሰባቱም አብያተ ክርስቲያናት የወርቅ መቅረዞች ናቸው።

አንዳንዶቹ የብር፥ ሌሎቹ የመዳብ፥ ወይም የብረት መቅረዞች ናቸው ተብሎ የልዩነት ደረጃ አልተሰጣቸውም። ጉድለት የተመዘገበባቸውና በድካም የተወቀሱት የኤፌሶን፥ የጴርጋሞን፥ የትያጥሮን፥ የሰርዴስና የሎዶቅያ አብያተ ክርስቲያናትም እንደ ሰምርኔስና ፊላዴልፍያ አብያተ ክርስቲያናት የወርቅ መቅረዞች ነበሩ። ራእ. 1፥12።

14.2 ጌታ በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ነው።

ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በጌታ ዙሪያ ከብበው ታይተዋል፥ ጌታም በአብያተ ክርስቲያናት ክቢ በማእከላይ (መካከለኛ) ስፍራ ላይ ነበር። 1፥13።

15. የአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች በጌታ ዘንድ አኩል ናቸው። (1፥16፥ 20)

የሰባቱም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሁሉም በጌታ ዘንድ የ"ሚበላለጡበት ደረጃ አልነበረም።

15.1 ሁሉም «ከዋክብት» ናቸው ተብለዋል። የተፈጥሮ ከዋክብት ይለያሉ፤ አንዱ ከሌላው በመጠን ይበልጣል፤ ከሌላውም ይበልጥ የሚያበራ ኮከብ አለ። (1ቆሮ. 15፥41) መንፈሳውያን ከዋክብት በተባሉት «ሰባት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች» መካከል ግን በድካማቸው ምክንያት ከተከሠተው ወቅታዊ ሁኔታ የተነሳ በጌታ ዘንድ ልዩነት አልተደረገም 1፥16፤20። በተሰጣቸው የንስሐ ዕድል ካለመጠቀም በኋላ ልዩነት ሊኖር እንደሚችል ግን ይታመናል። ምናልባትም መቅረዛቸው ከስፍራው ሊወገድ ይችላል።

15.2 ሁሉም በጌታ ቀኝ እጅ ነበሩ፥ በጌታ ግራ እጅ መያዝ ጉድለትን ላያመለክት ቢችልም፤ ከአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች እኩሌቶቹ በጌታ ቀኝ እጅ፥ እኩሌቶቹ ግን በግራ እጁ የተያዙ መሆናቸው ቢነገር ኖሮ፥ ያ ሁኔታ የደረጃቸውን መበላለጥ ያመለክታል የሚል ትርጓሜን ባፈለቀ ነበር።

16. የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት እነማን ናቸው?

የመላእክት አምልኮ (የሕርመተ መላእክት) ልምምድ ያላቸው ቡድኖች «የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት» የተባሉት መናፍስት የሆኑ መላእክት ናቸው ይላሉ። ይህም በቤተ ክርስቲያናችን ያልነበረ ዐዲስ ልብ ወለድ ትርጓሜ ነው። በዚህ ስፍራ መላእክተ የተባሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑ ሰዎች ናቸው እንጂ መናፍስት የሆኑ መላእክት አይደሉም። ለማስረጃም፤

16.1 ለያንዳንዳቸው የተላከላቸው ደብዳቤ ይዘት ሰዎች መሆናቸውን አጉልቶ ያስረዳል።

- በ2.5 ወድቀሃልና ንስሐ ግባ ተብሏል። መንፈስ ለሆነው መልአክ ከውድቀት ለመነሣት የንስሐ ዕድል ምንጊዜም በቤተ ክርስቲያን በኩል ሲተላለፍለት አልታየም። ቤተ ክርስቲያን ከሰዎች መካከል የተጠራች የምእመናን ጉባኤ ናት፤ ደግሞም የቤተ ክርስቲያኑ መልአክ (መሪ) ንስሐ ባይገባ ቤተክርስቲያኑን (መቅረዙን) ሊያስወግድ መወሰኑን ጌታ ተናገረ። መንፈስ የሆነ መልአኩ ቢሆን ኖሮ በእርሱ ንስሐ አለመግባት ምክንያት ጉባኤ ምእመናን ትወገድ ዘንድ የሚደረግበት ምክንያት ባልነበረ። እንዲሁም በ2፥14-16፤ 3፥3፤ 19 ተመሳሳይ ሐሳብ አለ።
- በ2፥10-11፤ መከራ ትቀበላላችሁና እስኮሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሚል ምክር ለሰምርኔሱ መልአክ ቤተ ክርስቲያን ተነግሮታል። መንፈስ የሆነ መልአክ ቢሆን ኖሮ በሥጋውያን ሊቀበለው ያለውን መከራ እንዳይፈራ ባልተመከረ፥ ለሕይወት አክሊል የሚያበቃ ሞት እንደሚጠብቀውም ባልተነገረው ነበር።
- በ3፥7-13 አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን ከሚሉት አንዳንዶቹን እሰጥሃለሁ፤ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ ተብሎ ቃል ተገብቶለታል። በተጨማሪም መንፈሳዊት ጽዮን (ኢየሩሳሌም) ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጠላቶቿና ተቃዋሚዎቿ ይገዙላት ዘንድ በኢሳ. 60፥14 የተነገረው ተስፋ ትንቢት ቤተ ክርስቲያኗን በሚመክለው አስተዳዳሪ (መልአክ ቤተ ክርስቲያን) በኩል እንደሚፈጸም የሚናገር ብሥራት ተያይዞ ተነግሮታል።

16.2 ከአበው ተያይዞ የመጣው ትርጓሜ «ሰብዐቱ ከዋክብት መላእክት እሙንቱ፥ እለ ሰብዐቱ አብያተ ክርስቲያናት» የሚለው ንባብ (1፥20) «ሰባቱ ከዋክብት፥ በሰባቱ አህጉር ባሉ ምእመናን ላይ የተሾሙ ሰባቱ መንፈሳውያን ከዋክብት ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው» ተብሏል። በቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ የተለየ ትርጉም ተሰጥቶት አያውቅም። (ትርጓሜ ራእየ ዮሐንስ)

16.3 በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምሮ በዚህ ንባብና ትርጓሜ መሠረት የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪን «መልአክ» ብሎ መሰየም የተለመደና እስከ ዘመናችን የደረሰ ትውፊት ነው። ለማስረጃ፤

- መልአከ ፀሐይ - የመንበረ ፀሐይ ቅ. ማርያም ቤ.ክ አለቃ፥
- መልአከ ገነት - የገነተ ጽጌ ቅ. ጊዮርጊስ ቤ.ክ አለቃ፥
- መልአከ ጎይል - የደብረ ጎይል ቅ. ራጉኤል ቤ.ክ አለቃ፥
- መልአከ ሚሀል - የደብረ ሚሀል ቅ. ሚካኤል ቤ.ክ አለቃ፥
- መልአከ ሰላም - የደብረ ሰላም ቅ. እስጢፋኖስ ቤ.ክ አለቃ፥
- መልአከ ብሥራት - የደብረ ብሥራት ቅ. ገብርኤል ቤ.ክ አለቃ፥
- መልአከ ብርሃን - የደብረ ብርሃን ቅ. ሥላሴ ቤ.ክ አለቃ፥ ወዘተ. የሹመት ስም እንደሆነ ይታወቃል።

17. ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሥር

ኤክሌስያን ተክቶ በገባውና «ቤተ ክርስቲያን» በሚለው ስም እየተጠራች ያለችውን ማኅበረ ምእመናን፥ በዓለም ላይ ካሉት መንፈሳዊና ሥጋዊ ማኅበራትና ድርጅቶች የሚለያት መለዮ ቤተ ክርስቲያን ምንጊዜም ከመንፈስ ቅዱስ ጋርና በእርሱ ምሪት ሥር መሆኗና መሥራቷ ነው።

17.1 ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት ለስብከተ ወንጌል እንዳይሰማሩ «ኀይልን እስክትለብሱ ድረስ ቈዩ» በሚል ትእዛዝ ታገዱ፤ (ሐዋ. 1፥4-5፤ 8) መንፈስ ቅዱስን

ከተቀበሉ በኋላ ግን (2፥1-4) በስብከተ መንጌል ተሰማሩ። (2፥14-36) እነሆ ሐዋርያት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበርና በእርሱም በመመራት ቤተ ክርስቲያንን፤

- በአይሁድ መካከል አቋቋሙ 2፥33፤ 41-42

- በሰማርያውያን መካከል አቋቋሙ 8፥14-17፤ 25

- በአሕዛብ መካከል አቋቋሙ 10፥44-48፤ 11፥18፤ 23-26

17.2 ቤተ ክርስቲያን ከታነጸችባቸው፥ (ከተገነባችባቸው) ምእመናን የትኖውም ቢሆን ለዚህ ጎብረትና አገልግሎት የበቃው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት መንፈስ ቅዱስ ስለገለጠለትና ጠንካራውን ልቡን በቅባቱ አለዝቦ ስላስተማረው ነው። 1ቆሮ. 12፥3፤ 1ዮሐ. 2፥20፤ 27፤ 4፥2።

17.3 መንፈስ ቅዱስ ምእመኑን በማስተማርና በመቅባት ብቻ ሳይወሰን፥ በውስጡ ያድርበታል፤ እንደማጎተምም ይታተምበታል። ዮሐ. 14፥15-17፤ 1ቆሮ. 3፥16፤ 2ቆሮ. 1፥21፤ ኤፌ. 1፥13።

17.4 መንፈስ ቅዱስ አንድ እንደመሆኑ መጠን፥ ያደረባቸውን ምእመናን ሁሉ እርስ በርስ በማገጣጠም የአንድ አጥቢያ፥ የአንድ ክልል፥ የአንድ ሀገር ቤተ ክርስቲያን ብሎም አድናሳዊቷን፥ (ሐዲስ ቅድስት እንተ ላዕለ ሁሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት) ቤተ ክርስቲያን ሆነው ይታነጹ ዘንድ ያስተሳስራቸዋል፤ ያዋሕዳቸዋል። ኤፌ 2፥20-22፤ 4፥3-4፤ 16።

17.5 ዕለት፥ ልሳት ታሉን በማስተማር፥ በማሳሰብና በመቋጮም፥ ምእመናንን በግልም ሆነ በቤተ ክርስቲያን እየመገበ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እስከ ፍጻሜው የሚንከባከብ ባለ አደራ መንፈስ ቅዱስ ነው። ዮሐ. 14፥25-26፤ 16፥12-15፤ ሮሜ 8፥26-27።

17.6 መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችን ለምእመናን አባሎቿ እያደለ፥ በአገልግሎታቸው ቤተ ክርስቲያን እንድትበረታታ ሁልጊዜም በተሐድሶ እንድትኖር ያደርጋል። ሮሜ 12፥4-13፤ 1ቆሮ. 12፥4-31፤ ኤፌ. 4፥7-16።

17.7 ምእመናን ከአሕዛብ ምድር ጋር ከሚያመሳስላቸው ርኩሰት እንዲለዩ፥ በቅድስናም እንዲኖሩ እያበረታታ፥ ያደረባቸውንም መለኮታዊ ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ እያደረገ ፍሬያማ (ትርፋማ) ሕይወትን የሚያለማምዳቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። ዮሐ. 10፥10፤ ሮሜ 8፥10፤ ገላ. 5፥16-26፤ 2ጴጥ. 1፥2-8።

18. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በምስክርነቱና በጸጋ ስጦታዎቹ

ጌታ ኢየሱስን ለመግለጥና ለማክበር የመጣ ስለሆነ፥ (ዮሐ. 15፥26፤ 16፥14) ቤተ ክርስቲያን በምድር እስካለች ድረስ አብሮት ይኖራል። በቤተ ክርስቲያንም መንፈስ ቅዱስ የመኖሩ ዋና ምልክቶች፤

18.1 በመጀመሪያ በጌታ የተነገረውና የሰሙትም ለእኛ ያጸኑት (ያስተላለፉት) የመዳን ወንጌል ሲሰበክ ታላቅነቱ፥ እውነተኛነቱና፥ ፍጹምነቱ እግዚአብሔርም እንደሚፈቅደው መከናወኑ በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታና በሚሠራው ድንቅ ሥራ ይገለጣል። ማር. 16፥17-20፤ ሐዋ. 5፥29-32፤ 10፥44፤ ዕብ. 2፥3-4።

18.2 ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎቷ፥ በድርጅታዊ አሠራሯና በውሳኔዋ የመንፈስ ቅዱስ ስምምነት ይኖር ዘንድ ትጋብዘዋለች፤ የስምምነቱንም መኖር ታረጋግጣለች። ሐዋ. 5፥32፤ 15፥28-29።

18.3 ከስሕተት ለመመለስ፥ ለመገሠጽ፥ ለመጽናናት፥ አዳዲስ ሥራዎችን ለመጀመርና ለመሥራት መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ድምፅ ለምእመናን የግል ሕይወትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ያለማዳረጥ ሁልጊዜ ሊሰማ ይገባል። ማቴ. 10፥19-20፤ ሐዋ. 13፥1-4፤ 16፥6-10፤ 21፥10-16፤ ራእ. 2፥7፤ 11፤ 17፤ 29፤ 3፥6፤ 13፤ 22፤ 14፥13፤ 22፥17።

19. የጉባኤ አምልኮ

19.1 ደቂቀ እስራኤልን ይገዛቸው ከነበረው ከግብጹ ፈርዖን እግዚአብሔር ነጻ ሲያወጣቸው እርሱን እንዲያመልኩና እንዲያገለግሉት ነበረ። ዘጸ. 3፥18፤ 4፥22-23፤ 8፥20፤ 9፥13፤ 12፥31።

19.2 ነጻ ከወጡ በኋላም የመጀመሪያውን የአምልኮ ጉባኤ አደረጉ። በቅኔ፥ በዝማሬና በማጎሌት በከበሮም በመታጀብና በመቀባበል (በማስተዛዘል) እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አደረጉት። ዘጸ. 15፥1-21።

19.3 ደቂቀ እስራኤል በዘመናት ውስጥ በመዘምራን እየተመሩ በልዩ ልዩ የዜማ ዕቃዎችም እየታጀቡ፥ በዜማ፥ በእልልታ በንግግርም፥ በስግደትም (በአስተብርኮም) እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ኖረዋል። 2ዜና. 29፥27-30፤ መዝ. 89፤ 98፤ 150፤ ዕዝ. 3፥10-11፤ ነህ. 12፥27።

19.4 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነጻ የወጡ ክርስቲያኖች የእውነተኛ ነገር ጥላና ምሳሌ የሚሆን የበታና የሌላም ግዙፍና ውሱን ነገር መኖርና አለመኖርን ዋና ጉዳይ ሳያደርጉ፤ በግልም በጉባኤም በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ ታዘዋል። ዮሐ. 4፥23-24፤ ፊል. 3፥3።

19.5 በክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ ከአምልኮ ዘርፎች ዋናዎቹ በ1ቆሮ. 14፥26 ተዘርዝረዋል።

19.5.1 መዝሙር፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዲስ ኪዳንን ሥርዓት ሲያቋቁም በሥርዓተ ቍርባን ፍጻሜ ወንድሞቹ ከሚላቸው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ዘመረ። ማቴ. 26፥26-30፤ ማር. 14፥22-26 ዝማሬውም በመንፈሰ ትንቢት «ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤ በማኅበርም መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ» ሲል አስቀድሞ ያናገረው መፈጸሙን የሚያበሥር ሁኔታ ነበረበት። መዝ. 22፥22፤ ዮሐ. 17፥6።

በመዝሙር ማምለክ ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው የተለማመዱትና መመሪያ የሰጡበት የአምልኮ ዘርፍ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ኤፌ. 5፥19፤ ቈላ. 3፥16-17

19.5.2 ትምህርትና መገለጥ፤ ምእመናን የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኖርባቸው ዘንድ፥ መንፈስ ቅዱስ በጸጋ ስጦታው በመደባቸው መንጌላውያንና መምህራን (1ቆሮ. 12፥28፤ ኤፌ. 4፥11) አማካይነት በጉባኤያቸው ቃሉን መማር ይገባቸዋል። ይህም የቅዱሳን ልምምድ ነበር። የሐዋ. 19፥9-10፤ 20፥7-12፤ 18-21፤ 1ቆሮ. 12፥7-8፤ 14፥3፤ 12፤ 24፤ 15፥1-11፤ ቈላ. 3፥16፤ 4፥16፤ 1ጴጥ. 3፥15።

19.5.3 በልሳን መናገርና በልሳን የተነገረውን መተርጐም፤ በጉባኤ የሚነገር ልሳን ትርጉም ያለውና ጉባኤው የሚታነጽበት ሊሆን ይገባዋል። የሐዋ. 11፥28-30፤ 21፥10-11፤ 1ቆሮ. 14፥27-30።

19.5.4 - ሥርዓተ ቍርባንን መፈጸም፤ የሐዋ. 2፥42፤ 1ቆሮ. 10፥16-22።

19.5.5 - ሥርዓተ ጥምቀትን መፈጸም፤ አንዳንድ ጊዜ የሚጠመቁ በጉባኤ ይጠመቃሉ። የሐዋ. 2፥41-42፤ 11፥45-48

19.5.6 - ጸሎትን ማድረስ፤ በሐዋርያት ጉባኤ ይደረግ ከነበረው አንዱ «ጸሎት» ነበረ። የሐዋ. 2፥42፤

- በጸሎት ውስጥ እንደ ጌታ ትምህርት ምስጋናና ውዳሴ፥ ልመናና ኑዛዜ፥ በሐዋርያትም እንደተደነገገው ምልጃ ከፍተኛውን ስፍራ ይይዝ እንደነበረ ግልጽ ነው። ማቴ. 6፥9-13፤ ኤፌ. 5፥20፤ 6፥18፤ ፊል. 4፥6፤ ቈላ. 4፥2። 1ጢሞ. 2፥1-2።

19.5.6 - መባዕን መሰብሰብ። 1ቆሮ. 16፥1-2፤ 2ቆሮ. 8እና9።

10. ቅዱስ ቊርባን

በጮራ ቁጥር 16 «ቃል ኪዳን» የተሰኘውን ዋና ቃል ስንመረምር ጥምቀትና ቅዱስ ቊርባን የአዲስ ኪዳን ምስጢራት መሆናቸውን አይተናል። በቊ. 18ም ጥምቀት ወደ አዲስ ኪዳንና ወደ ቤተ ክርስቲያን የመግቢያ ሥርዓት መሆኑ ተገልጧል። ከዚያም በተጨማሪ ቅዱስ ቊርባን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘው የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ምልክትና ማጎተም ማረጋገጫም መሆኑን መመርመር ይገባናል።

ቅዱስ ቊርባን «የጌታ እራት» እና «ሥጋሁ ወደሙ» በመባልም ይታወቃል። ቅዱስ ጳውሎስ ምእመናኗ በሥርዓቱ በአንድነት መሳተፍ ላልቻሉባት ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ «...የምትበሉት የጌታ እራት አይደለም ...» በማለት ወቀሳ ሰንዝሯል፤ 1ቆሮ. 11÷17-22 በተጨማሪም ሐዋርያው ሳይገባው (ያልተገባው ሆኖ ሳለ) ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት በማለት አስጠንቅቋል፤ 1ቆሮ. 11÷27-30። ምክንያቱም «የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? ...» የሚለው ቃል የሚበላውና የሚጠጣው ከክርስቶስ ጋር አንድነታችንን ማጠንከሩን ያሳያል፤ 1ቆሮ. 10÷16-22።

ክርስቶስ የፋሲካን እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከበላ በኋላ የቅዱስ ቊርባንን ሥርዓት ደነገገ፤ ማቴ. 26÷26-30፤ ማር. 14÷22-26፤ ሉቃ. 22÷14-20፤ 1ቆሮ. 11÷23-25። ከዚህ በላይ ከተጻፉት አንቀጾች በስተቀር ስለ ቅዱስ ቊርባን በቀጥታ የሚያመለክት በመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ክፍል የለም።

እውነት ነው ብዙዎች «የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። የሚለው አንቀጽ ቅዱስ ቊርባንን እንደሚያመለክት ያምናሉ፤ ዮሐ. 6÷52-58። ይህ አተረጓጐም ግን ክርስቶስ ከተናገረበት ጊዜ÷ ከአድማጮቹ ሁኔታና ከሰጠው ሌላ ትምህርት ጋር የሚስማማ አይመስልም። ክርስቶስ ይህን የተናገረው የቅዱስ ቊርባንን ሥርዓት ከደነገገበት ጊዜ በትንሹ አንድ ዓመት ይቀድም ነበርና አድማጮቹ ከሥርዓቱ ጋር ሊያገናኙት አይችሉም÷ ዮሐ. 6÷43 ከ13÷1 ጋር ያስተያዩ። ክርስቶስ ይህን ሲናገር የሚበዙቱ አላመኑበትም 6÷36፤ 52፤ 60፤ 66፤ 71)። የቅዱስ ቊርባንን ሥርዓት ሲደነግግ ግን አምነው የተቀበሉት ሰዎች ብቻ ከእርሱ ጋር ነበሩ። ይህንም አተረጓጐም የማንቀበልበት ዋና ምክንያት ክርስቶስ፥ ሰው የዘለዓለም ሕይወት የሚያገኘው በእርሱ በማመን እንደሆነ በዚህ አንቀጽ በማስተማሩ ነው። ደግሞም «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።» በማለቱ እምነትን በመብላትና በመጠጣት መሰለው፤ 6÷35፤ 47-48። ይህ አንቀጽ ቅዱስ ቊርባንን ያመለክታል የሚሉ ወገኖች ስሕተት÷ ክርስቶስ በምሳሌ አገላለጥ መናገሩን እንጂ ቃል በቃል አለማስተማሩን ያለመረዳታቸው ነው÷ ቁ. 63 ይመልከቱ። ለመሆኑ ክርስቶስ እዚህ ላይ የሚያስተምረው ምንድነው? በትምህርቱ ተጣምረው የምናያቸው ሁለት እውነቶች አሉ፤ እነርሱም የዘለዓለም ሕይወት የሚገኘው በክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑና ይህም ሕይወት በክርስቶስ ሞት ለሚያምኑበት ሁሉ መገኘቱ ናቸው÷ ቁ. 51። ቅዱስ ቊርባንም እነዚህን ሁለት እውነቶች ያስተምራል፤ ያሳይልም።

1. ቅዱስ ቊርባን ማስተባበሪያ ነው

ከአንድ መሶብ በፍቅር አብሮ መብላት ታላቅ ደስታ ነውና ከእኛ ጋር ከሚበሉት ጋር ኅብረት እንዳለን ይሰማናል። ቅዱስ ጳውሎስም በጌታ እራት ከዚህ የበለጠ ኅብረት እንዳለ ዐውቆ «አንድ እንጀራ ስለሆነ÷ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና» ብሏል። የክርስቲያን አንድነት በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም÷ ምክንያቱም አስቀድመን እንዳየነው ሁላችን በእምነት ከክርስቶስ ጋር በቅዱስ ቊርባን እንሳተፋለን። በዚህም ምክንያት «የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም ...» ብሏል። ስለዚህ ቅዱስ ቊርባን ከባዕድ አምልኮት የመለየት ግዴታ እንዳለብን ያሳየናል። መጀመሪያ ከክርስቶስ÷ ቀጥሎም ከሌሎች ምእመናን ጋር ያለንን ኅብረትም ያጠነክራል፤ 1ቆሮ. 10÷14-22።

2. ቅዱስ ቊርባን ማስተማሪያ ነው

የቅዱስ ቊርባንን ማስተማሪያነት መግለጽ የምንፈልገው ከሦስት ምክንያቶች የተነሣ ነው፤

ሀ) መታሰቢያ ነው፤ «ሶበ ዘንተ ትገብሩ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ። ይህን ስታደርጉ መታሰቢያዬን አድርጉ» በመጽሐፈ ቅዳሴ እንደተባለውና በእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጸው (ሉቃ. 22÷19፤ 1ቆሮ. 11÷24-25።) ኅብስቱ ሲቈረስ የክርስቶስ ሥጋ ስለ እኛ እንደተቈራረሰ÷ ወይኑ ሲፈስስም የክርስቶስ ደም ስለ እኛ እንደፈሰሰ እናስታውሳለን። እያንዳንዳችን ቅዱሳት

ምስጢራትን ስንቀበል «ያ ሥጋ የደቀቀው፥ ያም ደም የፈሰሰው ስለ እኔ ነው» ብለን ማሰብ ይገባናል።

ለ) ማስታወቂያ ነው፤ (1ቆሮ. 11፥26።) በፋሲካ እራት ጊዜ ልጆች ስለ እራቱ ምንነት ሲጠይቁ አባቶቻቸው «በግብጽ አገር ... ቤቶቻችንን ያዳነ የእግዚአብሔር የማለፉ መሥዋዕት ይህች ናት» ብለው ይመልሳሉ፥ (ዘጸ. 12፥26-27።) በአይሁድ ሥርዓት መሠረት በየዓመቱ የሚበላው የፋሲካ በግ በግብጽ አገር የታረዱት በጎች ደም ሕዝብን ከእግዚአብሔር ቁጣ ማዳኑን እንደሚያስታውቁ ሁሉ፥ በቅዱስ ቊርባን የምንቀበለው ኅብስትና ወይንም የሥጋውን መቈራረስና የደሙን መፍሰስ ባስቀደመው በክርስቶስ ሞት ከዘለዓለም ኩነኔ እንደዳንን ያስታውቃሉ። ቀሳውስትም በቃል «መነሃ ትሳተፉ ለቅድሳት ወለሙኑ ትንብሩ ተዝካሮ በአኰቴት ትቀደሱ ዘንድ በምስጢረ ቊርባን ከማን ጋር ልትዛመዱ፥ የማንንስ መታሰቢያ በምስጋና ልታከብሩ ቀረባችሁ?» በማለት ምእመናንን ይጠይቃሉ። በምሳሌም የኅብስቱ መቈራረስና የወይኑ ፍሬ ተጨምቆ በጽዋ መቅረብ፥ በኅልኀታ የተደረገውን ያመለክታል። ምእመናኑም ፍንዜኑ ሞተከ እግዚእ ወትንሣኤከ ቅድስተ፥ አቤቱ ሞትህንና ትንሣኤህን እንናገራለን» (መጽሐፈ ቅዳሴ) እያሉ ታሪኩን በጀሮና በዐይን ይግራሉ።

ሐ) መግለጫ ነው፥ (ማቴ. 26፥29፤ 1ቆሮ. 11፥26።) አማኞች ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ የጌታን እራት ይበላሉ፥ ይጠጣሉም። ሲመጣ ግን በግሩም ሁኔታ በክብር ከጌታቸው ጋር በ«በጉ ሰርግ እራት» ላይ ይቀመጣሉ፥ (ራእ. 19፥9።) ስለዚህ ቅዱስ ቊርባን ክርስቶስ የሚመጣ መሆኑን ያሳያል፥ እየተቃረበም መሆኑን ያረጋግጣልና ሲመጣ ከእርሱ ጋር እንደሚበሉና እንደሚጠጡ ይገልጣል።

3. ቅዱስ ቊርባን ማሳደጊያ ነው

ሰው ሲበላና ሲጠጣ ሕይወቱን ያድሳል፤ ያድጋልም። እንደዚሁ «ሥጋሁ ወደሙ» ሲቀበልም በነፍሱ ያድጋል። እንጀራ ለመኖር፥ ወይንም ደግሞ ለደስታ እንደሚሰጡ ሊያሳየን ይችላል። ቅዱስ ቊርባን ቢያንስ በሦስት ምክንያቶች ማሳደጊያ ነው፤ እነርሱም፥

ሀ) እንቅፋትን ያስወግዳል። ሰው ቅዱስ ቊርባን ከባድ ምስጢር መሆኑን በመገንዘቡ፥ ከመቀበሉ በፊት ራሱን ይመረምራል፤ ስለ ኃጢአቱ ንስሐ ይገባል፤ ከወንድሙም ጋር ይታረቃል፤ 1ቆሮ. 11፥27-32።

ለ) እውነተኛ ምግብን ያስገኛል፤ (ዮሐ. 6፥51።) ሥርዓቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት ያሳስባል። ይህንም በማድረግ አማኙ፥ ክርስቶስ የኃጢአቱ ማስተስረያ በመሆኑ በክርስቶስ ደም መሠረት እግዚአብሔር ልጅነትን እንደሰጠው፥ ኃጢአቱን ይቅር እንደሚለውና መንግሥቱን እንደሚያወርሰው ያውቃል፤ ወይም በዐጭሩ አለኝታ እንዳለው ይገነዘባል።

ሐ) ቁርጥ ውሳኔ ላይ ያስደርሳል። ኢየሱስ «እንካችሁ ብሉ ... ጠጡ» ብሎ አዝዟል፤ (ማቴ. 26፥27።) እንግዲህ ሰው በመቀበልም ይሁን ባለመቀበል ወደ ውሳኔ ይደርሳል። አማኙ በመብላትና በመጠጣት ከክርስቶስ ጋር አንድነት እንዳለው ያሳያል። ውሳኔውም በመጀመሪያ በክርስቶስ ሞት መዳኑን፥ ሁለተኛ ክርስቶስን በሁለንተናው መከተሉን፥ ሦስተኛው ክርስቶስ የሞተበትን ዓላማ፥ ይህም ከዘለዓለም የተመረጡት ወደ ሕይወት የሚደርሱበትን ተግባር ለመፈጸም በራሱ አርአያነትና ምስክርነት እንደሚጥር መቁረጡን ያሳያል።

የጌታ እራትን በዚህ መልክ ከተመለከትነው አንዳንድ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ። አንደኛው ቅዱስ ቊርባን ለክርስቲያን መንገድ ስንቅ ወይስ የበቁ ሰዎች ዋጋ ነው? ምእመናን ሁሉ ራሳቸውን መርምረው እንዲቈርቡ ታዝዘዋል እንጂ በረከቱ ለጥቂት «ቅዱሳን» የተወሰነ ነው የሚል ፍንጭ ፍጹም አይገኝም።

ሁለተኛው፥ ጌታችን በቅዱስ ቊርባን ውስጥ በምን አኳኋን ይገኛል? የሚለው ነው። ስለዚህ ብዙ አሳብ አለ። ክርስቶስ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ» የሚለውን የተስፋ ቃል በመስጠቱ በቅዱስ ቊርባን ሥርዓትም እንደሚገኝ እርግጠኞች ነን፤ (ማቴ. 18፥20።) እርሱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከሚያምኑት ጋር ነው (ማቴ. 28፥20) የሚገኘውም በመንፈስ እንጂ በሚታይና በሚዳሰስ ሁኔታ አይደለም፤ 1ጴጥ. 1፥8-9።

እንደዚህ ከሆነ በቅዱስ ቊርባን አማካይነት እርሱን በምን አኳኋን እንቀበለዋለን? የሚለው ሦስተኛ ጥያቄ ይነሣል። መልሱ «በእምነት ነው»። የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት ስንቀበል በቃሉ ውስጥ ያለውን ተስፋ ሁሉ በእምነት እንደምንጨብጥ ሁሉ፥ ክርስቶስን በቅዱስ ቊርባን የምንቀበለውም በእምነት ነው። ሰው ካላመነ ከእግዚአብሔር ቃል ምንም ጥቅም እንደማያገኝ ሁሉ፥ እምነት የሌለው ሰውም በቅዱስ ቊርባን እንጀራና ወይንን እንጂ ክርስቶስን አይቀበልም፤ ፍርድን እንጂ በረከትን አያገኝም።

የመጨረሻው ጥያቄ «ቅዱስ ቊርባን» ለዚህ ምስጢር ትክክለኛ ስያሜ ነውን? የሚል ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር ያቀረቧቸው መሥዋዕቶች ቊርባን የሚል ስያሜ ተሰጣቸው፤ ዘሌ. 1፥2፤ 9፤ 2፥1። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ክርስቶስ የደነገገው ሥርዓት ቊርባን ተብሎ ሲጠራ አናገኝም። ምክንያቱም ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለዘለዓለም ኃጢአትን ሁሉ የማስወገድ ብቃት ያለውን መሥዋዕት አቅርቧል፤ (ዮሐ. 19፥30፤ ሉቃ. 23፥45-46፤ ዕብ. 10፥12፤ 1ጴጥ. 3፥18።) ቅዱስ ቊርባን የዚህ ታላቅ ተግባር መታሰቢያ ነው። ለኃጢአታችን ሌላ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልግም፤ አንችልምም። ቀሳውስት በአገልግሎታቸው ቅዱሳት ምስጢራትን ለኃጢአት መሥዋዕት ሳይሆን፥ በምስጋና በእግዚአብሔር ፊት ያቀርቧቸዋል፤ (ማቴ. 26፥26-27፤ 1ቆሮ. 11፥23-25።) በኋላም ምእመናን እንዲቀበሏቸው በክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት ያቀርቡላቸዋል። በዚህ ሥርዓት ተቀባይ አማኙ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። እግዚአብሔር የተቀበለው መሥዋዕት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ያቀረበው ነው። ይህም አንድ ጊዜ ለዘለዓለም የተፈጸመ ነውና አይደጋገምም። እንግዲህ ይህን በማሰብ ስንቃችንን እየተቀበልን ወደ መንግሥተ ሰማያት የምናደርገውን ጉዞ እስከ መጨረሻው እንቀጥል!

ዮፍታሔና ቤተሰቡ

የዮፍታሔን ታሪክ የምናገኝበት የመሳፍንት ዘመን እግዚአብሔር የገዛ ሕዝቡን ለማዳን ባስነሣቸው ታዋቂ መሳፍንት አማካይነት ትድግናው የታየበት፥ ከእስራኤል ሕዝብ የውድቀትና የመከራ ታሪኮች መካከል አንዱ ነበር። ይህ ታሪክ በሚጀምርበት ጊዜ፥ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንደገና ማምለክ ትተው ነበር። በእርሱ ፈንታ በአካባቢያቸው ይኖሩ የነበሩ አሕዛብ ያመልኳቸው የነበሩትን በዓልን፥ አስታሮትንና ሌሎች ጣዖታትን ወደ ማምለክ ተመለሱ። ስለዚህ እግዚአብሔር «በፍልስጥኤማውያንና በአሞን ልጆች እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። በዚያም ዓመት የእስራኤልን ልጆች ሥቃይ አበዙባቸው» መሳ. 10፥7-8።

አሞናውያን በዮርዳኖስ ምሥራቅ በኩል ጀምረው ወደ ምዕራብ ተሻገሩ። ከ18 የጭቆና ዓመታት በኋላ «እስራኤልም እጅግ ተጨነቁ» (ቁ. 9)። ወደ እግዚአብሔር ሲጮሁ ግን፥ ፈጣንና ቀላል መልስ አልሰጣቸውም። ባዕዳን አማልክትን ከመካከላቸው ሲያስወግዱና በእውነተኛ ንስሐ እርሱን ወደ ማምለክ ሲመለሱ ግን፥ «ነፍሱ ስለ እስራኤል ጕስቍልና አዘነች» (ቁ. 16)። ስለዚህ እግዚአብሔር ዮፍታሔንም ያስነሣው እነርሱን ከእንደዚህ ዓይነቱ ጕስቍልና ለማውጣት ነበረ።

የማይንከባከቡት ልጅነት የማይረካ ልብን ያሸክማል

«ገለዓዳዊውም ዮፍታሔ ... ጀግና ወታደር ነበረ» (11፥1)። የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ በእነዚህ ቃላት ከ12ቱ መሳፍንት ሁሉ እጅግ ውስብስብ ከሆነው ከዚህ ታሪክ ጋር ያስተዋውቀናል። በመቀጠል ስለ ዮፍታሔ ቤተሰባዊ መነሻ መሠረት የሚነግረንም ዮፍታሔ እንዴት ጦረኛ ሰው ሊሆን እንደቻለ ይገልጣል። ገለዓድ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በያዕቆብ ዘመን ተጠቅሳ የምናገኛት፥ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ የነበረች አገር ናት። የዮፍታሔ አባት ስም ገለዓድ መሆኑም በገለዓድ ነገድ ውስጥ አባቱ የትልቅ ቤተሰብ መሪ መሆኑን ይጠቁማል። ምንም እንኳ ገለዓድ ከሕጋዊት ሚስቱ ልጆች ቢኖሩትም፥ ዮፍታሔን የወለደው ከጋለሞታ ሴት ነበረ። ስለሆነም ልጆቹ እያደጉ ሲሄዱ ዮፍታሔን እንደ ውጪ ልጅ በመቍጠር አገለሉት፤ አባረሩትም። «የልዩ ሴት ልጅ ነህና በአባታችን ቤት አትወርስም» (ቁ. 2) አሉት። የዮፍታሔ የመገለል ስሜት ቤተሰቡ በነገዱ ውስጥ ከነበረው ቁልፍ ሚና አንጻር ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነበረ። ስለዚህ ከወንድሞቹ ሸሽቶ በገለዓድ ሰሜን ምዕራብ በሚገኝ፥ ሽፍቶች በሚኖሩበት ምድረ በዳ በጦብ ምድር ተቀመጠ። በአካባቢው የዘራፊዎች ቡድን ተሰባስቦ ነበርና ዮፍታሔ በሁሉም የሽፍትነት ዘዴዎች በጣም በመለማመድ አደገ። ነገር ግን በዚያ ጭፍን የወንድ የበላይነት በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ዮፍታሔ ሚስት አገኘ፤ እንዴት ልጅ ተወለደችላቸው። እርሷም በበረሀ ውስጥ አንድ የምታምር አበባ በድንገት ብቅ እንደምትል፥ በጦብ አደገች፥ ፍቅር ይራብ ለነበረው የዮፍታሔ ልብም መመኪያና ደስታ ሆነች።

ይሁን እንጂ ቤትን ለመሥራት ጦብ የተመቸ ቦታ አልነበረም። ስለሆነም አንድ ቀን ለዮፍታሔና ለትንሽ ቤተሰቡ የክሥተቶችን አቅጣጫ ፈጽሞ የለወጠ አንድ ነገር ሆነ። አሞናውያን እስራኤልን እንደገና ወረሩ፤ የዮፍታሔን የውጊያ ችሎታ በእርግጥ ሰምተው የነበሩ የገለዓድ ነገድ አለቆችም ዮፍታሔ አዛዣቸው ሆኖ ከአሞናውያን ጋር የሚያካሂዱትን ጦርነት እንዲመራ ይጠይቁት ዘንድ መልእክተኞች ወደ እርሱ ለመላክ ወሰኑ።

የዮፍታሔ የመጀመሪያ መልስ እርሱን የጠሉበትን የጭካኔ መንገድና ከአባቱ ቤት ያስወጡበትን ሁኔታ ለአለቆች የሚያስታውስ ነበረ። ከእነርሱ ጋር ትክክለኛ በሆነ የሽፍትነት መልክ ስምምነት አደረገ። እነርሱ ፈልገውት የነበረው በጦርነቱ ላይ በኖና አዛዥነት እንዲመራቸው ብቻ ነው። እግዚአብሔር በአሞናውያን ላይ ድል ካጐናጸፈው በኋላ፥ የእነርሱ መሪ ይሆን ዘንድ እንደ ተገቢ ቅድመ ሁኔታ አድርጎ ተናገረ። ነገር ግን በመልሱ መካከል ላይ ምናልባት ለመጨረሻ ውሳኔ ቍልፍ የሆነ፥ ከእጃቸውም ከተቀበለው መገፋት የተነሣ ያደረበትን ቂም ሁሉ አጉልቶ የሚገልጥ፥ ልብን የሚነካ ሐረግ አለ። ይኸውም «እንግዲህ ወደ ቤቴ ከመለሳችሁኝ» (11፥9) የሚለው ነው።

«ወደ ቤት ከመለሳችሁኝ» የሚለው ዮፍታሔ ኑሮት የማያውቀው ቤት ማለት ነው። እናቱ ሕጋዊ ካልሆነው ልጇ ጋር የምትጋራው ምንም ቤት ስላልነበራት የተነቀፈች ሴት ነበረች። ከአባቱ የሚወለዱ ወንድሞቹም የአባቱ ቤተሰብ አባል መሆኑን አልተቀበሉም። አሁን ግን መጨረሻ ላይ የስምምነታቸው ማሰሪያ «ቤት» መሆን ነበረበት። ምናልባት እዚህ ላይ ለሚሰቱና (አሁንም ከእርሱ ጋር እንዳለች በማሰብ) ለትንሿ ልጁ ትክክለኛ ቤት የሚሠራበት አንድ የሕይወት ዕድል ነበረ። ጥሩ ጓደኞች ምናልባትም ተስማሚ ባል ለማግኘት፥ ይህ የልጁ ሕይወት አንድ ዕድል ይሆናል። አዎ፥ የ«ቤት» መጠቀስ የዮፍታሔን ልብ በኃይል ጐተተው። ቤት የማቋቋሙ ዐሳብ እንደ ማግኔት ሠራ። ስለዚህ «ዮፍታሔም ከገለዓድ ሽማግሌዎች ጋር ሄደ» (ቁ. 11)።

ነገር ግን ወዴት ሄደ? በገለዓድ ወደምትገኘው «የመጠበቂያ ማማ» ወደ ምጽጳ እንጂ የተጻፈውን ያህል ወደ አባቱ ቤት በመጀመሪያ አልሄደም። የገለዓድ ሽማግሌዎችና ሕዝቡ ባሉበት፡ «ቃሉን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ... ተናገረ» (ቁ. 11) የሚለው በዚያ ስፍራ ስለ ነበረው የመጠበቂያ ማማው ልዩ ሃይማኖታዊ ትርጕም ይሰማል። ምናልባት በልጅነት ሕይወቱ በአንድ ወቅት፡ ዮፍታሔ ስለ እግዚአብሔር በዚያ መማር ጀምሮ የነበረ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በአሞናውያን ላይ ድልን የሚያጐናጽፈው እግዚአብሔር እንደሆነ ያለ ጥርጥር ዐውቋል። ከሠላሳ ወይም ከአርባ ዓመታት በፊት ስለ እግዚአብሔር መማር እዚህ ተጀምሮ ይሆን? ብቸኝነቱንና መጣሉን በእግዚአብሔር ፊት አሽቀንጥሮ ለመጣል ምናልባት ወደዚህ ወደ መጠበቂያ ማማው ገና ልጅ ሳለም መጥቶ ይሆን? ወደ ጦብ ሲሄድ እግረ መንገዱን በመጠበቂያው ማማ በኩል ዐልፎ ይሆንን? ወደ «ቤት» መመለስ ማለት ለዮፍታሔ፥ መንፈሳዊ መሠረቶቹ ወዳሉበት ቦታ ወደ ምጽጳ ተመልሶ መምጣትም ነው።

ወደ ቤት መምጣት እንዴት አስደናቂ ነገር ነው! «ቤት» ለሕፃኗ ሕይወት ምን ያህል አስፈላጊ ነው! እውነተኛ ቤት ሕፃናት ተቀባይነት የሚያገኙበት፥ የሚወደዱበት፥ እንክብካቤ የሚያገኙበት ቤት ነው። የሚያድጉበት፥ ሁልጊዜ የሚናፍቁትና ተመልሰው ለመምጣት የሚወዱት የራሳቸው የሆነ ቦታ ነው። በተለይም «ቤት» መንፈሳዊ ቤትም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት የተጀመረበት ቦታ ሲሆን፥ ወደ ቤት ለመምጣት ያለው ግፊት ሁልጊዜ በይበልጥ የጠነከረ ነው። ስለዚህም ዮፍታሔ ወደ ቤት ወደ ምጽጳ፥ ወደ አባቱ ቤት መጣ።

የማይመጣጠን ትምህርት ያልተጠበቀ ስሕተትን ያስከትላል

ቀጥሎ የሆነው (የተፈጸመው) ዮፍታሔ ስለ እግዚአብሔር ያገኘውን የዕውቀት ዓይነት የበለጠ ያሳየናል። በገለዓዳውያን ላይ አዛዥና አለቃ ሆኖ በግልጽ ከተሾመ በኋላ፥ «አገሬን ለመውጋት ወደ እኔ የምትመጣ አንተ ከእኔ ጋር ምን አለህ?» (ቁ. 12) በማለት መልእክተኞችን ወደ አሞናዊው ንጉሥ ላከ። እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ አሁን እንዲመለስላቸው የፈለጉትን የአሞናውያንን መሬት መስደው እንደነበረ የሚገልጽ መልስ መጣ። የዮፍታሔ መልስ የወቅቱን ታሪክ ትክክለኛ ዕውቀት ያሳያል። ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን ተናገረ።

መጀመሪያ፤ እስራኤል መሬቱን የወሰደው ከአሞናውያን ሳይሆን፤ ከአሞራውያን ንጉሥ ከሴዎን ነበረ።

ሁለተኛ፥ መሬቱን ለእስራኤል የሰጠው እግዚአብሔር ነው።

ሦስተኛ፥ እስራኤል መሬቱን ከያዘው አሁን 300 ዓመት ሆኖአል።

ስለዚህ አሞናውያን መሬቱ የእነርሱ እንደሆነ አድርገው በእርግጥ ካሰቡ፥ ቀደም ሲል እንዲመለስላቸው እስራኤልን ለምን አልጠየቁም? «ፈራጁ እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆችና በአሞን ልጆች መካከል ዛሬ ይፍረድ» (ቁ. 27)።

ምናልባት የታሪክን ስሜት በዮፍታሔ ውስጥ ቀስ በቀስ እያስረዳ የሄደ የዮፍታሔ ቤተሰብ ዋና ስፍራ ሳይሆን አልቀረም። በጦብ ውስጥ እንደ ሽፍታና ኃያል ጦረኛ ያሳለፋቸው ዓመታትም ደግሞ ስለ ሕዝቡ የፖለቲካ እድገት ለነበረው አድናቆት አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ጥርጥር አልነበረውም። ቢያንስ፥ ቢያንስ እጠያያቂ በሆነ በአንድ ልዩ ወቅትም ጥንቃቄ ያለበት ጥናት አድርጎ ነበር። ሙቁትና ድንበሮች በጦብ ውስጥ ለብዙ ዓመታት በሽፍትነት በነበረበት ጊዜ በተሰማማባቸው ዲፕሎማሲያዊ ውሎች ትልቅ ስፍራ ነበራቸው። የእግዚአብሔር መገለጥ የነበረበትን ይህን ክፍል ዮፍታሔ በእርግጥ ተደስቶበታል። ሆኖም መልእክቱ ከአሞናውያን ንጉሥ ምንም መልስ አላስገኘም።

«የእግዚአብሔርም መንፈስ በዮፍታሔ ላይ መጣ» (ቁ. 29) በአሞናውያን ላይም ጥቃት ለመሰንዘር ወጣ። እግረ መንገዱን ቤቱ ይገኝበት በነበረውና የመጠበቂያ ግጣው ባለበት በምጽጳ በኩል ዐለፈ። ከእግዚአብሔር ጋር ቀጠሮ የያዘበት ቦታ እዚህ ነበረ። መልእክቱን ወደ አሞናውያን ንጉሥ ልኮ፥ አሁን ዐሳቡን ወደ ጌታ ማቅረብ ፈለገ። «ዮፍታሔም በእውነት የአሞንን ልጆች በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ፥ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደኅና በተመለስሁ ጊዜ፥ ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል፥ ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ» (ቁ. 30-31)።

ዮፍታሔ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፥ በሚመለስበት ወቅት ይሆናል ብሎ ያሰበው በእርግጥ ምን ይሆን? ሮጦ ወጥቶ ለእርሱ ሰላምታ ለማቅረብ የመጀመሪያው ውሻ፥ ወይም ደግሞ ሊሞት የተቃረበ ሽማግሌ አገልጋይ ሊሆን ይችላል ብሎ አልገመተ ይሆን? ወጥታ በመሮጥ ሰላምታ የምታቀርብለት ሚስቱ ወይም ተወዳጇ ልጁ ልትሆን እንደምትችል አላሰበ ይሆን? የሚቃጠል መሥዋዕትስ የሚሆኑት እነርሱ ይሆኑን? የአብርሃምን ታሪክና ለውን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብን በተመለከተ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያስተማረውን ትምህርት ዮፍታሔ አላወቀውምን? እግዚአብሔር የሰውን መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ አለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን፥ ፈጽሞ እንደ ከለከለው አልተረዳ ይሆን? በዘሌዋውያን ሕግ «ከልጆቻችሁ ማንኛውንም በእሳት ውስጥ እንዲያልፍ አታድርጉ፤ የአምላካችሁን ስም ማስነወር አይገባምና» የሚል ተጽፎ ይገኛል። የዚያ ዐሳብ ይዘት የአሞናውያንን አምላክ ሞሎክን የሚመለከት ነው። ነገር ግን የእስራኤል ታዳጊና ጌታ የሆነው አምላኩ እንደዚህ ዓይነቱን ጭካኔ እንደሚፈልግ ዮፍታሔ በእውነት ዐስቦ ይሆን?

ዮፍታሔ ስለ እግዚአብሔር ከፊል ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ምሳሌና ከተፈጥሮ ፍላጎታቸው ጋር የሚገናኙትን ብቻ ከሚያውቁ ጋር የሚመደብ ሰው ነው። ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በዚህ ዓይነት ይመለከቱታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ የሚያውቋቸው ክፍሎች ይገኛሉ። ያለ ማቋረጥም እየተመለሱ ያነብቧቸዋል። እንዲያውም በቅክክል ይጠቅሷቸዋል። ይሁን እንጂ የማያውቋቸውና ምናልባትም ፈጽሞ ያላነበቧቸው ሰፋ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የምንገኝ ከሆንን፥ ስለ እግዚአብሔር ያለን ዕውቀት ሚዛናዊ እድገት እንደሌለው ዛፍ ይሆናል፤ የሕይወት ማዕበል ሲመጣም ሊሰበር ይችላል። ዮፍታሔ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ቢያንስ የተወሰኑትን ክፍሎች ዐውቋል፤ ሆኖም የእግዚአብሔርን ሕግ ያወቀ አይመስልም። በታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የፈጸማቸው ተግባራት ተገልጠዋል፤ በሕግም የእግዚአብሔር ፈቃድ ተገልጧል። ወላጆች ሁለቱን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፤ ልጆቻቸውን «በጌታ ምክር» (ኤፌ. 6፥4) ማሳደግ የሚችሉ በሳል ወላጆች መሆን ካለባቸው፥ በብሉይና በዐዲስ ኪዳናት የተካተተውን «የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ» (ሐሥ. 20፥27) በእርግጥ ሊያውቁ ይገባል። ይህ ተገቢነት አባላቱ ዘወትር ጌታን በማወቅ ያድጉ ዘንድ፥ ጠቅላላ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የሚያስችል የታቀደ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መርሐ ግብርን ያካትታል። ከዚያም በኋላ በሚያውቋቸው የተወሰኑ ክፍሎች ላይ ሳይሆን፥ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጠው የጌታ ባሕርይና መንገድ የተመጣጠነ ዕውቀት ላይ ተመርኩዘው ውሳኔ ላይ መድረስ ይችላሉ።

የማይቈጣጠሩት ንግግር ያልታሰበ ጉዳትን ያስከትላል

ዮፍታሔ ለጌታ ስእለት በተሳለበት ጊዜ፥ በከፍተኛና በሚገፋፋ ስሜት ውስጥ ነበረ። የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ውጊያው ይገሠግሥ ዘንድ ሲቀሰቅሰው ሊሰማው ይችላል። እሽቅድምድም ላይ ሊጋልብ እንደሚቅበጠበጥም ፈረስ አድርጎት ይሆናል። የዮፍታሔ ዲፕሎማሲያዊ ስልት ከሰው ጋር በሚያደርጋቸው ንግግሮች ታላቅ ችሎታ እንደነበረው ያሳያል። ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው ንግግር ግን በጊዜ ግፊት በጥድፊያ የተደረገ ይመስላል። «ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ፥ እግርህን ጠብቅ፤ ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መሥዋዕት ይበልጣልና፤ እነርሱም ክፉ እንዲያደርጉ አያውቁምና» እግዚአብሔር በሰማይ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን፥ በእግዚአብሔርም ፊት ቃልን ይናገር ዘንድ ልብህ አይቸኩል፤ ስለዚህም ቃልህ ጥቂት ትሁን።» ከሰባኪው አንደበት የተሰነዘሩ የጥበብ ቃላት መክ. 5፥1-2።

በእርግጥ ድል አሁንም ረጅም መንገድ የሚያስኬድና ወደ ቤት መመለሻውም በቀን መቁጠሪያው ላይ በጣም ያልታወቀና ያልተወሰነ መስሎ ይታያል። እነዚህን ቃላት ተናግሮ «ዮፍታሔም ሊዋጋቸው ወደ አሞን ልጆች ዐለፈ፤ እግዚአብሔርም በእጁ አሳልፎ ሰጣቸው» (ቁ. 32)። ዮፍታሔ በጦርነቱ 20 ከተሞችን ደመሰሰ፤ በውጤቱም ምናልባት ከጠበቀው ቀደም ብሎ እስራኤል አምንን ተቈጣጠረ።

እንግዲህ ዮፍታሔ ምጽጳ ውስጥ ወዳለው ቤቱ የሚመለስበት ጊዜ ደረሰ፤ ያም ቤት የሚወድዳት ልጁ የነበረችበት ነው። ምጽጳም ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት፥ ስእለቱን ሁልጊዜ የሚያስታውሰው ቦታ ነው። የመጠበቂያ ማማውን እንዳለፈ የገባውን ስእለት እንዴት እንደሚፈጽም ሳያሰላስል አልቀረም።

ከመጠበቂያ ግማው ወደ ቤቱ እየተቃረበ ሲሄድ «ሴት ልጁ አታም ደዛ እየጨፈረችና እየጨፈረች ልትቀበለው ወጣች።» ከእርሷ ሌላ ወንድም ሆነ ሴት ልጅ እንዳልነበረውና ልጁ እርሷ ብቻ እንደነበረች፤ መጽሐፍ ቅዱስ ልብ በሚሉ ሁኔታ ያስታውሰናል (ቁ. 34)። ከወር ሚዳ በድል የሚመለስ ሠራዊትን በዚህ ዓይነት መንገድ ሴቶች መቀበላቸው በእስራኤል የተለመደ እንደነበረ እንኳ ዮፍታሔ አላስታወሰ ይሆን? የሙሴ እኅት ማርያም ቀይ ባሕር በግብጻውያን ላይ ከተገኘው ድል በኋላ ሴቶችን የመራችው ከበሮ እየመታችና እየዘመረች አልነበረምን? (ዘጸ. 15፥20-21)። በአሞናውያን የተገኘው የድል ወሬ የዮፍታሔን በዚያ መድረስ ሳይቀድም አልቀረም፤ ከዚህ የተነሣም አባቷን በዚህ መንገድ ለመቀበል ከወጡት መካከል ልጁ የመጀመሪያዋ ለመሆን መፈለጓ ብቸኛ አማራጭ ነበረ።

የዮፍታሔ ታላቅ ሐዘን ምን እየተደረገ እንደነበረ ሲያረጋግጥ ሳለ፥ ልብሱን በመቅደዱና በመራር ልቅሶው ተገልጿል፤ «እመይ ልጄ ሆይ! ... በጣም አዋረድሽኝ፥ አስጨነቅሽኝም» (ቁ. 35)። በጊዜው በነበረው ግፊት የተነገሩት ቃላት በሕይወት ዘመን ዘላቂ የሆኑ ውጤቶችን አሁን የሚያመጡ ናቸው።

የማይናወጥ ታማኝነት ያልተወሰነ በረከትን ያስገኛል

ዮፍታሔ ስለ እግዚአብሔር ያልገባው ወይም ያላወቀው ብዙ ነገር ነበረ። ነገር ግን አንድ ነገር በግልጽ ተረድቷል። «እኔ ለእግዚአብሔር በመሐላ ቃል ገብቼ ተስያለሁ፥ ልመልሰውም አልችልም»። ይህ አመለካከት ለእግዚአብሔር ስለሚደረግ ስእለት አስፈላጊነት በመጽሐፈ መክብብ ላይ በተሰጠው ተከታታይ ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ የተመሠረተ ነው። «ሰነፎች ደሰ አያሰኙትምና ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ፤ የተሳልኸውን ፈጽመው። ... ሥጋህን በኃጢአት እንዲያስተው ለአፍህ አርነት አትስጥ፥ በመልአኩም ፊት፦ ስሕተት ነበረ አትበል፤ ... አንተ ግን እግዚአብሔርን ፍራ።» (መክ. 5፥4-7)። ዮፍታሔ ያደረገው ያንኑ ነው። የሚያስደንቀውም ነገር ገና ወጣት ልጃገረድ የነበረችው ልጁ አባቷ ተስሎ እንደነበረ ማረጋገጫና፥ «አባቴ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ቃል ገብተህ ከሆነስ እግዚአብሔር

ጠላቶችህን አሞናውያንን ስለተበቀለልህ በእኔ ላይ ልታደርግ ያቀድከውን ፈጽም።» (ቊ. 36) ማለቷ ነው።

በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት ላይ አባቷ የተጐናጸፈው ድል ከራሷ የግል ደስታ የበለጠ አስፈላጊ እንደነበረ ልጅቱ ከዕድሜዋ በላይ በብስለት ተረዳች። በፈቃደኝነትም ራሷን ለአባቷ አስገዛች። በገለዓድ ገና ከተገኙ አዳዲስ ሴት ጓደኞቿ ጋር ለማልቀስ ሁለት ወር ለመነች። በዘመኗ ለነበረችዋ ልጃገረድ አንድ አሳፋሪ (አዋራጅ) ውድቀት ብቻ ነበረ፤ ያም ልጅ አልባ ሆኖ መገኘት ነው፤ እርሷም አሁን ልትሞት ነው፤ ሞቷም ልጅ አልባ ሆኖ መሞት ብቻ ሳይሆን፥ ገና ሳታገባም መሆኑ ነው። በእርግጥ በኮረብታዎቹ ዙሪያ እያለቀሱ የመንከራተት ጉዳይ ነበረ። ነገር ግን ሁለቱ ወራት ሲፈጸሙ፥ በታማኝነት ወደ አባቷ ተመለሰች፤ «እርሱም ለእግዚአብሔር ቃል የገባውን ፈጸመ» (ቊ. 39)።

ይህን እንግዳና አሳዛኝ ሁኔታ የምንገመግመው እንዴት ነው? ሰውን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብን እንደከለከለ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሁለቱ፥ በአብርሃም ታሪክና በሙሴ ሕግ በግልጽ ተናግሮ ሳለ፥ ዮፍታሔንና የወሰደውን እርምጃ እንዴት ሊቀበለው ይችላል? እግዚአብሔር ዮፍታሔን እንዴት እንደገመገመው መጽሐፍ ቅዱስ ፍንጭ ይሰጣል? ዮፍታሔ የተሳለውን ስእለት ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመረምር፥ ሦስት ነገሮችን ልብ ማለት ያስፈልገናል።

- በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ መጥቷል፤ (ቊ. 29)። ይህም ዮፍታሔ ማንኛውንም ስሕተት ከመፈጸም ነጻ ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን ላስነሣበት የወደፊት ዘመቻ (ጦርነት) በእግዚአብሔር ተቀብቶ ነበረ ማለት ነው። ለውጊያው በመውጣት ዮፍታሔ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር ነበረ።
- ሁለተኛ የተናገራቸው ቃላት የእምነትን ዐሳብ ይዘዋል፤ «ድል አድርጌ ከዘመቻ ወደ ቤቴ ስመለስ» (ቊ. 31)። እግዚአብሔር ድል ስለሚያነናጽፈው፥ ዘመቻው ውጤታማ እንደሚሆን ዮፍታሔ ሙሉ በሙሉ አመነ፤ ከ11፥9 ጋር አነጻጽር።
- ሦስተኛ ስእለቱ ከተነገረ በኋላም እንኳ እግዚአብሔር ዮፍታሔን ባረከው፤ አሞናውያንን በእጁ አሳልፎ በመስጠት የእምነቱን ትክክለኛነት አረጋገጠ።

ከልጁ ሞት በኋላ ከኤፍሬማውያን ጋር መገናኘቱና ከዚያም ቀጥሎ የነበረው ጦርነት በዮፍታሔ በኩል በበለጠ ዲፕሎማሲና በመለስተኛ ተቃውሞ ሊወገድ የቻለ ሌላው አሳዛኝ ሁኔታ የነበረ ይመስላል። በልጁ ሞት ያደረበትን ጸጸት ሁሉና ታምቆ የነበረውን ሐዘን ምናልባት ያወጣው በዚያ ውጊያ ወቅት ነበረ። እርሱም እስራኤልን ስድስት ዓመት ብቻ ስለመራ፥ ብዙ ጊዜ በሕይወት አልቈየም። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾችን አገላብጠን ወደ ዕብራውያን መልእክት ብንሄድ፥ ከዚህ ችግር ሁሉ ባሻገር፥ «እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፤ በትክክለኛ ፍትሕ አስተዳደሩ፤ የተሰጣቸውን ተስፋ አገኙ፤» (ዕብ. 11፥33) ተብሎ በመጽሐፍ ከተነገረላቸው ሰዎች መካከል የዮፍታሔ ስም በክብር መዝገብ ተጠቅሶ እናገኛለን። የዮፍታሄ ስም እንደ እርሱ እጅግ እንቆቅልሽ ሕይወት በነበረው በሳምሶንና «እንደ እግዚአብሔር ልብ» (ሐ.ሥ. 13፥22) ተብሎ በተነገረለት በዳዊት ስም መካከል ይገኛል። እግዚአብሔር ሰውን የሚቀበለው ሕግን በመጠበቁ ሳይሆን፥ እምነትን በእርሱ በመለማመዱ ነውና። የእግዚአብሔርን ሕግ ከመጠበቅ አንጻር ቢፈረድበት፥ እኛ ሁላችን እንደምናደርገው፥ ዮፍታሔ ወድቋል። ነገር ግን ዮፍታሔ «ጀግና ወታደር» የእምነት ሰው ሆነ።

የዮፍታሔ እምነት በአሞናውያን ላይ ለተጐናጸፈው ድል በእግዚአብሔር ላይ ከነበረው ትምክህት አንጻር ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ጥሪ ተረድቶ በታዛዥነት በመፈጸሙም ጭምር ተንጸባርቋል። ከሚወዳትና ብቸኛ ልጁ ከነበረችው እንኳ እግዚአብሔር መቅደም እንደሚገባው ተረድቷል፤ በዚህም ውስጥ ጌታ ኢየሱስ፥ «ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንና ልጆቹን፥ ወንድሞቹንና እህቶቹን፥ የራሱንም ሕይወት እንኳ ከእኔ አብልጦ የሚወድ ከሆነ የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም።» (ሉቃ. 14፥26) በማለት ለሐዲስ ኪዳን ምእመናን ከሰጠው የሕይወት መስፈርት ውስጥ በዚያን ጊዜው በብሉይ ኪዳን አመለካከት በተወሰነ መጠን ተረድቶ እንደ ነበረ ታሪኩ ሊያስረዳ ይችላል።

እስካሁን ስለ ዮፍታሔ ከተመለከትናቸው ትንተናዎች ውስጥ ለዚህ ዘመን ክርስቲያን ወላጆች የሚጠቅሙ ሁለት ዋና ትምህርቶችን መቅሰም እንችላለን :-

- የመጀመሪያው ለእግዚአብሔርና ለልጆቻቸው በሚናገሯቸው ቃላት ላይ ወላጆች ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። በአሰቸጋሪ እርግዝና ወይም ከብዙ የመካንነት ዓመታት በኋላ ስለ ተገኘ ልጅ ለእግዚአብሔር የተናገራችኋቸው ቃላት ሁሉ ለእግዚአብሔር ሕያዋን ናቸውን? ልጃችሁ ታሞ በነበረበት ወቅት ለእግዚአብሔር በተናገራችሁት ታማኞች ናችሁ? የተናገራችሁትን እግዚአብሔር አይዘነጋውም። ልጃችሁን ከመውደድ አስቀድሞ ወይም በላይ እግዚአብሔርን ትወዱታላችሁን? ለልጆቻችሁ የምትናገሯቸው ቃላት ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚነገሩ ናቸውን? ቃላችሁንስ ትጠብቁላቸዋላችሁን? አንድ ነገር እንደምታደርጉላቸው ስትነግሯቸው መልካም ነገርም ይሁን አስፈላጊ ቅጣት እንደምትፈጽሙት በእናንተ ሊተማመኑ ይችላሉን? ቃልን ማክበር በሰማዩ አባታችን ሁል ጊዜ ያለ ነው፤ ወላጆችም ለሚናገሩት ቃላት ባላቸው ታማኝነት፥ ይህንኑ ጠባይ በግል ከሰማያዊ አባታቸው ባሕርይ የተወሰነውን ማንጸባረቅ ያስፈልጋቸዋል። የዮፍታሔ ልጅ በአባቷ ውስጥ የታየውን ይህን ጠባይ አከበረችው። የክርስቲያን ወላጆች ልጆችም በወላጆቻቸው የሚያዩትን ተመሳሳይ ጠባይ እንደዚሁ ማክበር መቻል አለባቸው።
- ሁለተኛው ትምህርት ክርስቲያን ወላጆች በሚፈጽሟቸው ስሕተቶችና በልባቸው ውስጥ በሚኖሩት አነሳሽ ምክንያቶች መካከል ያለውን ልዩነት እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን ያስገንዝበናል። ስለ ልጆቻቸው ዐልፎ፥ ዐልፎ የተሳሳተ ውሳኔ ሲወስኑ፥ ወይም ደግሞ ከልጆቻቸው መካከል ለአንዱ **ትክክለኛ ያልሆነ ምክር ሲሰጡ ወላጆችሁ**ሉ፥ ውጤቱ ወይም ግቡ አሰቃቂም ሊታያቸው ይገባል። አንድ ነገር ሲያደርጉ፥ ወይም ልጃቸው እንዲያደርግ ሲከለክሉ በእርምጃቸው የልጃቸውን የወደፊት ሕይወትም እንኳ ምናልባት ሊያበላሹ እንደሚችሉ ማሰብ አስፈላጊ ነው።

እነዚህን በመሳሰሉ ስሕተቶች ከሚያድርባቸው ጥልቅ ሐዘንና ጸጸት የተነሣ ብዙ ሊሠቃዩ ይችላሉ። የዮፍታሔ ታሪክ ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ወላጆች የመጽናናት መልእክት አለው። ምንም እንኳ ውሳኔዎች ሁል ጊዜ የብስለት ውሳኔዎች ባይሆኑም፥ ወይም ደግሞ ስለ እርሱ ባሕርይና መንገዶች የተመጣጠነ ግንዛቤ ባይፈነጥቁም፥ እግዚአብሔር ከስሕተቶች ባሻገር በእርሱ ስላሉ እምነት ወደሚሰጥ መሠረታዊ ትምህርትና እርሱን ለማክበርና ለመታዘዝ ወደሚታየው ፍላጎት ያመለክታል። ለተዘበራረቁና እጅግ ውስብስብ ለሆኑ የሕይወት እንቆቅልሾች እግዚአብሔር በእምላካዊ ዕቅዱ መፍትሔ ሰጥቷል፥ ስለሆነም ከዘለዓለማዊነት አመለካከት አቅጣጫ ሙሉ ዕቅዱ ይገለጣል።

በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል በተሰጠን የተሟላ ዕውቀት መሠረት የዮፍታሔን ልጅ ሰም አንድ ቀን ግወቅ እንደምንችል ለማመን ሙሉ መደፋፈር አለን። በዕብራውያን መልእክት ውስጥ በተገለጡት ታላላቅ የእምነት ሰዎች የክብር መዝገብ ባትጠቀስም እንኳ፥ ገና የመጨረሻው ክብር በሰማይ ሲሰጥ እርሷም ተጨምራ እንደምናገኛት መጠበቅ ይኖርብናል። ስሕተተኛው ሰው ዮፍታሔ ለተሳለው ስእለት ታማኝ ስለ ነበረ፥ እግዚአብሔር የበኩሉን ለመፈጸም የበለጠ ታማኝ ይሆናል፤ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ለእግዚአብሔር ይሆናልና (መሳ. 11፥31) «የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» (ዘፍ. 18፥25)። ዮፍታሔ መክሰት የነበረውን የእውነተኛ ፈራጅ ባሕርይ በግልጥ ያሳየው ለታሉ ባለው ታማኝነት ነው።

የሚሳሳቱ ክርስቲያን ወላጆች ንስሐ መግባትና ስሕተቶችን ለማስተካከል የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ነገር ግን በመጨረሻ ላይ ለእርሱ የገቡትን ሁሉ ማክበር የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከሐዋርያው ጋር በእንድነት «ያመንሁትን ዐውቃለሁና የሰጠሁትንም እደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ።» (2ጢሞ. 1፥12) ብለው ያውጁ።

መንፈሳዊ ትረካ

ከነቅዐ ጥበብ

አለቃ ነቅዐ ጥበብ በሚከተሉት አስተምህሮ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ወገን ናቸው ተብሉ በብዙ ሊቃውንት ይነገርላቸዋል። በነገረ መለኮት ትምህርት ቤትና በመድረክ በሚያስተላልፉት ትምህርት የተዋሕዶ እምነት ሊቃውንት «ይበል፥ መልካም፥ እግዚአብሔር ቃለ ሕይወት ያሰማ!» እያሉ ይባርኳቸዋል። «ካለፉት ነገሥታት ሰይፍ ጥቂት መምህራንን አትርፍ ለተዋሕዶ እምነት ትንሣኤ ይሰጡ ዘንድ አለቃን የመሰሉ ሊቃውንት በቃለ እግዚአብሔር ተመልደው እንዲቆሙ ያደረገ የአባቶቻችን አምላክ ይባረክ» በማለትም ልዑል እግዚአብሔርን ያከብራሉ።

በሌላው ጐን ደግሞ የካራ እምነት ተከታዮች አለቃ ነቅዐ ጥበብ በተናገሩ ቍጥር አንገታቸውን ደፍተው ያጉረመርማሉ። መቼም የአባብ ልጅ ያው እባብ መሆኑ አይቀሬ ነውና የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከተል የካራ ልጆች በእነአለቃ ነቅዐ ጥበብ አገልግሎት ላይ በየጊዜው በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት እየተገኙ አደጋ ሲያደርሱ ኖረዋል።

ከምእመናን አብዛኛዎቹ ግን በሁለቱ እምነቶች መካከል ያለው የአስተምህሮ ልዩነት እንዲብራራላቸው አለቃ ነቅዐ ጥበብን በጽሑፍም በቃልም ሲጠይቁ ቈይተዋል። በተዋሕዶና በካራ እምነት ደጋፊዎች መካከል ጸብ በተፈጠረባቸው አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ የዕለተ እሑድ ተማሪዎች በዘንድሮው «ርክበ ካህናት» በዓል በግልጽ ይወያዩ ዘንድ አለቃ ያቀረቡት ሐሳብ ዐብይ አቡነ ፍሬምናጦስ ስለ ጸደቀ በዛሬው ቀን ይህ የውይይት መድረክ በፍካሬ መጻሕፍት ትምህርት ቤት መከፈቱን አለቃ አበሠሩ።

የደብረ መንክራት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መልአከ መንክራት ጥዑመ ልሳን ጉባኤውን በጸሎት ከፈቱ፤ ቀጥሎም የዚሁ ቤተ ክርስቲያን የዕለተ እሑድ ተማሪዎች፤ አባት ሆይ፥ በስምህ አንድ እንዲሆኑ ጠብቃቸው የሚለውን በግእዝ፤

«አ አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ፥ አ አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ፥

በስምከ ወበኀይልከ ዕቀቦሙ፤

ከመ ይኩኑ አሐደ ብነ ከማነ፥ ከመ ይኩኑ አሐደ ብነ ከማነ፥

ከመ ይኩኑ።» እያሉ በጸሎት መንፈስ ዘመሩ፤ ጉባኤውም ተከተላቸው፤ በጭብጨባና በእልልታም አጀባቸው።

የመርሐ ግብሩ መሪና አስተባባሪ፥ አለቃ ነቅዐ ጥበብ ከወንጌለ ማቴዎስ 22፥29 «ወአውሥአ ኢየሱስ ወይቤሎሙ፦ ትስሕቱ በኢያእምሮ መጻሕፍት ወኢ ኀይለ እግዚአብሔር፥ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል አታውቁምና ትስታላችሁ» የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር ካነበቡ በኋላ፥ ሲያብራሩ፤

- ክርስቲያን ለሚያምነውና የኔ ብሎ ለያዘው እምነት መሠረቱ ግድግዳና ጣሪያ፥ ጉልላቱ ቅዱሳት መጻሕፍት መሆን አለባቸው፤ የእምነት አስተምህሮውን በቅዱሳት መጻሕፍት ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ሊጨርስ፥ ሊደመድም ይገባዋል።
- ማንም ቢሆን የቅዱሳት መጻሕፍትን ኀይለ ቃል ከተነገረበት ዐላማ ውጪ ላለ ጉዳይ መሠረትም ሆነ ድጋፍ እንዲሆን ሊጠቅሰው አይገባውም።
- እያንዳንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ኀይለ ቃል የተነገረበት ዐላማ በዐውደ ንባቡ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ሰፍሮ ይገኛል።
- አንድ ኀይለ ቃል በዐውደ ንባቡ ውስጥ ከተነገረበት ዐላማ ውጪ ሌላ ሁለትና ምስት፥ አሻሚና አሳሳች ትርጉሞች አይኖሩትም።

ታዲያ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰይጣንም ይጠቅሳቸዋል፤ (ማቴ. 4፥6) ግን ከተነገሩበት ዐላማ ውጪ ላለ ጉዳይ ስለሚጠቅሳቸው የሰይጣን ዐላማ ተቀባይነት አይኖረውም» አሉ አለቃ።

በመቀጠልም «ከፍ ብሎ በጠቀስኩት በወንጌለ ማቴዎስ ያነበብኩት ኀይለ ቃል ጌታ ኢየሱስ ሊከራከሩት ለቀረቡት ሰዱቃውያን የሰጣቸው ምላሽ ነው። እነርሱም በንግግራቸው መክፈቻ በኦሪት ዘዳግም 25፥5-10 ያለውን ኀይለ ቃል ጠቅሰው ነበረ፤ ጌታ ኢየሱስም የሰጣቸውን መልስ አሁን ሰምተነዋል። ስለዚህ በአንድ ርእሰ ጉዳይ የተለያየ ሐሳብ ይዛችሁ ለውይይት በቀረባችሁት በሁለታችሁም በኩል የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ለአባባላችሁ በማስረጃነት ስትጠቅሱ ጥንቃቄ ልታደርጉ እንደሚገባ አሳስባችኋለሁ።

በዚህ መንፈስ ውይይታችሁ ርእሱን ተከትሎ ከመሥመሩ ሳይወጣ፥ በአግባቡ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የቀረቡለት መሆኑን እንዲከታተሉና የግራ-ቀኙን ሐሳብ ተቀብለው ከመረመሩ በኋላ የዳኝነት ውሳኔያቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡና ለጉባኤው እንዲያሰሙ፥

ሊቀ ሊቃውንት ዮሐንስ	ዳኛ
መጋቤ ብሉይ ኢያሱ	ዳኛ
መጋቤ ሐዲስ ጳውሎስ	ዳኛ
ርእሰ ደብር ደምፀ ቃለ አብ	ታዛቢ
መምህርት ሲያዱ	ታዛቢ
እማሆይ ኤልሳቤጥ	ታዛቢ

እንዲሆኑ በሁለታችሁም በኩል በአንድ ድምፅ በመመረጣቸው ለዳኞችና ለታዛቢዎች የተመደበውን ስፍራ እንዲይዙ እጠይቃለሁ። እንዲሁም፤ የተዋሕዶ እምነትንና የካራ እምነትን መክለው የቀረቡት፤

ከደብረ መንክራት ኢየሱስ

ዲያቆን ሥምረተ አብ

ዕጩ ዲያቆን ገብረ ክርስቶስ

ከደብረ ፋይድ ገብርኤል

ሊቀ ዲያቆናት ኀይለ ማርያም

ዲያቆን ሀብተ ሥላሴ

መሆናችሁ ከየአጥቢያችሁ በተጻፈ ደብዳቤ ስለተረጋገጠ፤ የተመደበላችሁን ስፍራ እናንተም እንድትይዙ እጋብዛለሁ» በማለት አለቃ አሳሰቡ። ከዚያም ሁሉም ስማቸው የተጻፈበትን ወንበር በመረከብ ተቀመጡና የውይይቱ ሥነ ሥርዓት ቀጠለ።

ቀደም ሲል የደብረ ፋይድ ገብርኤል ዕለተ እሑድ ተማሪዎች «መልአክ እንደ እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ ነው» ሲሉ በበራሪ ጽሑፍ በትነው ስለ ነበረና የደብረ መንክራት ኢየሱስ ዕለተ እሑድ ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ የተቃውሞ መልስ ሰጥተው ስለነበረ ይኸው ርእሰ በሁለቱም መንኖች ለውይይት ተመረጠ።

በበራሪ ወረቀቱ ላይ በዐውር ቃል የተገለጸው ሐሳብ ሰፋ ያለ በመሆኑ ለውይይት እንዲያመች፥ እንዲተነተንና ርእሰ ይዞ እንዲቀርብ ዳኞቹና ታዛቢዎቹ ተስማሙና ርእሶቹ እንደሚከተለው ተቀርጸው ቀረቡ።

1. መልአክ ምሉዕ በኩለሄ ወይስ ውሱን መንፈስ?
2. ክርስቲያን ወደ ማን ይጸልይ? ወደ መናፍስት?
3. የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ከየት እስከ የት?

በእነዚህ ላይ በቅድሚያ የማስረዳቱ ዕድል በዕጣ ለደብረ ፋይድ ገብርኤል ዕለተ እሑድ ተግሪዎች ደረሰ።

አንደኛ፤ የውይይት ርእስ፥

መልአክ ምሉዕ በኩለሄ ወይስ ውሱን መንፈስ?

የደብረ ፋይዶች ማብራሪያ፤

«አንዱ መልአክ እግዚአብሔር በሚገኝበት በማናቸውም ስፍራ ይገኛል፤ ለዚህም ማስረጃው ወደ ዘካርያስ የተላከው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፤ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ ማለቱ ነው። ሉቃ. 1፥19

በእግዚአብሔር ፊት ሁሉ ነገር ስለሚታይ መልአኩ ሁሉን በሚያይ በእግዚአብሔር ፊት ከቆመ እግዚአብሔር የሚያየውን ሁሉንም ነገርና ሁሉንም ስፍራ ያያል ማለት ነው። ቅዱስ ገብርኤል በሁሉም ስፍራ ስሙን በሚጠሩት ሁሉ ዘንድ ሊገኝ ሁሉንም ሊያይ፥ በሁሉም የሚባለውን ሊያዳምጥ ይችላል።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ መላእክትም መናፍስት ናቸው፤ መንፈስ በሆነው እግዚአብሔር ፊት መሆን እንደ እርሱ በሁሉ ቦታ መሆን ማለት ነው።

በተጨማሪም በመዝሙረ ዳዊት 34 (35)፥7። «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል» ስለሚል አንዱ መልአክ በስፋትና በምልዐት ስፍራን ሁሉ የመሸፈን ብቃት እንዳለው ያመለክታል» ሲሉ ደብረ ፋይዶች አብራሩ።

የደብረ መንክራቶች መልስ፤

«እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ የሆነ ሕያው መንፈስ ነው፤ ሰማያትንና ምድርን፥ ባሕርንና ቀላያትን፥ ሲያልንና ዝክንን፥ ገዢነ እላትንና መንግሥተ ሰማያትን ሁሉ በአንድ ጊዜ ማየት የሚችል፥ ህላዌውንም ጠብቆ በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ የሚገኝ ሲሆን፤ በአጠቃላይ የሚታዩና የማይታዩ ዓለማትና በውስጣቸው ያሉ ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ ቍጥጥር ሥር ይገኛሉ። ወደ ፍጡራን ስንመጣ ግን፤

1) በዓለመ መንፈስና በዓለመ ግዘፍ ተመድበው ይኖራሉ።
2) ሁሉም በየዓለማቸው ውስጥ በተሰጣቸው ውሱን ሥራና ስፍራ ጸንተው ይኖራሉ።
3) መናፍስትም ቢሆኑ ከተወሰነላቸው ዓለም ወደ ሌላው ዓለም፤ በዚያው በሚገኙበት ዓለምም ቢሆን ከነበሩበት ወዳልነበሩበት ዐዲስ ስፍራ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ብቻ ይሄዳሉ።
4) መላእክት በውሱንነት የሚታወቁ ፍጡራን መናፍስት ናቸውና እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ አይገኙም።
5) ምሉዕ በኩለሄነት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ ልዩ መገለጫ ስለሆነ፥ ለእግዚአብሔር ብቻ ይነገራል እንጂ ለፍጡራን ባሕርይ መገለጫ ሆኖ ሊነገር አይችልም። ኢዮብ 11፥7-10፤ መዝ. 139፥7-10፤ ኤር. 23፥24፤

ስለሆነም በእግዚአብሔር ፊት መቆም እግዚአብሔር የሚያየውን ሁሉ ማየት፥ እግዚአብሔር የሚሰማውን ሁሉ መስማት ያስችላል ለሚል ዓላማ የቀረበው ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፤ ሕያውም ሆነ ኢሕያው ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ፥ በዓይናቹም የሚታይ ነውና። ቅዱስ ገብርኤል ብቻ ሳይሆን ፍጥረት ሁሉ ማለት የቆመውም፥ የተቀመጠውም፥ የተኛውም፥ የሚንቀሳቀሰውም የተሸፈነውም የተገለጠውም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይኖራል። ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ፥ በዓይናቹም የሚታይ ነውና። ዕብ. 4፥13።

እያንዳንዱ ፍጥረት ሁሉ ምንም በእግዚአብሔር ፊት ቢሆን ከሚኖርበት ዓለም ውጪ ያለውን አያየውም፥ አያውቀውም። በሚኖርበት ዓለም ውስጥም ቢሆን እንኳ በወሰነ ህላዌ የተገደበ ስለሆነ ከወሰነ ህላዌው ውጪ ከሚኖረው ሌላ ፍጥረት ጋር አይተያይም፤ አይተዋወቅም። በእግዚአብሔር ፊት ያለን ኢትዮጵያውያን በእግዚአብሔር ፊት ያሉትን አሜሪካውያንን አናያቸውም። በእግዚአብሔር ፊት ያለን እኛ ምድራውያን በእግዚአብሔር ፊት ያሉትን ሰማያውያን ፍጥረታት ልናያቸው አንችልም፤ ወሰነ ህላዌያችን አይፈቅድልንም።

ምሉዕ በኩለሄ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት መሆንና ግንልገል የተፈጥሮ ህላዌ ውሱንነትን ሊያጠፋና ወደ ኢውሱን መንፈስነት ወይም ወደ ምሉዕ በኩለሄነት ማንንም ለማሸጋገር አይችልም።

እንደ ተጨማሪ ማስረጃም ሆኖ የቀረበውን፥ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል (መዝ. 35፥7)» የሚለውን የቤተ ክርስቲያናችን አበው ሲተረጉሙ «አንድ መልአክ እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ዙሪያ ይከትማል፥ ይሰፍራል ማለት አለቃው መልአክ ካለበት ጭፍሮች መላእክት አይለዩምና፥ ሠራዊቱን በአለቃው ሰይሞ መናገር ነው» ብለውታል። (የመዝሙረ ዳዊት አንድምታ ትርጓሜ)» በማለት ደብረ መንክራቶች ሰፊ ማብራሪያ ሰጡ።

ሁለተኛ የውይይት ርእስ

ክርስቲያን ወደ ማን ይጸልይ? ወደ መናፍስት ሊጸልይ ይችላልን?

የደብረ ፋይዶች ማብራሪያ

«እግዚአብሔር ከሰው መካከል በተመረጡ ቅዱሳን በኩል ድኅነተ ነፍስን፥ በምድር ከችግር ነጻ መውጣትን ይሰጥ ዘንድ ወደ ቃል ኪዳን አቁሞላቸዋልና ቀደም ብሎ ያንቀላፉ ቅዱሳንን፥ በጸሎት ብንጠይቅ በሕይወተ ሥጋ እንደነበሩበት ጊዜ ሁሉ ጥያቄያችንን ተቀብለው ስለ እኛ በመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ያግልዱናል።

1) በያዕ. 5፥16 «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ጎይል ታደርጋለች» ስለሚል፤
2) በሉቃ. 20፥37-39 እግዚአብሔር እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅ አምላክ፥ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ያለው እነርሱ ለእግዚአብሔር ሕያዋን ሆነው በመገኘታቸው ነውና ምሉዕ በኩለሄ ሆነው ምድራውያን የሚናገሩትን እየሰሙ፥ የሚሠሩትን እያዩ የምልጃ ሥራን ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ስለሚገልጽ፤

ወዳንቀላፉት ቅዱሳን መጸለያችን ጥቅም አለው» በማለት አብራሩ።

የደብረ መንክራቶች መልስ

«ክርስቲያን ምን ጊዜም የጸሎት አድራሻው ሰማያዊ አባቱ እንዲሆን ጌታችን ጸሎትን ባስተማረበት ክፍል መመሪያ ሰጥቶበታል። (ማቴ. 6፥9-13፤ ሉቃ. 11፥1-4) በጌታችን የተሰጠው መመሪያ የሚይለወጥና የጸና ነው።

በዘመነ ብሉይ በተሰጡ የሕግ መጻሕፍትም፤ መናፍስትን የሚጠራ፥ የሙታንን ነፍሳት በድግምት የሚስብ በሕዝቡ መካከል እንዳይኖሽ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። (ዘሌ. 19፥31፤ 20፥6፤ ዘዳ. 18፥10-12) መናፍስት ሲባል መናፍስት ሆነው የተፈጠሩትን ሁሉ ማለቱ ሲሆን፥ (መዝ. 104፥4፤ ዕብ. 1፥14) የሙታን ነፍሳት ሲባልም አሁን በሕይወተ ሥጋ የሌሉ ከዓለመ ግዘፍ ወደ ዓለመ መንፈስ የተዛወሩ ሰዎች ነፍሳትን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።

የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ሕግ መሠረት ከእስትንፋሳቸው ይልቅ የሚቀርባቸውን እግዚአብሔርን በችግራቸው ሲጠሩት እርሱም ይመልስላቸው ነበር። (መዝ. 3፥4፤ 34፥17፤ 65፥2) እግዚአብሔርም ወደ እርሱ ለሚቀርበው ልመና ምላሽ የሚሰጠው በወደደው መንገድ ነው፤ በነቢያት በኩል መልስ ሊሰጥ ይችላል፤ (ዘጸ. 14፥10-16፤ ኢሳ. 38፥1-8)፤ በፊቱ ከሚያገለግሉ መላእክት አንዱን ልኮ ምላሽ ይሰጥ ይሆናል። (ሐዋ. 12፥4-11፤) ቀጥታ መልስም ሊሰጥ ይችላል። (ሐዋ. 16፥25-28) ዳሩ ግን ሰው ምን ጊዜም መጸለይ ያለበት ወደ አምላኩ ብቻ እንጂ ፍጡራንን ተስፋ በማድረግ ወደ መላእክት ወይም ወዳንቀላፉ ሰዎች ነፍሳት መሆን የለበትም። መዝ. 146፥3-5፤ ኤር. 17፥5-8።

እግዚአብሔር በዘመነ ብሉይ የተለየ ሕዝቤ ብሎ ለጠራው የአብርሃም ዘር ብሉይ ኪዳን በሚል ማጠቃለያ የተጠሩ የኪዳን

ተስፋዎች ሰጥቶ ነበር። (ዘሌ. 26፥42፤ ሉቃ. 1፥72-73) በዘመነ ሐዲስ ግን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሕዝብም ለሕዛብም ታላ ኪዳን አድርጎ ሰጠ። (ኢሳ. 42፥6-9፤ 49፥8) በእርሱም አዲስ ኪዳን ተመሠረተ። (ኤር. 31፥31፤ ሉቃ. 22፥20) ልጁን ታላ ኪዳን ያደረገበትን ምክንያት ሲገልጽም፥ ክብሩን ለሌላ መስጠት ስለማይፈቅድ መሆኑን ተናግሯል» (ኢሳ. 42፥8) በማለት አጠቃለሉ።

ሦስተኛ የውይይት ርእስ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ከየት እስከ የት?

በዚህ ርእስ በሁለቱም አጥቢያዎች መካከል የተፈጠሩትን የሐሳብ ልዩነቶች ይዘው የጻኘነት ጉባኤ እንዲመሥርጉና በቅዱሳት መጻሕፍት የተደገፈ ጻኘነት እንዲሰጥ ስለተጠየቅ ውሳኔዎ መሠኞች በዚህ ርእስ በየክፍሉላቸው የበተኗቸውን ፬፫፪ መረጃዎች ተረክበው በሁለቱም በኩል ተጨማሪ ማብራሪያ ሳያስፈልግ በዚሁ ውሳኔ ሊሰጡ ጻኞቹና ታዛቢዎቹ ተስማሙ።

ከሦስት ቀን በኋላም በሁሉም ነጥቦች ላይ ጻኞቹና ታዛቢዎቹ ውሳኔያቸውን ሊያስታውቁ ታላ ጉባተው ጠቅላላው ጉባኤ በጸሎት ስብሰባውን ዘጋ።

በቀነ ቀጠሮው ጻኞቹና ታዛቢዎቹ በስፍራቸው ተሰየሙ። አዳራሹ በተመልካች ተሞልቶ ነበር። ብዙ አዩነ ፍሬያሮናሮስም ከሌሎች ጳጳሳት ጋር በአዳራሹ ተገኝተው በብሥጠንታቸው ቢቃመራው ጸሎት የፅልቱ ስብሰባ ተከፈተ።

ጻኞቹና ታዛቢዎቹ ምርመራቸውን አጠናቀው ያቀረቡት የጻኘነት አስተያየት በንባብ እንዲሚሰማ አለታ ነቅዐ ጥበብ አስረድተው መድረኩን ለጻኞቹና ለታዛቢዎቹ አስረከቡ።

ሰብሳቢው ጻኛ ሊቀ ሊታውንት ዮሐንስ ቆመው፥ ከሁለቱም ወንድማማች ወገኖች የቀረበውን ሐሳብ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እኩል እየመሠኑ መገምገም ታላቁ ሥራቸው እንደነበረ ገልጸው፤ ጊዜ ቢወስድም ድካም ቢኖርበትም እግዚአብሔር ረድኤቸው ግጠታሊያውን ሠርተው ማቅረባቸውን አስረዱ። እንደ ጥያቄው ቅደም ተከተል የጻኞቹንና የታዛቢዎቹን የተናት ውሳኔ በሚከተለው ሁኔታ አነበቡት።

ሀ) መልአክ ምሉዕ በኩለሄ ወይስ ውሱን መንፈስ?

«በመሠረቱ መላእክትና የሰዎች ነፍሳት በተፈጥሮ ባሕርያቸው መናፍስት መሆናቸው በግልጽ የተነገረ ስለሆነ፥ ነጥቡ አያከራክርም። (ኢዮብ 12፥10፤ ዕብ. 1፥14) ጻሩ ግን የተፈጠሩ መናፍስት እንደመሆናቸው መጠን መንፈስ በሆነው በእግዚአብሔር እንጹር ሲታዩ የባሕርያቸው እየቅል መሆን በመንፈስነታቸው ደረጃ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር ፈጣሪ፥ አምላክ፥ ልዑል ባሕርይ፥ ምጡቀ ህላዌ፥ ምሉዕ በኩለሄ የሆነ፥ ዘላለማዊ መንፈስ ሲሆን፥ የሰዎች ነፍሳትና መላእክት ግን በዚህ ተቃራኒ ሁኔታ ላይ ናቸው። የጊዜ መነሻ እንዳላቸው ሁሉ፤ ፬ሥራና በቦታም የተወሰነ መኖሪያ አላቸው። አንዳንዶች መላእክት ተወስኖ የተሰጣቸውን መኖሪያ ስፍራና ሥራ አጥብቀው ባለመያዛቸው ወድቀዋል። ይህ ሁኔታቸው መንፈስ ከሆነው፥ መኖሪያ ሥራና ስፍራ (ዳን. 10፥20-21፤ 2ጴጥ. 2፥4፤ ይሁዳ 6) ወስኖ ከሰጣቸው ፈጣሪያቸው ጋር ለንጽጽርም ቢሆን አያቀርባቸውም» አሉ። በመቀጠልም፤

«በእግዚአብሔርም ፊት ያገለግላሉ መባላቸው መላእክትን የእግዚአብሔር ፊት የሚያየውን ሁሉ ለማየት፥ የእግዚአብሔር ጆሮ የሚሰማውን ሁሉ ለመስማት ያበቃቸዋል ወደሚል ነጥብ አያሸጋግራቸውም፤ ይኸውም፤

1) ቅዱስ ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ከሚያገለግሉት፥ ቍጥራቸው ሺህ ጊዜ ሺህና አልፍ አእላፋት ከሆኑት መላእክት መካከል አንዱ መልአክ ብሥራት ነው። ለነቢዩ ዳንኤል እንደተገለጸለት እነዚህ ሁሉ በፊቱ ቆመው ያገለግላሉና ዳን. 7፥10።

2) ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል። ኢዮብ 1፥6፤ 12፤ 2፥1-7፤ 1ነገ. 22፥21-22። ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ የወጣና የወደቀ መንፈስ ስለሆነ፤ በፈቃዱ አዳሪ ሆኗልና እንጻሻው ዘሞሪ ሆኗል፤ ኢዮብ 1፥7።

3) እንደ መላእክት ሁሉ፤ በምድር ያሉ ቅዱሳንም እግዚአብሔርን በፊቱ ቆመው እንደሚያገለግሉት ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል። መዝ. 34፥15፤ ሉቃ. 1፥74። ለምሳሌ ነቢዩ ኤልያስ በሰማርያ የአስራኤልን ንጉሥ አክዓብን ያነጋገር በነበረ ጊዜ፤ በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው። (1ነገ. 17፥1) በዚህ አባባል ኤልያስ ያነጋገረው አክዓብም በእግዚአብሔር ፊት እንደነበረ አይጠረጠርም፤ ኤልያስን ያይ የነበረ እግዚአብሔርም ኤልያስ ያነጋገረው የነበረውን ንጉሥን አክዓብን በፊቱ ቆሞ አይቶታል ግለት ነው።

ጻሩ ግን በእግዚአብሔር ፊት የቆሙት ኤልያስም ሆነ አክዓብ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት የሚታየውን ሁሉ ሊያዩ ይቅርና በዚያው በምድረ አስራኤል ውስጥ፤

- አብድዩ ምን እንጻደረገ እንኳን አላዩም። 1ነገ. 18፥13
- ለበዓል ያልሰገዱ 7000 እስራኤላውያን መኖራቸውን አላዩም። (1ነገ. 19፥18፤ ሮሜ 11፥2-4)

4) ጎጥአንም እንኳ በእግዚአብሔር ፊት ሆነው ይበድላሉ፤ ለመሰወር ቢሞክሩም ከእግዚአብሔር እይታ ሊያመልጡ አይችሉም። (ዘፍ. 20፥6፤ 39፥9፤ 2ሳሙ. 12፥9፤ መዝ. 34፥16፤ 90፥8፤ ሉቃ. 15፥18) ሲበድሉም በእግዚአብሔር ፊት መሆናቸው አግዚአብሔር ያየውን ሁሉ ለማየት አያበቃቸውም።

5) የአሕዛብ ድምር በፊቱ ወደ ገንቦ እንደሚገባ ጠብታ ነው፤ ሁሉም ግን በድምርም በዝርዝርም (በነጠላም) በእግዚአብሔር ይታያሉ። (ኢዮብ 26፥6፤ ኢሳ. 40፥15፤ ኤር. 23፥24)

6) ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በዓለመ ግዘፍም ሆነ በዓለመ መንፈስ የሚኖሩ እያንዳንዱ ሕያውም ሆነ ኢሕያው ፍጥረት በእግዚአብሔር ፊት ነው። የሁሉም እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር ዓይን ይታያል።

- በዓለመ ግዘፍ ያለ እያንዳንዱ ጻድቅም ሆነ ጎጥአ ምሉዕ በኩለሄ በሆነው በእግዚአብሔር ዓይን ከነሙሉ ሥራው በመታየቱ እርሱ ከሚኖርበት ዓለም ውጪ ያለውን እግዚአብሔር ያየውን እንዲያይ ያወቀውን እንዲያውቅ አያበቃውም። በሚኖርበት ዓለም ውስጥም ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር ያየውን ሁሉ እንዲያይ፥ እንዲያውቅ የሚያበቃችሎታ የለውም።
- ቅዱሳን እንዳንድ ጊዜ በዓይነ ሥጋ ሊታይ የማይችለውን ነገር የሚያዩት ለዚያው ውሱን ጊዜ ለልዩ መገለጥ በሚሰጣቸው ጸጋ ነው። 2ነገ. 6፥8-17።

7) ጻድቃንም ሆኑ ጎጥአን በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚኖሩበትን ዓለመ ግዘፍ ለቀው ወደ ዓለመ መንፈስ ሲዛወሩ ብቻ ወደዚያ መሔድና በዚያ መኖር ይችላሉ።

- በገቡበት ዓለመ መንፈስም ቢሆን እግዚአብሔር ባሰቀመጣቸው ስፍራ ይኖራሉ፥ ለመንፈሳቸው በሚቻለው መጠን ህላዌ ያለውን ያያሉ፥ ያውቃሉ እንጂ በዓለመ መንፈስ የሚካሔደውን ሁሉ የማወቅ ዕድል አይኖራቸውም፤ ሉቃ 16፥22-23።

ውነበ ሕሑቲ መዝገብ ይትወደይ ሥርናይ ዘአልቦ ክርዳድ፤ ህየ ይሰየማ መህየ ይትዐቀባ ነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን እስከ እመ ይፈድዮ ለኩሉ በክመ ምግባሩ፤ እንክርዳድ ያልተቀላቀለበት ስንዴን የመሰሉ ጻድቃን በአንድ ስፍራ በገነት እንዲኖሩ ይደረጋሉ፤ ለሁሉም ለእያንዳንዱ እንደየሥራው እስኪከፍለው ድረስም በዚያ ይኖራሉ። ይጠበቃሉም። ቅዳሴ 300።

- ወደ ዓለመ መንፈስ የተዛወሩት ነፍሳት በተውት ዓለመ ግዘፍ ከዚያ በኋላ ምን እየተደረገ እንዳለና እንደሚኖርም አያዩም፤ አያውቁምም። ኢዮብ 14፥5-12፤ 21፥21፤ መክ. 9፥5-6

8) በዓለመ መንፈስ የሚኖሩ መላእክትም፤

- በፊቱ ቆመው የሚያገለግሉትን. እግዚአብሔርንም ቢሆን በምልዐቱ አያዩትም። «እይታው የሚሰግዱለት አይደለም፤ ለሥልጣኑ ይሰግዳሉ፤ ለጌትነቱም ይገዛሉ እንጂ» ቅዳሴ 300።
- በሚላኩበት ጊዜም አንዱን ስፍራ ለቀው ወደ ሌላው ስፍራ ይሄዳሉ፤ የነበሩበትን ስፍራም ለቀው ከሔዱ በኋላ በተላኩበት ስፍራ ይገኛሉ፤ ተልእኳቸውን ጨርሰው ካልተመለሱ በቀር በለቀቁት ስፍራ አይገኙም። ኢሳ. 6፥6፤ ሐዋ. 12፥7-10።

«ወይሰሩ ውስተ ትርብዕተ ዓለም ለገቢረ ኩሉ ፈቃዱ»

- ፈቃዱን ለመፈጸም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይበራሉ። ቅዳሴ 300።
- ዮሐንስ አፈወርቅም በድርሳኑ ወደ ዕብራውያን የተጻፈውን መልእክት 1፥14 ሲተረጉም፥ የወልድን መላክ ከእነርሱ መላክ ጋር አነጻጽሮ እንዲህ አለ። «ወአኮ ዘፈለሰሰበ ተፈነወ እመካን ውስተ መካን ከመ መላእክት፤ እስመ ይትገዮኡ እመካኖሙ ሶበ ይትፈነው። ወልድ፤ በተላከ ጊዜ እንደ መላእክት ቦታውን ለቆ የሄደ አይደለም፤ መላእክት ሲላኩ የነበሩበትን ቦታ ለቀው ይሄዳሉ፤ ወደተላኩበትም ስፍራ ይደርሳሉ።»
- መላእክት በጉዟቸውም ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። ዳን. 10፥12-13፤ 20፤ 21።

9) «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል፥ ይከትማል» (መዝ. 34፥7) የተባለው አገላለጽ ሠራዊቱን በአለቃው አጠቃሎ ለመናገር መሆኑ ግልጽ ነው።

- ለብዙ ቅዱሳን የጥበቃ አገልግሎት እንዲፈጽሙ ብዙ መላእክት እንደሚላኩ በሌላ ስፍራ ተገልጿልና። ማቴ. 18፥10፤ ዕብ. 1፥14።
- ለአንድ ሰውም ቢሆን ብዙ መላእክት ይመደባሉ። ዘፍ. 32፥1፤ መዝ. 91፥11።

10) የቅዱሳንን የምልጃ ጸሎት በሚመለከት በመልእክተ ያዕቆብ የተጠቀሰው ቃል ዐውዱ ከሚጀምርበት ንባብ ከቁጥር 13 ጀምሮ እስከ 20 ያለው ተነቦ ለግንዛቤ መወሰድ ይኖርበታል።

10.1) ከእናንተ መካራን የሚቀበል ይጸልይ፤ የታመመም ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች (ቀሳውስት) ይጸልዩለት። የምልጃውን ጸሎት ጌታ ስለሚቀበለው፥ ሕመምተኛውን ከደዌው ይፈውሰዋል፤ ለደዌው ምክንያት የሆነውንም ኃጢአት ይቅር ይለዋል። ቁ. 13፥14።

10.2) ስለዚህ የኃጢአትን ስርየት ለማግኘት ከበሽታም ለመፈወስ አንዱ ለሌላው ይጸልይለት ዘንድ እርስ በርስ ኃጢአትን መናዘዝ ያስፈልጋል። ቁ. 15-16።

10.3 በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚቀርብ የጻድቅ ሰው ጸሎት ያለ ጥርጥር በጌታ ዘንድ ቱቀባይነትን እንደሚያገኝ የኤልያስን ታሪክ በማስረጃነት ያቀርባል። ቁ. 17-18።

10.4) እንደዚህ ከሆነ፥ በኃጢአት የወደቀ ክርስቲያን ወደ ባለ ደረጃ ከመድረሱ በፊት በጸሎት በተደገፈ ምክር ሌላው ክርስቲያን ወንድም ቢመልሰው ወደ ሞት ከመወሰድ እንዲድን ረዳው ማለት ነው። ቁ. 19-20።

እንግዲህ በዐውደ ንባቡ ውስጥ ያለው ሐሳብ ኤልያስ በሕይወተ ሥጋ ያደረገውን ጠቅሶ በማስረጃነት በማቅረብ «አንዱ ለሌላው ይጸልይለት» የሚል ስለሆነ፥ በሕይወተ ሥጋ ያሉ ክርስቲያኖች በጸሎት የሚረዳዱበት መመሪያ እንደሆነ በቃሉ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ይታያል። አገልግሎታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከዓለመ ግዘፍ ወደ ዓለመ መንፈስ ወደተዛወሩት ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ያሉ ክርስቲያኖች ሊጸልዩ ይገባል፤ ወይም በዓለመ መንፈስ ያሉ ነፍሳት በዓለመ ግዘፍ ካሉ ሰዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ የሚል ሐሳብ በዐውደ ንባቡ ውስጥ የለበትም።

10.5) ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ በማኅበርም ሆነ በግል በችግር ውስጥ ለወደቀ ክርስቲያን ይጸልዩ እንደ ነበረ ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል።

- ሄሮድስ ቅዱስ ጴጥሮስን በወህኒ አሳስሮት በነበረ ጊዜ ማርቆስ በተባለው በዮሐንስ እናት ቤት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ጸለየች። ጸሎቷም በጌታ ዘንድ ተቀባይነትን አገኘና ጴጥሮስ ከወህኒ ወጣ። የሐዋ 12፥1-17።
- ቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎቱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ እንዲጸልዩለት በመልእክቱ በሕይወተ ሥጋ የነበሩትን ቅዱሳን አሳሰበ። ሮሜ 15፥31-32፤ 2ቆሮ. 1፥10-11፤ ኤፌ. 6፥18-20፤ ቈላ. 4፥2-4፤ 1ተሰ. 5፥25፤ 2ተሰ 3፥1-2፤ ፊል. 22።
- እርሱም በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ጊዜ በሕይወተ ሥጋ ለነበሩት ቅዱሳን ይጸልይ ነበረ። ኤፌ. 1፥15-17፤ 3፥14-21፤ ፊል. 1፥3-5፤ ቈላ. 1፥3-5፤ 1ተሰ. 1፥2-3፤ ዕብ. 13፥ 18-19።

ከዚህ የምንወስደው ማጠቃለያ ሐሳብ ቡጥንታዊቷ (የሐዋርያት) ቤተ ክርስቲያን ልምምድ በሕይወተ ሥጋ የነበሩ ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ለነበሩ ቅዱሳን ይማልዱ እንደነበረ የሚገልጽ ነው። ዳሩ ግን በሕይወተ ሥጋ የነበሩት ቅዱሳን ቀደም ሲል ሩጫቸውን ጨርሰው ወዳንቀላፉት ማለት ከዓለመ ግዘፍ ወደ ዓለመ መንፈስ ወደተዛወሩት ቅዱሳን ይማልዱላቸው ዘንድ አለመጸለያቸውን፤ ወይም በሕይወተ ሥጋ ያሉት ላንቀላፉት ሰዎች አለመማለዳቸውን ልንገነዘብ ችለናል።» የሚለው የዳኞቹና የታዛቢዎቹ ማብራሪያ ከተነበበ በኋላ ቀጥሎ ወዳለው ንዑስ ርእስ ተሻገረ።

10.6) «ቃል ኪዳንን በሚመለከት :-

በዘመነ ሐዲስ በወልድ በኩል ከቆመው ኪዳን በቀር ሌላ ኪዳን ተሰጥቷልን?

አሁን ካለንበትና ከተሸፈንበት ከሐዲስ ኪዳን በፊት በሥራ ላይ የነበረው ብሉይ ኪዳን መሆኑ የታወቀ ነው። የዕብራውያን መልእክት እንዳብራራው ያ ብሉይ ኪዳን በእነድ[illegible] ምክክኖኛ ዘመኑ የተሰጠ አልነበረም፤ የተሰጠበትም ሥነ ሥርዓት አንድ ብቻ አልነበረም፤ በማእዘ· ሐዲስ ኪዳን በብዙኅ ነገር ወበብዙኅ መክፈልት፤ በኤን አይ ቪ የእንግሊዝኛ ትርጉም at many times and in various ways በብዙ· ጊዜያት፥ በተለያዩ መንገዶች በየዘመናቱ በተነሡ ብዙ አገልጋዮች በኩል ከእግዚአብሔር የተነገሩ ቃላት ተጠራቅመው የተጋጠሙ ብዙ ተስፋዎችን፥ ትእዛዞችን፥ ምሳሌዎችን፥ ትንቢቶችን ... አዋሕዶ የያዘ የብሉይ ኪዳንን ጥራዝ አስገኘ።

ስለ ብሉይ ኪዳን አመጣጥ ጸሐፊው በዚህ ሁኔታ ከተናገረ በኋላ ወደ ሐዲስ ኪዳን ሲመጣ «በመጨረሻው ዘመን በአንድ ልጁ ተናገረን» ይላል። (ዕብ. 1፥1-3) ከልጁ በኋላ የተነሡና የሚነሡ አገልጋዮች ሁሉ እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን ያንኑ በመጨረሻ ዘመን በልጁ የተናገረውን ለማዳረስ፥ ለመተርጐም፥ ለማብራራት እንጂ «አዲስ ወንጌል፥ ወይም ሌላ ቃል ኪዳን[1] ይዘው እንዳልመጡ ወይም እንደማይመጡ ግልጽ ነው።

. የሐዲሱ ቃል ኪዳን ዋና መልእክት በሰው የተበደለው እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ ካማ ሆኖ መሰጠት ምክንያት ከሰው ጋር መታረቁንና ዕርቁም ዘልጁ ደም የጸና መሆኑን የሚያረጋግጥ ኪዳን ነው። ሉቃ. 22፥20፤ ሮሜ 5፥6-11፤ 1ቆሮ. 11፥25።

በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ ልዩ ልዩ አገልጋዮችን በዘመነ ሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ሲልክ «በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ታርቁዋለሁና ሰው ሁሉ የዕርቁን ቃል እንዲቀበል ይህን የምሥራች ቃል ንገሩ» በሚል ትእዛዝ ነው። 2ቆሮ. 5፥18-20።

የብሉይ ኪዳንን ነቢያት ብዛትና የልጁን አንድዩ መሆን ወንጌል በምሳሌ ሲገልጽ (ማቴ. 21፥33-46፤ ማር. 12፥1-12) የወይኑ አትክልት ባለቤት በገቡት የኮንትራት ውል መሠረት ገበሬዎች ለባለቤቱ የሚገባውን ሰብል እንዲሰጡ ሦስት ጊዜ የተለያዩ አገልጋዮችን ላከ፤ ገበሬዎች ግን ጥያቄውን ለመፈጸም ፈቃደኞች አለመሆናቸውን፥ ወደ እነርሱ የተላኩትን አገልጋዮች በመግደል ገለጹ። በመጨረሻ የሚወደው አንድ ልጅ ገና ነበረውና እርሱን ላከባቸው። አንድያ ልጁንም ለመቀበልና ለማስተናገድ ፈቃደኛ ያልሆኑት ገበሬዎች ልጁን ከገደሉት በኋላ የወይኑ አትክልት ባለቤት ወደ ፍርድ ሄደ እንጂ ከልጁ በኋላ ሌላ መልእክተኛ አልላከባቸውም።

የእይሁድ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት ይህን ታሪክ ሲሰሙ ምሳሌውን ስለ እነርሱ እንደተናገረ ዐውቀው ነበር፤ ሆኖም በዐመፃቸው ገበሬዎች ላይ ሊወስድ ስለሚገባው ርምጃ ጌታ በጠየቃቸው ጊዜ «እንዲ፤ ሌላ አንድ ፅድል ሊሰጣቸው ይገባል!» ይሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ስላልፈቀደላቸው ዐመፃኞቹ ገበሬዎች የመጨረሻ ቅጣት ይገባቸዋል ሲሉ በራሳቸው ላይ ፈረዱ።

በልጁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በዘናው ሐዲስ ኪዳን ያልተሸፈኑ ሰዎች ፅድል የመጨረሻ ፍርድ እንጂ ሌላ የሚጠብቃቸው ኪዳን የለም፤ ይህን ሐዲስ ኪዳንን የሚያስረጅ ሌላ ምስተኛ ኪዳን ከቶ የለም፤ እርሱ የመጨረሻ ነውና። ዕብ. 1፥2፤ 8፥7-13፤ 10፥9-18፤ 1ጴጥ. 1፥20-21። ስለሆነም፤

1ኛ. ዛሬ የምንመራበት ሐዲስ ኪዳን እንደሚመጣ ራሱን በራሱ ያስረጀው ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር «ሌላ» ግለት ዐዲስ ኪዳን ይሰጣችኋል ብሎ አስቀድሞ በትንቢት የሰውን ልብ አዘጋጅቶ መቼየቱን፤ ኤር. 31፥31-33፤ ዕብ. 8፥6-13።

2ኛ. ዐዲሱ ኪዳን ግን ሌላ ኪዳን እግዚአብሔር ይሰጣችኋል አለግለቱን፥ እንዲያውም ለዘመን መጨረሻ የተመደበ የመጨረሻ እንደሆነ መግለጹን፤ ዕብ. 1፥1-2፤ 1ጴጥ. 1፥18-21፤

3ኛ. በብሉይ ኪዳን ያልተፈጸሙ ውሉ በሐዲስ ኪዳን የተፈጸሙና የሚተበለውን ሰው ብቻ የሚመለት ሲሆን፥ በዐዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ያልፈጸሙት፥ በዕሩቅ ብእሲ ወይም በፍጡር እንዲፈጸም ለት የሚጠብቀው አለመኖሩን፤

4ኛ. በክርስቶስ ጸጋ የተሰበከውና ዐዲሱ ኪዳን የጸናበት መንገል፤

- የእግዚአብሔር መንገል ነው፤ ሮሜ 1፥1-2፤ 15፥16፤
- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገር የልጁ መንገል ነው፤ ሮሜ 1፥3-4፤ 1ቆሮ. 9፥12፤
- የሰውን ዘር ሁሉ የሚያድነው የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጠበት መንገል ነው፤ ሮሜ 1፥16፤ 1ቆሮ. 15፥1፤
- የእግዚአብሔርና የሰው ዘር ዕርቅ የታወጀበት የሰላም መንገል ነው፤ ኤፌ. 6፥15፤
- ምን ጊዜም የማይለወጥ የዘላለም መንገል ነው። ማር. 16፥8፤ ራእ. 14፥6፤ እንዲህ በመሆኑም፥ ሐዋርያም ሆነ መልእክተ የእኛን ኀጢአት ለማስተስረይ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም የጸናውን፥ ዐዲስ ኪዳን (ማቴ. 26፥27-28፤ ሉቃ. 22፥20) ሆኖ የታወጀውን መንገል ሌላ ኪዳን ይ። በሚመጣ መንገል መለወጥ መርገም መሆኑን «ዳኛውና ታዛቢዎች በማስራት ካሰረዱ በኋላ ወደሚቀጥለው 3ኛ የመወያያ ርእስ ተሻገሩ። ከሁለቱ ወገኖች መግለጫም በመነሣት በትዳሳት መጻሕፍት ምስክርነት የተደገፈውን ውጤት እንደሚከተለው አነበቡ።

3) የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ከየት እስከ የት?

«ክህነት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በመካከለኛነት መከናወን ካለባቸው አገልግሎቶች አንዱ ነው። ስለሆነም በዚህ ርእስ ላይ ለተከራከሩት ለሁለቱ አጥቢያ የዕለተ እሑድ ተማሪዎችና የክርክሩን ውጤት ለሚጠባበቁ ምእመናን ሐሳቡ ይበልጥ ግልጥ እንዲሆንላቸው መካከለኞች የተመደቡባቸውን ሦስቱን ዋና ዋና አገልግሎቶች በዚህ ስፍራ ልንመረምራቸው እንደሚገባ እናምናለን።» አሉና ሲያብራሩ፥

1. የመካከለኛ ሥራዎች አስፈላጊነት

በሰው ኀጢአት ምክንያት በተበደለው በእግዚአብሔርና በደል ባደረሰው የሰው ዘር መካከል ጠብ እንደተፈጠረና መለያየት እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል። ኢሳ. 59፥1-3። በእግዚአብሔርና በሰው መካከልም ዕርቅ ይፈጠርና ግንኙነት ይታደስ ዘንድ የመካከለኞች ሥራ መደብ ይፈጠር ዘንድ አስፈለገ።

2. የብሉይ ኪዳን መካከለኞች

- ነቢያት ለእርቅ ተስታኞችና አቀራራቢዎች
- ካህናት አስታራቂዎች
- ነገሥታት የዕርቁን ቃል ኪዳን ሕዝብ አስተዳዳሪዎች ሆኑ

3. የብሉይ ኪዳን መካከለኞች ባሕርይ

እግዚአብሔርንና ሰውን የማቀራረብ፥ የመሸምገልና የማስታረቅ አገልግሎት በዘመነ ብሉይ ለሁለቱ እኩል ዝምድና ወይም እኩል የባሕርይ ውክልና በሌላቸው፥ በአበው አነጋገር ዕሩቅ ብእሲ በሚባሉ መካከለኞች ብቻ የማቀራረቡ፥ የማስታረቁና የማገናኘቱ ሥራ ሲሠራ ኖረ። እንደ እውነቱ ከሆነ መካከለኛ ተብሎ ከተሾመ አንዱን ወገን ብቻ የሚወክል መሆን አልነበረበትም፤ (ገላ. 3፥20 የ1980 ትርጉም) ጸሩ ግን ብሉይ ኪዳን አማናዊ ያልሆነ የጥላ (የምሳሌ) አገልግሎት ነበረና ከመካከለኞቹም ሆነ ከአገልግሎታቸው ፍጹምነት አልተገኘም። ዕብ. 8፥5፤ 10፥1።

4. የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ

ይህ ጊዜ የጥላና የምሳሌ አገልግሎት ማከናወኛ ወቅት ሳይሆን አማናዊና አካላዊ አገልግሎት ሊከናወንበት የሚገባ ዘመን ስለሆነ ከመካከለኛውም ሆነ ከአገልግሎቱ ፍጹምነትና ብታት ይጠበቅበት ነበረ። ስለሆነም፤

- እግዚአብሔርም ሰውም መሆኑ የተረጋገጠለት ለእግዚአብሔርም ለሰውም ዝምድናው እኩል የሆነ መካከለኛ ለአገልግሎቱ ይመደብ ዘንድ ተገባ።

- ፍጹም እግዚአብሔርና ፍጹም ሰው ሆኖ በተዋሕዶ በአንድ እኔ ነኝ ባይነት (አካል) የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛ ሆኖ ተገኘ። 1ጢሞ. 2፥5፤ ዕብ. 8፥6፤ 12፥24።

«ወመጽአ ክርስቶስ ዐራቂ ማእከለ እግዚአብሔር ወእጓለ እመሕያው፤ ወዐረቆ ለክልኤሆሙ፤ መለኮትሰ ዘአቡሁ ወዚአሁ፤ ወትሰብእትሰ ዘዚአነ፤ ወከነ ዐራቂ ማእከለ ክልኤሆሙ።» ወአሰረ ክልኤተ ህላዊያተ በበይናቲሆሙ በተዋሕዶ። ወከመዝ አማሰነ ቦቱ ጽልዐ። ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አስታራቂ ሆኖ መጣና ሁለቱንም አስታረቃቸው። መለኮት የአባቱና የራሱ ባሕርይ ነው። ትስብእትም (ሰብእነትም) የእኛ ባሕርይ ነው። ስለሆነም በሁለቱ መካከል አስታራቂ ሆኖ ለየራሳቸው የነበሩትን ሁለት ባሕርያት (መለኮትና ትስብእትን) በተዋሕዶ በአንድ እኔ ነኝ ባይነት እናናንና በዚው ተዋሕዶው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን ጥል አስወገደ።» ዮሐንስ አፈወርቅ፤ ሃ.አ.

5. የመካከለኞች አገልግሎቶች፤

5.1 ነቢይ፤ ቀስታኝና አቀራራቢ

ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለሰው ያስተላልፋል። ዘዳ. 5፥5፤ ኤር. 1፥4-10።

በዘመነ ብሉይ በብዙ ነቢያት ሲካሄድ የኖረው አገልግሎት በአዲስ ኪዳን በእንዱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ተያዘ። ዕብ. 1፥1-3።

ጌታ ራሱ ነቢይ እንደሆነ በቃሉ አረጋግጧል። ማቴ. 13፥57፤ ሉቃ. 4፥24፤ 13፥33፤ ዮሐ. 4፥44።

5.2 ሊቀ ካህናት፥ አስታራቂ ዕብ. 5፥1-4።

ከሰው መካከል ይመረጣል፤

ስለ ሰው ይሾማል፤

የእግዚአብሔር በሆነው ነገር ላይ ይሾማል፤

በእግዚአብሔር ይሾማል፤

መሥዋዕትንና ቍርባንን ሊያቀርብ ይሾማል

ጌታ ኢየሱስ ይህን የክህነት መስፈርት አሟልቷል። ዕብ. 1፥5-6፤ 9፥11-14።

5.3 ንጉሥ (እረኛ) ዘኍ. 27፥17፤ 2ሳሙ. 7፥8፤ ሕዝ. 34፥5-10።

የቃል ኪዳኑን ሕዝብ ይጠብቃል፤ ይመግባል፤ ይገዛል፥ ያስተዳድራል።

ይህም ሥራ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጥቷል። ኢሳ. 9፥6-7፤ ኤር. 23፥5-6፤ ዮሐ. 10፥11-15፤ 27-30።

6. የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ክህነቶች ልዩነቶች

የብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት (አሮንና ልጆቹ)	የመል ጥቅሶች	የሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ)
6.1 ከነገደ ሌዊ፥ ከዚያውም ከቤተ አፎን በመወለዳቸው ይሾማሉ	ዘጸ. 28፥1፤ 29፥4-7፤ ዕብ. 7፥11-17	የተወለደው ከነገደ ይሁዳ ሆኖ ሳለ፥ በማያልፍ ሕይወት ጎይል ተሾመ
6.2 የተሾሙበት ሕግ ደካሞችን ጎያላንና ፍጹማን ለማድረግ አልረዳም	ዕብ. 7፥18-19፤ ሮሜ 8፥2-4፤ ፊል. 4፥13	በሥጋ ድካም ምክንያት ሕግ ሊያደርግ ያልቻለውን አደረገ
6.3 አገልግሎታቸው ጊዜያዊ ስለነበረና አርኪ ስላልሆነ እግዚአብሔር በመሐላ አልሾማቸውም።	መዝ. 110፥3-4፤ ዕብ. 7፥20-22	ኢየሱስ ካህን በሚሆንበት ዕቅዱ ላይ እንኳ እግዚአብሔር አስቀድሞ ማለ።
6.4 ለዘላለም ስለማይኖሩ፥ ከሞቱም በኋላ የማስታረቅ አገልግሎታቸውን መቀጠል ስለማይችሉ፥ በሕይወተ ሥጋ በሚገኝ ሌላ ካህን ይለወጡ ነበር።	ዕብ. 7፥23-25፤ ሮሜ 8፥34	ሞትንና ሲያልን አሸንፎ ስለተነሣ ለዘላለም ይኖራልና ክህነቱም አይለወጥም፤ ዘለዓለማዊ ነው።
6.5 እነርሱ እንደ ማንኛውም ሰው ኀጢአተኛ ባሕርይን ወርሰዋል፤ በድለዋልም	ምሳ. 20፥9፤ ሮሜ 3፥23፤ ዕብ. 7፥26	እርሱ ግን ቅዱስ፥ ያለ ተንኮል፥ ያለ ነውር፥ ከኀጢአተኞችም የተለየ ነው።
6.6 እነርሱ ሰው ያመጣውን መሥዋዕት ከማቅረባቸው በፊት ስለራሳቸው ኀጢአት እንዲሠው ይገደዱ ነበር	ዘሌ. 16፥6 ዕብ. 7፥27	እርሱ ግን ቅዱስ ስለሆነ ስለራሱ መሥዋዕት ማቅረብ አላስፈለገውም
6.7 ስለ ራሳቸውም ስለ ሌላውም የሚያቀርቡት መሥዋዕት አይቋረጥም ነበር። በየጊዜው በየዓመቱና በበደሉ ቁጥር ማቅረብ ነበረባቸው።	ዕብ. 5፥3፤ 7፥27	ለአንድ ጊዜ ብቻ አንድን መሥዋዕት አቀረበ
6.8 ንስሐ የሚገባው ኀጢአተኛ የሚሠዋ እንስሳ እንዲያመጣላቸው ያስፈልጋቸው ነበር	ዕብ. 7፥27፤ 10፥1-7፤ 14፥1	እርሱ ግን ራሱን መሥዋዕትና ቊርባን አድርጎ አቀረበ
6.9 የሰማያዊት መቅደስ ምሳሌ በሆኑት ምድራዊት መቅደስ ሲያገለግሉ እየኖሩ ሞቱ	ዕብ. 7፥23፤ 8፥5፤ 9፥12	የእግዚአብሔር ዙፋን በሚገኝባት፥ በሰማያዊቷና በአማናዊቷ ቅድስተ ቅዱሳን አገለገለ
6.10 የብዙ መቶ ካህናት፥ የ1500 ዓመት አገልግሎት፥ የሰማያዊት ቅ. ቅዱሳን ምሳሌ የነበረችውን ምድራዊቷን ቅድስተ ቅዱሳንንም ቢሆን እንኳ ለምእመናን ክፍት ማድረግ አልቻለም	ዕብ. 9፥1-10፤ 23-24፤ ማቴ. 27፥50-51፤ ዕብ. 9፥6-10፤ 10፥19-22፤	በጌታ በኢየሱስ የክህነት አገልግሎት በቀረበው መሥዋዕት ምክንያት ምድራዊቷም፥ ሰማያዊቷም (ምሳሌይቱም፥ አማናይቱም) ቅድስተ ቅዱሳኖች ለዘላለም ለምእመናን ክፍት ሆኑ
6.11 ምንም ምድራዊት ቅድስተ ቅዱሳን ብትሆን የየዓመቱን አገልግሎት ሲጨርሱ፥ በሌላ ጊዜ ለአገልግሎት እስኪመለሱ ድረስ ከመጋረጃው ወጥተው ይሄዱ ነበር እንጂ በዚያ እንዲቀመጡ አልተፈቀደላቸውም ነበር።	ዕብ. 8፥1-2፤ 10፥11-12	ጌታ ኢየሱስ በአገልግሎቱ ፍጻሜ ለምእመናን ክፍት ባደረጋት በሰማያዊት ቅድስተ ቅዱሳን በአብ ቀኝ ተቀመጠ።

7. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ ተቀምጦ ምን እየሠራ ነው? የሚለውን ጥያቄ ቅዱሱ መጽሐፍ ይመልሳል። አበውም አስተጋብተውታል።

7.1 በነቢይነቱ፤ ቤተ ክርስቲያንን በትምህርትና በጸጋ ስጦታ ያሳድጋል። ኤፌ. 4፥10-16

7.2 በሊቀ ካህንነቱ፤ በአብ ቀኝ ተቀምጦ

- ዐዲስ ምእመናን በመሥዋዕትነቱ ታምነው ወደ እርሱ በእምነት ሲመጡ፥ ስርየትን በመስጠት ያድናቸዋል። ዕብ. 7፥24-25።

- ነባር ምእመናን እግረ ልቡናቸውን በንስሐ ሲሰጡ ያጥባቸዋል፤ ያነጻቸዋል። ዮሐ. 13፥6-11፤ 1ዮሐ. 2፥1-2

7.3 በንጉሥነቱ ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድራል። ኤር. 23፥5-6፤ ኤፌ. 5፥24-30፤ ሮሜ 12፥27-28

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት «ስለ እኛ» የታየበትንና እሁን «ለእኛ» የሚታይበትን ውኔታ በሚመለከት የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ በምዕራፍ 9፥24-28 ሁለት ሐሳቦችን አቅርቧል።

8.1 ስለ ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት መታየት፤ የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ በስርየት ቀን ገብቶ የሕዝቡን ሁሉ ኀጢአት የሚያስወግድ መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። ሥነ ሥርዓቱ በዘሌ. 16፥2-34፤ 23፥26-32፤ ዘኍ. 29፥7-11፤ በዝርዝር ተጽፏል። በዚህ በተባለው ዕለት ሊቀ ካህናቱ የሕዝቡን ኀጢአት ሊናዘዝና ስርየት ሊቀበል ለኀጢአት ማስተስረያ የቀረበውን እንስሳ ደም ከመሠውያው ቀድቶ፥ ሕዝቡን ወክሎ፥ መገናኛውን ድንኳን ዐልፎ ቅድስቱን ሰንጥቆ፥ ዝጉንም የቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ ገልጦ ወደ ውስጥ ይገባ ነበር። በዚያ ሕዝቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት ስለሚታይ ሌላ ሰው በድንኳኑ ውስጥ እንዲገኝ አይፈቀድም ነበር፤ ሕዝቡ ግን በወዶዎ ምሕረቱ ሆኖ የሊቀ ካህናቱን በሰላም መመለስ ይጠባበቅ ነበር። ዘሌ. 16፥17።

8.2 ለሕዝብ መታየት

ሊቀ ካህናቱ የወሰደውን ደም በስርየት መክደኛው ላይ ከረጨና ካስተስረየ በኋላ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ተቀብሎ በሰላም ካሰናበተው ከቅድስተ ቅዱሳን ወደ ቅድስት ተመልሶ፥ የመገናኛውንም ድንኳን ዐልፎ በዐውደ ምሕረቱ አደባባይ ለሚጠባበቁት ሕዝብ ይታይላቸዋል፤ የምሥራች እንደ ማለት ነው። ከዚያም በቃለ ቡራኬ ያሰናብታቸዋል። ዘኍ. 6፥22-27

ዘካርያስ የስርየትን ቀን ሥርዓት ሊፈጽም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ በመዘግየቱ በዐውደ ምሕረት ሆነው መመለሱን ሲጠባበቁ የነበሩትን ሕዝብ አሳስቢቸው እንደነበረ ይታወሳል። ሉቃ. 1፥21

8.3 በዚህ ታሪካዊ መግለጫ አንጻር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፤

ኀጢአታችንን ተሸክሞ ስለ እኛ መከራ ሊቀበልና ሊሞት፥ በዚህም ውኔታ የኀጢአታችንን ዕዳ ሊከፍልና በደሙ ሊያስተሰርይልን በእግዚአብሔር ፊት አንድ ጊዜ ታየልን፤ እኛን ሆኖ ስለ እኛ ታየ። ኢሳ. 53፥4-6፤ ዕብ. 9፥24-26

- ኀጢአታችንን ተሸክሞ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ ሊታይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንደገባ እያሰብን፥ የኃጢአትን ስርየት የምሥራች ሊለን እንደሚገልጥልን አምነን ለምንጠባበቀው፥ ስርየትን በሚያበሥር መገለጥ ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኀጢአት ይታይልናል። ኢሳ. 53፥10፤ ዮሐ. 20፥19-23፤ ዕብ. 9፥24፤ 28። ይህ መገለጥ ዛሬ ዕለት፥ በዕለት እርሱን በመንፈስ የምናይበት፥ ስርየት የማግኘታችንን የምሥራች የምናረጋግጥበት ዕይታ ሲሆን በዳግም ምጽአቱ ግን ፊት ለፊት እናየዋለን።

9. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደጠበቃና እንደ ሊቀ ካህናት መታየቱ፤

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ዐረገ፥ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ። እዚያ ሆኖ በዘላለማዊ ሊቀ ካህናትነቱ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በፈጸመው የማዳን ሥራው ያመኑበትን ሁሉ ያድናቸዋል፤ ያመኑበት ሁሉ በርሱ መካከለኛነት የተገኘውን ዕርቅ የተቀበሉ ሆነዋልና፥ በመካከለኛነቱ፥ «ፍናት ለኀበ አቡሁ፥ አንቀጽ ዘመንገለ ወላዲሁ ፤- ወደ አባቱ የሚያደርስ መንገድና የሚያስገባ በር ሆኖ፤» ከአባቱ ጋር ሲያገናኛቸው ይኖራል። ዮሐ. 14፥6፤ ዕብ. 5፥10፤ 7፥24-25።

- የየዕለቱን ኑዛዜያቸውን እየተቀበለ ኀጢአታቸውን ይቅር የሚል የታመነ ሊቀ ካህናት ነው። ዕብ. 2፥17።

- በአብም ቀኝ ተቀምጦ በመገኘቱ የእርሱ በሆኑት ላይ ስለሚቀርብ ክስ መልስ ሰጪ፥ ጠበቃ ሆኖልናል፤ ጥብቅና ቆሞልናል። 1ዮሐ. 2፥1።

- ጥብቅና በመቆም ሥራ መታወቁም ስለ እኛ በተከራካሪነት ምሳሌ እንደሚታይልን ያበሥረናል። ሮሜ 8፥33-39። በአበው አገላለጽም «ሊቀ ካህናት ዘይቀውም ሎሙ ለቅዱሳን በደብተራ ስምዕ እንተ እግዚአብሔር ተከላ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እግዚአብሔር ራሱ በሠራት ደብተራ ስምዕ (የምስክር ድንኳን) ለቅዱሳን ሊቀ ካህናት ሆኖ የሚቆምላቸው (የሚታይላቸው የሚከራከርላቸው) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» መጽ. ሰዓታት።

በግለት የተደመደመው የዳኞቹና የታዛቢዎቹ መግለጫ በሊቀ ሊታውንት ዮሐንስ ተነበበ። አንዳንድ ጥያቄዎችም ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖችና ከሰሚዎቹ ቀርቦ መልስ፥ ማብራሪያና አስተያየት ተሰጥቶበታል። በመጨረሻ ሁለቱም ወገኖች በተሰጠው የዳኝነት ውሳኔ መስማማታቸውንና በማብራሪያውም መርካታቸውን አስረድተው፥ ሁሉም በአንድነት «ይህን የመሳሰለ የተለያየ ትምህርት በቤተ ክርስቲያናችን ሊፈጠር የቻለው በቅዱሳት መጻሕፍትና በአበው ጥንታዊ አስተምህሮ ላይ ካለመጽናት የደረሰ እንደሆነ ተገንዝበናል» አሉ። «ለወደፊቱም በዕለተ እሑድ ትምህርት ቤቶችና በዐውደ ምሕረት ጥራት ያለው ትምህርት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሊሰጥ ይገባል» በማለት አሳሰቡ።

በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ፍሬምናጦስ ለውይይቱ መድረክ በማዘጋጀት ትጋትና ጥሬት የታየባቸውን አለቃ ነቅዐ-ጥበብንና የሥራ ባልደረቦቻቸውን አመስግነዋል። በማያያዝም፤ «በወንጌል እንደተገለጠው የእርሻው ባለቤት በእርሻው ብዙ የእህል ዓይነቶችን ግለት ገብስን፥ ባቄላን፥ አተርን፥ ሽንብራን፥ አደንጓሬን የመሰለ ብዙ ዘርን አልዘራም፤ ስንዴን ብቻ ዘራ እንጂ። የእርሻው ጠባቂዎች ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘራ። የተዘራው እንክርዳድም ሊታይ የተቻለው ከወራቶች በኋላ ማለት በፍሬ ጊዜ ነበር። ይህም ወቅት እንክርዳዱን ለመንቀል አስቸጋሪ የሆነበት ጊዜ ነው፤ እንክርዳዱ ተመቻችቶ በእርሻው ውስጥ ስፍራ ስለያዘ እርሱን ለመንቀል ሙከራ ቢደረግ ኖሮ ስንዴውም አብሮ በተነቀለ ነበር። ስለዚህ የተሻለ ዘዴ ሆኖ የተገኘው በመከር ወራት በፍሬያቸው መሠረት መለየት ስለሆነ፥ ስንዴውንም እንክርዳዱንም ለየራስ ለማጨድ፥ ስንዴውን ወቅቶ ወደ ጐተራ ለመክተት፥ እንክርዳዱን ግን ወደ እሳት ለመጣል በባለቤቱ መወሰኑን ጌታ አብራራ።» (ማቴ. 13፥24-30፤ 36፤ 43)

አሉና ብፁዕነታቸው ቀጠሉ፤ «ጌታ ንጹሕ የሆነ ለሰባኪውም ለተቀባዩም የማያሳስት በስንዴ የተመሰለውን አንድን የደኅንነት ወንጌልን ብቻ አስተማረ። ወንጌልን የሚመስሉ ብዙ ወንጌሎች ቢኖሩም እነዚያ በጌታ አልተሰበኩም። ታዲያ ሰይጣን ይባስ ብሎ በዓይነቱ እህል ያልሆነውን ዐረም፥ እንክርዳድን በክርስትና ትምህርት ውስጥ ዘራ። መቼ? በእርሻ የተመሰለችውን ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ ታላቅ አደራና ኀላፊነት የተሰጣቸው አበው (ዮሐ. 21፥15-17፤ ሐዋ. 20፥28-30) ባንቀላፉበት ጊዜ ማለት ከወደቀባቸው ድንዛዜ የተነሣ ለሥልጣን፥ ለክብር፥ ለሀብት፥ ለዝና፥ ለገንዘብ ይሽቀዳደሙ በነበረበት፥ መንፈሳዊ እንቅልፍ በተጫጫናቸው ሰዓት ጠላት እንክርዳዱን ዘራ።» በማለት አቡኑ በትካዜ ተውጠው ተናገሩ።

ከዚያም ቀጠል አድርገው «ሆኖም» አሉ። «ሆኖም ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እንክርዳዱን ትምህርት ከንጹህ ወንጌል ጋር በማስተያየት በእንክርዳድ የተመሰለው ከጠላት ከሰይጣን የተዘራው ትምህርት የቱ፥ የቱ እንደሆነ ለይታ ዐውቃዋለች። እህል ሆነው ነገር ግን ስንዴም

ባይሆኑ ለሆድ መሙሊያ የሚያገለግሉት፥ ባዕድ ወንጌሎች የትኞቹ እንደሆኑም ተረድታቸዋለች።

ችግሯ ሌላ ነው» አሉ ብፁዕነታቸው ዓይናቸው በእንባ ተሞልቶ፤ «ችግሯ ሌላ ነው። ፍጹም እንክርዳድ የሆነውንና ስንዴ ያልሆነውን እህል የሚመስሉት ትምህርቶች በእርሻ በተመሰለችው ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሥር ሰድደዋል፤ በስንዴ ከተመሰለችው ንጹሕ ወንጌል ይልቅ በስፋት ስፍራ ይዘዋልና እንዴት ይነቀሉ?

ለምሳሌ፤

- እዚህ ካላችሁት መካከል የብዙዎቻችሁ አንገቶች ቢዳበሱ ከታብ ቢጤ ታብቶባቸው ይሆናል። የወንጌል ማዕተብ (ማኅተም) ብቻ ያለባቸው አንገቶች፥ዕፅ ያልተቀበረባቸው፥ ከጋኔን ጋር ያልተወራረሱ አገልጋዮች ቢኖሩ በጭጥር ጥቂቶች ናቸው።
- ዛሬ ለበረንትቻ፥ ለዛር፥ ለውቃቢ፥ ለጨሌ፥ ለአደባር፥ የሚሠዉ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ናቸው፤ የመሥዋዕቱ ባራኪዎችም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው።
- መስተሐምም፥ መስተፋቅር፥ መድፍነ ፀር፥ ዐቃቤ ርእስ፥ ግርማ ሞገስ፥ ዓይነ ጥላ፥ ጥላ ወጊ ወዘተ ለሚባለውና ለመሳሰለው ሁሉ አስማት ደጋሚዎች፥ ጋኔን ጎታቾች፥ ጠንቋዮች፥ መናፍስት ጠሪዎች፥ ሟርተኞች፥ የመታን ነፍሳት ሳቢዎች፥ ክክብ ቄጣሪዎች፥ ወዘተ ... በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሞልተዋል። ደጋሚዎቹም አስደጋሚዎቹም ተንሰራፍተው ይገኛሉ።
- የቤተ ክርስቲያናችን ልብስ ተክህኖና ንዋየ ቅድሳት በአብዛኛው ለባዕድ አምልኮ ከሚጠቀሙባቸው አልባሳትና ዕቃዎች ጋር ተመሳሳዮች ናቸው። በአንድ በኩል የቤተ ክርስቲያናችን አባላትና መሪዎች የሆኑት በሌላ በኩል የባዕድ አምልኮ ካህናት ሆነው የሚሠሩ ናቸው።
- ንዋያተ ቅድሳት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በስጦታና በብፅዐት የሚመጡት በአብዛኛው ለባዕድ አምልኮ ካህናት ገቢ ከሆኑት ውስጥ በክፍያ ድርሻችን የሆኑት ናቸው።
- የቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎቶች በአብዛኛው የተያዙት ከዚህ በላይ በተገለጹት የባዕድ አምልኮ ካህናት መሆኑን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ።

እንግዲህ እነዚህ እንክርዳዶች እንዴት ይነቀሉ? እውነት መናገር ይጣናልና በአሁኑ ጊዜ ድምፅ ቢሰጥ ቤተ ክርስቲያናችን የእንክርዳዶቹ ስፍራ ናት እንጂ የስንዴዎቹ አይደለችም። በስሟ የእኛ የክርስቲያኖች መድረክ በመሆኗ በውስጧ እንገኛለን። እስካሁን ድረስም በውስጧ መቄየታችን የሚያስደንቅ መለኮታዊ ሥራ ነው።

1) በመዝ. 124፥1-8 እንደተገለጸው እንክርዳዶች እንደ ብዛታቸውና እንደ ቁጣቸው ሊያጠፉን እየወደዱ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በመሆኑ ለጥርሳቸው ንክሻ እንሆን ዘንድ አላልፎ አልሰጠንም።

2) በመዝ. 118፥10-17 እንደተመሰከረውም በታጠቅነው ስውር ኃይላችን በሆነው በእግዚአብሔር ስም ከበባቸውን በመበጣጠስ ነው፤» በማለት ጎይልን በተሞላ ስሜት አባታችን ተናገሩ።

ከዚያም ሲያጠቃልሉ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃልና፤ ሰሞኑን በደብረ ፋይድ ገብርኤልና በደብረ መንክራት ኢየሱስ አብያተ ክርስቲያናት የዕለተ እሑድ ተማሪዎች መካከል እንደተካሄደው በፍቅር ላይ በተመሠረተ ውይይት አማካይነት በቤቱ ያስቀመጣቸው የክብር ዕቃዎች ከዝንተና ከመወየብ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ቅኝት ተወልውለውና ታድሰው በንጹሕ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ ጠቃሚነቱ ታምኖበታል።» 2ጢሞ. 2፥16-21 በማለት ንግግራቸውን ደመደሙ። ከዚያም ብፁዕነታቸው ጸልየውና ቡራኬ ሰጥተው **መርሐ ሕዝብ ሆኑ።**

መልካም ዜና!!

አርቶዶክሳዊ ትምህርተ ክርስትና፥ በመላላክ በነጻ ይሰጣል እንደገና።

ለመማር ይፈልጋሉን?

ሙሉ ስምዎን፥ የመ.ሣ. ቁጥርዎን፥ ገልጸው ይጻፉልን።

የእኛ አድራሻ የመ.ሣ.ቁ. 56307፥ አዲስ አበባ ነው።

ከገጽ 26 የዞረ፤

አራተኛው መብራት የሁኔታዎች መመቻቸት ነው። ነህምያ አራት ወር ሙሉ ሲጸልይ መብራቱ ቀይ ነበረ። በየቀኑ ቢጸልይም ለንጉሡ ባልተፈቀደው መንገድ ለመናገር አልቸኩለም ዛሬም በፈቃድ፥ በጤና፥ በገንዘብ፥ በትምህርት ጉድለት፥ በቤተሰብ ወይም በሌላ ምክንያት መብራት ቀይ ሊሆን ይችላል፤ የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ ግን መብራቱ አረንጓዴ ይሆናል። መብራቱ ቀይ ሲሆን ክርስቲያን በጸሎት መትጋትና በሚቻለው ሁሉ ለሥራው ራሱን ማዘጋጀት የእምነት መንገድ ነው።

አምስተኛው መብራት የልብ ሰላም ነው። ንጉሡ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ሲፈቀድለትና የሚሻውን ሲሰጠው ነህምያ በምንም መንገድ ሰላልተጠራጠረ የልብ ሰላም ነበረው፤ ተነሥቶም ሄደ። ሐዋርያው ጳውሎስ «የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ» ብሎ አዘዘን፤ ቈላ. 3፥15። የእግዚአብሔርን ሥራ በማከናወን ሂደት ብዙ ችግር፥ ብዙ ተቃውሞ፥ ብዙ መለያየት ... ወዘተ። ሊነሣ ይችላል። ክርስቲያን የተቀበለውን ጥሪ ሲከተል ግን የልብ ሰላም ካለው እስከ መጨረሻው ሊታገሥ ይችላል፤ የክርስቶስ ሰላም በልቡ ከሌለ እግዚአብሔር ፈቃዱን እስኪገልጥለት ድረስ መቆየት ይኖርበታል።

የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ

ከናሁ አዳም

ቤተ ክርስቲያንን ወደ ሞት እየነዷት የነበሩ የበሽታ ዓይነቶች ምንና ምን እንደሆኑ ባለፈው እትም ላይ በአጠቃላይ ቀርበው አንብበናቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ከሚያሰቃዩዋት በሽታዎቿ ትፈወስ ዘንድ በፈዋሽነቱ የታወቀውን ቅዱስ መንጌል አስይዞ፥ እግዚአብሔር እስጢፋኖስንና ደቂቀ እስጢፋ በመባል የታወቁትን ደቀ መዛሙርቱን አስነሥቶና ልኮላት እንደነበረ የሚተርከውን ከፍልም ተመልክተነዋል። ካራ ታጣቂው መንግሥት ንጉሥ ወሊ ዘርዓ ያዕቆብ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መራኑ፡ በእክርስቶፍሮስና በደቂቀ መዛሙርቱ ላይ ያደረሰባቸውን ስቃይ፥ ስደት፥ ግድያና ንብረት መወረስም በመጠኑ አይተናል። ከዚሁ ጋር የተያያዘውን ሌላውን ታሪክ ቀጥሎ እንመለከታለን።

1. ከመናፍስት ጋር የሚቈራኝ ድግምቱ

በአንድ ጊዜ የሁለት እቴጌዎች ባል፥ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መሪ፥ የጸሎት መጻሕፍት ደራሲ ነበር ተብሎ የሚተረክለት ወዜ ዘርዐ ያዕቆብ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናኖቿን ከመናፍስት ጋር ለግቈራኘት በቅዱሳን ስም እየደረሰና እያስደረሰ የጸሎት መጻሕፍትን አሠራጨ። በዚህ ሁኔታ እየጻረና እያጻረ ከበተናቸው የድግምት ጸሎቶች አንዱ ዛሬ ከ«አባታችን ሆይ (አቡነ ዘበሰማያት)» ቀጥሎ የሚደገመው «በሰላመ ንብርኤል፥ በንብርኤል ሰላምታ» የሚለው ነው። ይህ የድግምት ጸሎት እንደ ዛሬው ሁሉ ያን ጊዜም አባ እስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቱ እንዲከሰሱ ምክንያት ሆኖ ነበር።

የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም ጠርቶ ገብርኤል ያን ጊዜ ሰላም ላንቺ ይሁን ብሎሽ እንደነበረ እኔም ዛሬ ሰላም አልሻለሁ በማለት የሚጀምረው ሙገሳ፥ ልጅሽ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎጢአታችንን ይቅር እንዲለን ለምኝልን በማለት ይጨርሳል። ድርሰቱ በ500 ዓመታት ውስጥ ሥር እየሰደደና እየታወቀ የመጣ ሲሆን፥ ያን ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ ምእመናን በመልም በግልም እንዲጸልዩት በንጉሡ ሥልጣን ተበትኖ እንደነበረ መገመት አያስቸግርም። አባ እስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቱ ግን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ራሱን ከሰየመ መንፈስ ጋር የሚያቈራኝውን ይህን የድግምት ጸሎት አንቀበለውም አሉ። በዚህም ተከሰው እስከ ንጉሡ ድረስ ቀርበው እንደነበረ ገድሉ ይተርካል።

በመሠረቱ ሰው በአጠገቡ የሌለውን፥ እንዲያውም ከዓለመ ግዘፍ ወደ ዓለመ መንፈስ ተዛውሮ በአካለ ነፍስ በገነት ወይም በሲዖል የሚገኘውን፥ የቅርብ ዘመዱም ቢሆን እንኳ፥ ሊጠራውና ርዳታ ሊጠይቀው አይችልም፤ አይደግመውም፥ አይተያይም፥ እንደዚሁም በዓለመ መንፈስ ያለው ሰው በዓለመ ግዘፍ ከሚገኙ ዘመዶቹ ጋር ሊነጋገርና እርዳታ ሊጠይቅ አይችልም፤ ሁለቱም ወገኖች በተለያዩ ሁለት ዓለማት ውስጥ ይኖራሉና። ልዑል እግዚአብሔር ብቻ በዓለመ ግዘፍም በዓለመ መንፈስም መልቶ በሊውሉንነት በሁሉ ስፍራ የሚኖር መለኮት ሲሆን ፍጡራን ሁሉ ግን ዓለማትን መልተው እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ይገኙ ዘንድ ባሕርየ ተፈጥሮአቸው አይፈቅድላቸውም።

በወጸደ ሥጋ ያሉ ፍጡራን በዓለመ ግዘፍ ሲኖሩ በወጸደ ነፍስ ያሉት ግን በዓለመ መንፈስ ይኖራሉ። በዓለመ መንፈስ ያሉትም ደግሞ በዓለመ ግዘፍ ካሉት ጋር ሊገናኙና ሊነጋገሩ የሚችሉት ነፍሳቸው ከዓለመ መንፈስ ወጥታና ወደ ሥጋዋ ተመልሳ ስትገባና በአካለ ሥጋ ስትገለጥ ብቻ ነው፤ ወይም እግዚአብሔር ክብሩን ለመግለጥ ወዶ በአካለ ነፍስ እንዳለች እንድትገለጥ ሲፈቅድ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክብሩን በገለጠበት ተራራ እንደተደረገው ማለት ነው። ማር. 9፥4።

የሰው ነፍስ ከሥጋ በምትለይበት ጊዜ የሚች ዘመዶች ሲጨነቁ፥ ሲያለቅሱ፥ መጽናናት አቅቷቸው ከፍተኛ የኅሊና ስብራት ሲደርስባቸው፥ በጠቅላላው በዓለመ ግዘፍ እየተካሄደ ካለውና ከሚሆነው ነገር ሁሉ የሚች ነፍስ የምታውቀው ምንም የለም። ብታውቅማ ኖሮ በመሪር ኀዘን የተዋጡትን ዘመዶቿን፥ ተዉ፥ ተጽናኑ ባሉዋቸው ነበር። ሁለቱም ወገኖች በሁለት በተለያዩ ዓለማት ውስጥ ስለሚኖሩ ብሚች ነፍስና በሚች ቋሚ ዘመዶች መካከል መደግመጥ፥ መተያየት፥ መልስ መሰጣጣት ሊኖር አይችልም፤ ሊኖር ያልቻለበትና የማይችልበት ምክንያትም የሚች ነፍስ ወደ አለመኖር ከመለወጧ የተነሣ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ነፍሳት በገነት ወይም በሲዖል ሊሆኑ ይችላሉ። ከቋሚዎች ጋር የማይተያዩበትና የማይደማመጡበት ምክንያት ግን የሚችኽ ነፍሳት በገነትም ሆነ በሲዖል ቢሆኑ እነርሱ የሚገኙበት ዓለመ መንፈስ ሲባል የሚችኽ ቋሚ ዘመዶች ደግሞ በዓለመ ግዘፍ ስለሚኖሩና በሁለቱ ዓለማት መካከል ግንኙነት ስለማይኖር ነው።

የአምልኮተ እግዚአብሔር ክፍል አይደለም እንጂ በአረማውያን ዘንድ ከጥንት ጀምሮ በሚርት፥ በጥንቈላ፥ በድግምት የሞቱ ሰዎችን ነፍሳት እንስባለን እያሉ ከሚገለጡላቸው መናፍስት ጋር መነጋገር፥ ምክርና ርዳታ መጠየቅ የተለመደ ነበር። መናፍስትንም ሆነ የሙታንን ነፍሳት በድግምት እንዳይጠሩና እንዳይጠሩ፥ እግዚአብሔር ደቂቀ እስራኤልን፥ የከለከላቸው ይህን አረማዊ ልምምድ እንዳይወርሱና ከመናፍስት ጋር እንዳይቈራኙ ማስጠንቀቁ ነበር። ዘሌ. 19፥26፤ 31፤ 20፥6፤ ዘዳ. 18፥9-12።

መቸም በእግዚአብሔር ቃል ስማቸው ተጠቅሶ እንድናውቃቸው ከተደረጉት ቅዱሳን መላእክት ከሚካኤልና ከገብርኤል በቀር፥ እልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክት በጌታ ፊት ቆመው እንደሚያገለግሉ እናውቃለን። (ዳን. 7፥10፤ ራእ. 5፥11) ከዓለመ ግዘፍ ወደ ዓለመ መንፈስ የተዛወሩ (ሞቱ) ሰዎች ነፍሳትም በየተመደበላቸው ቦታ በገነት ወይም ለሲዖል ተቀምጠዋል፥ ይቀመጣሉም፤ እስከ ፍርድ ቀን ድረስም በዚያው ይቆያሉ። ስለሆነም መላእክትንም ሆነ ነፍሳትን በዓለመ ግዘፍ የሚገኝ ሰው ቢጠራቸው አይሰሙምና ለጥሪው ምላሽ አይሰጡም።

በዓለመ ግዘፍ ያሉ ደቂቀ አዳም በእግዚአብሔር ፊት የመኖራቸውን ያህል በዓለመ መንፈስ ያሉ መላእክትም በእግዚአብሔር ፊት ሆነው ያመሰግኑታል፥ ትእዛዙንም በጥንቃቄ እያዳመጡ ሲላኩ እንደ ፈቃዱ ፈጽመው ይመለሳሉ። ዘማሪው «ቃሉን የምትፈጽሙ ብርቱዎችና ኀያላን ያቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ባርኩ። ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ እግዚአብሔርን ባርኩ» ይላል። (መዝ. 103፥20-21) መላእክትም በሚላኩበት ጊዜ ሥልጣን ባለው በእግዚአብሔር ቃል ከዓለመ መንፈስ ወጥተው ወደ ዓለመ ግዘፍ ይገባሉ፤ ተልእኳቸውን ከፈጸሙ በኋላም ወደነበሩበት ዓለም ይመለሳሉ።

በዓለመ መንፈስ ያሉት መላእክትና የሞቱ ሰዎች ነፍሳት፥ እንደዚሁም በዓለመ ግዘፍ ያሉ ደቂቀ አዳም ሁሉም በእግዚአብሔር

ፊት የሚኖሩ ቢሆኑም እርስ በርሳቸው አይተያዩም፥ አይደማመጡም፤ በተለያዩ ዓለማት የሚኖሩ ሁሉ በየዓለማቸው በስፍራ የተወሰኑ ፍጡራን ናቸው።

ታዲያ እንደዚህ ከሆነ አረማውያን ሲጠሯቸው የሚገለጡላቸው ወይም ምላሽ የሚሰጧቸው እነማን ናቸው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ምስጢሩን የተረዳ ሰውም ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት እንደሚችል ይታወቃል። ለአረማውያን በድግምት፥ ወይም በሟርት ጥሪያቸው የሚገለጡላቸው መናፍስት በጌታ ፊት ከቆሙት ቅዱሳን መካከል ያሉ መላእክት አይደሉም፤ እንደዚሁም በሰዎች ነፍሳት ተመስለው የሚገለጡላቸው በሲያል ወይም በገነት ከሚገኙት መካከል የሆኑ ነፍሳት አይደሉም። በመላእክትና በነፍሳት ተመስለው የሚገለጡላቸው የወደቁ መላእክት ማለት ሰይጣንና ጭፍሮቹ ናቸው።

የወደቁት መላእክት (ሰይጣንና ጭፍሮቹ) ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛትን ትተው በፈቃዳቸው አዳሪዎች ሆነዋልና፤ በዚህም ምክንያት ከሥራቸውና ከስፍራቸው ተጥለዋል። ኢዮብን ለመክሰስ በእግዚአብሔር ፊት የቀረበው ሰይጣን «ምድርን ሁሉ ዞርሁዋት፤ በእርስዋም ተመላለስሁ» ሲል (ኢዮ. 1፥7፤ 2፥2) እንደፈለገው ሲንቀሳቀስ የሚኖር፥ መላእክትንና ነፍሳትንም እየተመሰለ አለሁ፤ መጣሁ የሚል ፍጡር መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስም ይህንኑ የሰይጣን ዘዋሪነት እንዲህ ሲል ገልጾታል። «የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና» 1ጴጥ. 5፥8።

ሰይጣንና ጭፍሮቹ በምድር ላይ በመንቀሳቀስ ሲኖሩ፤

- የእግዚአብሔር መንፈስ በሌለባቸው ሰዎች ያድራሉ። ማቴ. 12፥43-45
- በእንስሳት ውስጥ ያድራሉ። ማር. 5፥11-13
- ምድርንና የከበባትን አየር ሁሉ ይቈጣጠራሉ። ዮሐ. 12፥31፤ ኤፌ. 2፥1-2።
- የወደቁ መላእክት እንደመሆናቸው መጠን ረቂቃን፥ መንፈሳውያን ናቸው። ኤፌ. 6፥12።
- በድግምት ለሚጠሯቸውና የእግዚአብሔርም መንፈስ ለሌለባቸው ሰዎች ራሳቸውን ለውጠው በብርሃን መላእክትና በጌታ ሐዋርያት ተመስለው ይቀርባሉ። 2ቆሮ. 11፥13-15።

መልአክ ማለትም ከጥንቱ ከዉቱ በጌታው ሲጠራ፤ «አቤት! ሲላክም ወዴት?» የሚል ተላላኪ፥ አገልጋይ ማለት ስለሆነ እንደ ሰይጣንና ጭፍሮቹ ሲንቀሳቀስ የሚውል ሊሆን አይችልም። የተሰጠውን ሥራና ስፍራ በመተው፥ በራሱ ፈቃድም ከዓለመ መንፈስ ወጥቶ ወደ ዓለመ ግዘፍ አይሻገርም። የመጀመሪያው ስሑት ፍጡር የሆነው ሰይጣንና እርሱን የተከተሉት ጭፍሮቹ ከማዕርጋቸው ለመውደቅ የበቁት እግዚአብሔር በተፈጥሮ የሰጣቸውን መኖሪያ ሥራና ስፍራ ትተው፥ ባልተመደቡበት በመገኘታቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁዳ 6።

ይሁዳ መኖሪያ ሥራንና ስፍራን የተው ናቸው ያላቸውን ሰይጣንና ጭፍሮቹን፥ ቅዱስ ጴጥሮስ «ጎጢአትን ያደረጉ» ብሎ ስለሚገልጻቸው፥ ከተመደቡበት መኖሪያ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ በራሳቸው ፈቃድ መንቀሳቀሳቸው ጎጢአት ሆኖ እንደተቈጠረባቸው ያመለክታል። 2ጴጥ. 2፥4።

ሰዎች መናፍስትንና (መላእክትንና) በሲያል ወይም በገነት ያሉ ነፍሳትን በሚጠሩበት ጊዜ ተጠሪዎቹ በሰው ፕሪሊመጡ ባይችሉም፥ እነዚህ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ የወደቁ መላእክት «ሳይጠሯቸው አቤት ባይ፥ ሳይሰጧቸው ተቀባይ» ለመሆን የሚተጉ ናቸውና «የተጠራነው እኛ ነን» በማለት ተጠሪዎቹን ቅዱሳን መላእክትንና የሰዎችን ነፍሳት ተመስለው ይገለጣሉ። ይህንንም ሁኔታ በሚገባ ለማስተዋል፥ የሞቱ ነፍሳትን በሟርት ድግምቷ በመጥራት የታወቀችው እንዶራዊት የሞተውን ሳሙኤልን የሚመስል መንፈስ ለንጉሡ ለሳዖል በመሳብ እንዳመጣችለት መጽሐፍ ቅዱስ የሚተርከውን ደጋግሞ ማንበብ ይገባል። 1ሳሙ. 28፥1-19።

እንግዲህ አባ ዐቤ ዘርዐ ያዕቆብ በዘመነ መንግሥቱ ከፈጸማቸው ክፉ ሥራዎቹ መካከል አንዱ ዋነኛው ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳይለማመዱት የተከለከለውን አረማዊ ባህል መውረሱ፡ መናፍስትንና ነፍሳትን የመሳቢያ ድግምት እየደረሰ፥ ምእመናንን በግልም በቤተ ክርስቲያንም እንዲጸልዩት ማስገደዱ ነበር። ከእነዚህም የመናፍስት መሳቢያ ድርሰቶቹ መካከል «በገብርኤል ሰላም ታ ሰላም እልሻለሁ» ተብሎ የተደረሰውን ሙገሳ አባ አስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቱ አልተቀበሉትም፤ የእምቢተኝነታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር ቃል የተከለከለ አረማዊ ባህልና ልምምድ በመሆኑ እንጂ የንጉሥነቱን ሥልጣን ለመጋፋት አስበው አልነበረም።

አባ አስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቱ የወልም ሆነ የግል ጸሎታቸውን ጌታ ባስተማረው ጸሎት «አቡነ ዘበሰማያት፤ አባታችን ሆይ» በሚለው ይደመድሙ ነበር ማለት ነው።

ከጌታም ሆነ ከሐዋርያት በተማርነው የጸሎት አቀራረብ ትምህርት ውስጥ፥ የትኛውንም መልአክ ቢሆን፥ በገነት ወይም በሲያል የሚገኘውን የማንንም ነፍስ ቢሆን የጸሎታችን ሰሚና ተቀባይ አድርገን እንድንጠራ አልታዘዝንም። ምንጊዜም ለጸሎታችን ሰሚና ተቀባይ አድርገን ልንጠራው የሚገባ እግዚአብሔርን ብቻ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል። «ሕዝቡ በሄደበት መንገድ እንዳልሄድ፥ እግዚአብሔር በብርቱ ጎደሉ አስጠነቀቀኝ፥ እንዲህም አለኝ፥ «በሚያቅደው ነገር ሁሉ ከዚህ ሕዝብ ጋር አትተባበሩ፥ እነርሱ የሚፈሩትንም ሁሉ አትፍሩ፤ እኔ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆንሁ አስቡ፤ መፍራት የሚገባችሁም እኔን ብቻ ነው።

«... በሹክሹክታ የሚንተባተቡትን ሟርተኞችንና የሙታን **መናፍስት ጠሪዎችን ጠይቁ» እያሉ የሚነግሩአችሁ ወንዶች ሁሉ፤ ታዲያ ስለ ሕያዋን ሙታንን ከመጠየቅ ይልቅ፥ ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? ስለዚህ ለእነርሱ «እግዚአብሔር የሚያዝዛችሁንና የሚያስተምራችሁን ቃል ስሙ፤ የሙታን መናፍስት ጠሪዎች የሚሉአችሁን ግን አትስሙ፤ ምክንያቱም ከእነርሱ የምትሰሙት ነገር ምንም አይጠቅማችሁም «ብላችሁ መልሱላቸው» ኢሳ. 8፥11-12፤ 19-20።

ከሐዲስ ኪዳንም የቅዱሳንን ልምምዶችና መመሪያዎች ብንመረምራቸው ይህንኑ ያስገነዝቡናል።

- ለሐዋርያት የጸሎታቸው አድራሻ ልዑል እግዚአብሔር ነበር፤ ሐዋ. 1፥25-26፤ 4፥24።
- የሐዋርያው የጳውሎስ ጸሎት አድራሻ ልዑል እግዚአብሔር ነበር። ሮሜ 1፥8፤ 1ቆሮ. 1፥4፤ 2ቆሮ. 1፥3፡ ኤፌ. 1፥17፤ 3፥14-15።

ወደ መናፍስትና ወደ ሰዎች ነፍሳት ራሱ የጸለየ ወይም ክርስቲያኖች እንዲጸልዩ መመሪያ የሰጠ ሐዋርያም ሆነ ወንጌላዊ የለም።

2. ቅዱሳት መጻሕፍትን የመከለስና የመበረዝ ድርሰቱ፤

አባ ዐቤ ዘርዓ ያዕቆብ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ተጽፈው የምናነባቸው ታሪኮችና ትምህርቶች የያዙትን ሐሳብ ያለ ጎፍረትና ይሉኝታ ገልብጦ የእግዚአብሔርን ስም እያወጣ የማርያምን ወይም የሌላ ያሰኘውን ስም ሲያስገባ ጎሊናውን የሚሰቀጥጠው ሰው አልነበረም። የታወቁትን የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪኮች ዐዲስ ድርሰት አድርጎ እንዴት እንደሚጽፋቸው አንባቢ ይረዳ ዘንድ «ተአምረ ማርያም» ከሚባለው መጽሐፉ አንዱን ተአምር ከዚህ ቀጥሎ አቅርበነዋል።

«በእንተ ጳውሎስ ሐዋርያ

ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ

ልመናዋ ክብሯም በኛ ለዘላለም በእውነት ይደርብንና አምላክን የወለደች በድንግሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችን ያደረገችው ተአምር ይህ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክቱ እንደተናገረው መላእክት እስከ ሦስተኛ ሰማይ ድረስ አሳርገውት ሳለ፥ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ስለ ጸናች ስለ ክብርት እመቤታችን ክብር ሲናገር እንዲህ አለ።

እኔ ጳውሎስ ገና አብያተ ክርስቲያናትን በማፈራርስበትና የጌታን ደቀ መዛሙርት ለመግደል በማሳድድበት ጊዜ ይልቁንም በየመንደሩ እየገባሁ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጐተትኩ ወደ እስር ቤት በምጨምርበት ወቅት፤ እነሆ ከዚያ ምእመናንን እያደንኩ የምይዝበት የሥልጣን ደብዳቤ ይዤ ወደ ደማስቆ ሰንዛ ድንገት ከሰማይ ጸዳል አንጸባረቀብኝ።

በዚህም ጊዜ በምድር ላይ ወደቅሁና እነሆ በሰው ልጅ አንደበት ሊነገር ወይም ሊተረጐም የማይቻል ቃል ሰማሁ። ከእኔም ጋር ቆመው የነበሩ ሰዎች ድምፁን ከመስማት በቀር ማንንም አላዩም። በመሬትም ላይ ወድቄ እየትፍገመገምኩ ሳለሁ እኔን ጭንጋፍ የሆንኩ ሰው መላእክት መጥተው አጽናኙኝ፥ አንሥተውም እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ አሳረጉኝ።

በዚያም ጊዜ የደም ጥማቷ ጸዳል እንደ ፀሐይ የሚያበራ ድንግል ከሩቅ ስትመጣ ተመለከትኩ። ከእሷም ጋር ሁለት መቶ መላእክት በፊትና በኋላዋ ሆነው እየዘመሩ መጡ። ከእኔም ጋር ያለውን መልአክ ይህች ማናት? በዚህን ያህል ክብር ከብራ የምትመጣ አልሁት። መልአኩም ይህች አንተ የምታሳድደው የናዝሬቱ የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ናት አለኝ። በዚያም ጊዜ ወደ እኔ መጣችና ሰላም ከአለችኝ በኋላ ሳውል፡ ሳውል ልጄን የናዝሬቱ ኢየሱስን ለምን ታሳድደዋለህ? የሸለውን ብረት ብትረግጥ ለአንተ ይብስሃል።

እኔም እየፈራሁና እየተንቀጠቀጥሁ፥ እመቤቴ ሆይ፤ ስለ ጎጠአቴ ምን አደርግ ዘንድ ይገባኛል የሰው ደም እያፈሰስኩ ወንጀለኛ ሆኛለሁና፥ አሁንም እመቤቴ ሆይ፥ ጎጢአቴን ይቅር በይልኝ እሷ አንቺ እናቱ እንደሆንሽ ተገልጸልኛልና አልኩ። እሷም እነሆ ጎጠአትህ ይሰረይልህ ዘንድ ስለ ለመንኩልህ እነሆ ጎጢአትህን ይቅር ብሎሃል፥ አሁንም በሕይወት ሥጋ ሳለህ ወደዚህ ትመጣ ዘንድ ልጄን የሱስ ክርስቶስን ማለድኩት፤ እሱም እሺ ጥቂት ታገሺ አመጣዋለሁ አለኝ።

ይልቁንም አቤቱ ልጄ ወዳጄ አታዘግይብኝ ፈጥኖ ልታመጣው እመጻለሁ፡ በእሱ የትምህርት ዘመን ስምህ እጅግ እንዲመሰገን ታውቃለህና አልኩት። ልጄ ወዳጄም አዎን እናቴ ሆይ በእሕዛብና በነገሥታት በእስራኤልም መካከል የሞቴን መስቀል ተሸክሞ በጣፈጠ አንደበቱ በቀለጠፈ አነጋገሩ በታማኝነቱ የወንጌልን መንግሥት ያስተምር ዘንድ የተመረጠ ዐርበኛ አድርጌ አልከዋለሁ አለኝ። በስሜ ብዙ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው ብሎሃልና ስለዚህ በሥላሴ ስም ተጠመቅ፡ እነሆ አሁንም ቅዱሳኖች ሁሉ ታላቅ አቀባበል የደርጉልሃል አለችኝ።

ይህች ድንግል እንዲህ እያለች በምትነግረኝ ጊዜ እነሆ ፊታቸው ብሩህ የሆነ ሦስት ሰዎች መጡ። ከእኔ ጋር የነበረውን መልአክ እሊህ እነማናቸው? ብዬ ጠየቅሁት። እሱም እሊህ አባቶች አብርሃም፥ ያሕቅ፥ ያዕቆብ ይባላሉ አለኝ። እነሱም መጥተው ለእመቤታችን ሰገዱ፡ እኔንም ሰላም አሉኝ እኔም እጅ ነሣኋቸው።

ከዚህም በኋላ እመቤታችን ከሷ ጋር ከነበሩ መላእክት መካከል ሦስቱን በዮርዳኖስ ውሃ ያጠምቁኝ ዘንድ ነገረቻቸው። እኔም ተጠመቅሁ፤ የመንፈስ ቅዱስም ጎይል መላብኝ፥ አደረብኝ። በዚያም ጊዜ በደሌ ሁሉ ከዓይኖቼ እንደ ቅርፊት እየተቀረፈ ወደቀ። ብርሃንም መላብኝ፥ ጎይኖቼም ተከፈቱ፤ ያን ጊዜውንም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለማስተማር እፋጠን ጀመር።

ይህንንም ያዩ ሁሉ አደነቁ፡ እንደዚሁም በያሁዳና በገሊላ፥ በሰማርያም የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዕረፍት አገኙ፡ በእግዚአብሔር ቸርነትና በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት እየተስፋፉና እየጸኑ ሄዱ አለ ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ክብር በተጠራ ጊዜ።

እናንተ የእግዚአብሔር የወንጌሉና የሰላም ልጆች! አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችንን ጳውሎስ ያየውን ክብርና መላእክት በፊት በኋላዋ ሆነው እየዘመሩ ሲያከብሯት ተመልከቱ። እነሆ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችን ምስጋና በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም በመላእክት እንደበት ይነገራልና።

እንግዲህ ጳውሎስን መላእክት እንዳከበሩት እኛንም ያክብሩን ዘንድ ባለን ጎይል ሁሉ እመቤታችንን ማመስገን ይገባናል። ይልቁንም ጳውሎስን ከፈጣሪዋ አማልዳ ለጌታው የታመረጠና የታመነ እገልጋይ እንዳደረገችውና ከሐዋርያት ማዕርግ እንደ አደረሰችው የቸርነቷን ብዛት እናስተውል። የእኛንም ጸሎታችንንና ልመናችንን ለዘለዓለሙ ክብር የተገባው ወደ ልጅዋ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ታሳርግልን፤ ከወዳጆቹ ከቅዱሳን ጋር አንድ ያደርገን ዘንድ ለዘለዓለሙ። ልመናዋ ክብሯ በእውነት ለዘለዓለሙ በኛ ይደርብን። ተስፋ ማተሚያ ቤት በ1983 የታተመ 97ኛ ተአምር።

ይህን ድርሰት ያነበቡ ወይም የሰማ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ ቅዱሳን የጻፉትን፥ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ የሚነበበውን ታሪክ ዐዬ ዘርዐ ያዕቆብ ሲበርዘውና ሲከልሰው ጎሊናው እንዴት ፈቀደለት እንደሚል የታወቀ ነው። ይኽ የብዙዎች ጥያቄ ነውና። የተአምረ ማርያም ጸሐፊና ደራሲ የሆነው ንጉሥ ግን የጳውሎስን ታሪክ ባለቤቱ የተናገረውን፥ መንፈስ ቅዱስም ያጻፈውን ያለ ጎፍረት ለውጦ ሲያቀርበው ከጎሊናው ወቀሳ ነጻ የወጣ ወይም ጎሊናው አስቀድሞ የሞተበት ሰው እንደነበረ ያረጋግጥልናል።

በመሠረቱ የሐዋርያት ሥራ 9፥1-18፤ 22፥3-16 እና 26፥4-18፤ የሚተርከው ጳውሎስ ገና ሳውል እየተባለ ይጠራ በነበረበት ጊዜ ጌታ በደማስቆ መንገድ ተገልጦለት ያምን ዘንድ የተጠራበትን ሁኔታ ነው። በሁለተኛ ቆሮንቶስ 12፥1-4 ያለው ታሪክም ጳውሎስ በአገልግሎቱ ላይ እያለ እስከ ሦስተኛ ሰማይ የተነጠቀበትን ራእይ የሚተርክ ነው። ሁለቱም በተለያየ ጊዜ የደረሱ ከሥተቶች ሲሆኑ የዘርዐ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ግን አደባልቆ አንድ አድርጓቸዋል።

በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አገላለጽ ሳውል እንዲያምን፥ ሐዋርያም እንዲሆን የተጠራበት ዘመን ጌታ ባረገ በስምንተኛ ዓመት መሆኑ ይተረካል። ጳውሎስ እስከ ሦስተኛ ሰማይ የተነጠቀበት ጊዜ፥ ሳውል ካመነ በኋላ ስድስት ዓመት ቆይቶ ወይም ጌታ ባረገ በዐሥራ አራተኛው ዓመት እንደሆነ ሊቃውንቱ የሚተርኩ ሲሆን ለቆሮንቶስ ምእመናን ይህን ሁለተኛውን መልእክት የጻፈበትን ዘመን የመነጠቁ ታሪክ ከተፈጸመ ከ14 ዓመት በኋላ ቄይቶ መሆኑን አከለው ይገልጻሉ። (ትርጓሜ ጳውሎስ አንድምታ)

ዐዬ ዘርዐ ያዕቆብ ግን ስለ ታሪክ ቢሆን፥ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እውነት ቢሆን ደንታ የሌለው የቅዱሳንን ክብር ለማጋነን አስመስሎ ሐሰትን ከሚሰብክ መንፈስ ጋር የተወራረሰ፥ የቅዱሳን ክብር ምንጭ የሆነውን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ክብር በውሸት ለቅዱሳን በመስጠት እነርሱን ያለ ክብር ያስቀረ አደገኛ ሰው እንደሆነ በሥራው ይታወቃል። እስኪ እግዚአብሔር በፈጠረልን በልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ነጻ በወጣው ጎሊናችን እንመዝነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገሩትን እውነት በመለወጥ፥ የለም ይህ የተደረገው በቅድስት ድንግል ማርያም ነው እንጂ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም ብንል ቅድስት ድንግል ማርያም በውሸተኛ ታሪክ ትከብራለችን? ከቶ አትከብርም።

ይህን እውነት ይዘን የተአምረ ማርያምን ታሪክ በዝርዝር ባይሆንም በአጠቃላይ ወደ መገምገም እንመለስ። ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ታሪክ በሚመለከት የሰጠውን የምስክርነት ቃል፤ ወንጌላዊ ሉቃስም አዋሕዶና በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የጻፈውን ከ1400 ዓመት በኋላ የተነሣው ዘርዐ ያዕቆብ የሚቀበለው ቢያገኝ በሚከተለው ሁኔታ አስተባብሎታል።

1) ሳውል (ጳውሎስ) በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስደነግጥ ብርሃን በተገናኘው ጊዜ ዓይኑ መታወሩንና ማንንም ሳያይ ድምፅ ብቻ መስማቱን ቅዱስ መጽሐፍ ሲተርክ፥ የዘርዐ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ግን፤ የለም፥ ጳውሎስ ድንግል ማርያምን ከሁለት ሙቶ መላእክት ጋር፥ እንደዚሁም አብርሃምን፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን አይቷል ይላል።

2) ጳውሎስ «ስለምን ታሳድደኛለህ?» የሚለውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ ሰማሁ ማለቱ በቅዱስ መጽሐፍ የተመዘገበ ሲሆን፥ የዘርዐ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ግን፤ የለም፥ ልጇን ለምን ታሳድደዋለህ? ያለችው ድንግል ማርያም ናት ይላል።

3) ጳውሎስ፥ «በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ የለየኝ፥ የጠራኝም ከጸጋው የተነሣ ራሱ እግዚአብሔር ነው» ሲል (1ቆሮ. 15፥8-10፤ ገላ. 1፥15-16፤ 1ጢሞ. 1፥12-17) የዘርዐ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ግን፥ የለም፥ ጳውሎስ ለእምነትና ለሐዋርያነት የተጠራው በድንግል ማርያም አማላጅነት ነው ይላል።

4) በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ሳውልን (ጳውሎስን) ያጠመቀውና ያስተማረው ሐናንያ የተባለው ደቀ መዝሙር እንደሆነ የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ሲናገር፥ የዘርዐ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ግን፤ የለም፥ በቅድስት ማርያም ትእዛዝ ጳውሎስን ያጠመቁት ተክትለዋት ከመጡት መካከል ሦስት መላእክት ናቸው ይላል።

5) ጳውሎስ፥ በተጠመቀበት በደማስቆ ከደቀ መዛሙርት ጋር ጥቂት ቀን መቀመጡን የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ሲናገር፥ የዘርዐ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ግን፥ የለም፥ ጳውሎስ የተጠመቀው በዮርዳኖስ ውሃ ነው ሲል ይተርካል።

በተአምረ ማርያም ውስጥ የሰፈረውን ሐሰት ለቅሞ ለማውጣት ረጅም ጊዜንና ብዙ ወረቀትን መጠቀም ያስፈልጋል። መቼም የመጽሐፉ ዓላማ ግልጽ ነው፤ በአጠቃላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት ለማስተባበል፥ ትእዛዙንና ታሪኩን ለመበረዝና ለማከለስ ረቂቅ የሰይጣን ሥራ በውስጡ እንዳለ ይታየናል። ራሱ ጳውሎስ «ከመ ኢይትአገለነ ሰይጣን ዘእኮ ኀሳቤሁ ጎሊናሁ። በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና።» እንዳለው (2ቆሮ. 2፥11) የጠላታችንን ተንኮል ነቅተን ለመከላከል ቁርጠን ለተነሣን ይሽን የመሳሰለው የሰይጣን አሠራር ምንም ያህል የረቀቀ ቢመስል ከቶ አይሰወረንም።

የእምነታችን መሠረት የሆነውን ቅዱሱን መጽሐፍ ለማስተባበል በዚህ ሁኔታ የተቀናበረው ተአምረ ማርያም የክርስቶስን ሥጋና ደም ይተካል ተብሎ በመጽሐፉ ውስጥ ሰፍሮአል። መንፈሳዊ መብል የሆነውን ሥጋዉን ያልበላ፥ መንፈሳዊ መጠጥ የሆነውን ደሜን ያልጠጣ ሰው የዘላለም ሕይወት የለውም ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር (ዮሐ. 6፥35-63) ዘርዐ ያዕቆብ ግን እኔ የጻፍኩት ሐሰትን የሚያወራው መጽሐፍ (ተአምረ ማርያም) ጎጢአትን ለማስተስረይ የተቈራረሰውን የጌታን ሥጋና የፈሰሰውን ደሙን ይተካል ይላል። ምእመን በምስጢረ ቍርባን አምክይነት ከጌታው ጋር እንዳይገናኝ ሰይጣን በዘርዐ ያዕቆብ በኩል ይህን የመሰለ ደባ ሠርቷል።

ይህን ሐሰተኛ ትምህርቱን የተቃወመውን አባ እስጢፋኖስን ከነ ደቀመዛሙርቱ እንዴት እንዳስገደላቸው ገልጾ ዘርዐ ያዕቆብ በትዕቢት የፎከረበት ታሪክም በዚሁ ተአምረ ማርያም ውስጥ ተጽፎአል። ይህም ሆኖ ተአምረ ማርያም በግብጽ በመንበረ ማርቆስ ከጥንት ጀምሮ የነበረና በእኔ ዘመን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመ ነው ይለናል። ሆኖም «አንተ ሐሰተኛ፥ በዘመንህ፥ አንተው ራስህ የሠራኸውን የሚተርከውን መጽሐፍ ከመንበረ ማርቆስ መጣ ብለህ እንዴት ታታልለናለህ?» ለማለት የደፈረ ሰው ከአባ እስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቱ በቀር አልነበረም።

3. የቍርባንን ጎብስት በእንጨት ላይ ለምን ትፈትታለህ?

ታቦት ተብሎ ከማእከል በተሰጠ ንዋየ ቅድሳት ላይ ካልሆነ በቀር ጎብስተ ቍርባን እንዳይፈተት የተላለፈውን መመሪያ አላከበረም ተብሎ አባ እስጢፋኖስ ተከሶ እንደ ነበረ ገድሉ ይተርካል። በባዶ ጠረጴዛ (ወይም ገበታ) ላይ ጎብስተ ቍርባንን እንዴት ወይም ለምን ትፈትታለህ? ነበር የአባ ዐዜ ዘርዐ ያዕቆብ ጥያቄ።

ይህን ዐዲስ ሥርዓት ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነው የአበረኛው የአባ እስጢፋኖስም መልስ እንዲህ የሚል ነበር። «ወበእንተሰ ዘይቤ በዕፅ ትንብር መሥዋቱ፥ ወልዎ እወ አምከርክዎሙ ለእጓየ ይግበሩአ፤ እስመ ኢረክቡ ውስተ መጻሕፍት ዘይብል ኢይግበሩ በዕፅአ፤ እስመ ክርስቶስ ዘተሰቅለ ዲቤሁ ዕፅአ፤ ወቀደሶ በደሙ ለዕፀ መስቀልአ። ታቦትኒ ዘይትገበር ዕፅ ውእቱ ዘይትቀባዕ ሜሮንአ፤ ወለዘሰ ይፈቅድ ይግበር በወርቅ ወብብሩር ኢግእዝክምአ። በዕንጨት ላይ ጎብስተ ቍርባንን ትፈትታለህ ለተባለው፥ አዎን በዕንጨት ላይ እንዳይቀርብ የሚከለክል ትእዛዝ በመጻሕፍት ውስጥ ስላላገኘሁ፥ ወንድሞቼን በእዚህ ሁኔታ እንዲሠሩ ምክር የሰጠኋቸው እኔ ነኝ። (አማናዊው መሥዋዕት) ክርስቶስም ራሱን መሥዋዕት አድርጎ የሰጠው በዕንጨት ላይ ነውኮ። ዕፀ መስቀልን በደሙ ቀድሶታል። ታቦትም ቢሆን እኮ በሜሮን ተቀብቶ ነው እንጂ ከዕንጨት የተሠራ ነው። ሆኖም በብርና በወርቅ ጠረጴዛ ላይ ጎብስተ ቍርባንን የሚፈትተውንም እኔ አልነቀፍኩትምኮ።»

ስለ ታቦት በጮራ ቍጥር 15 በገጽ 12-16 የተጻፈውን ይመለከታል።

4. ለንጉሥ ለምን እንደማይሰግድ በተደጋጋሚ ለተጠየቀው የሰጠው መልስ

«ወበሳኒታ አዘዘ ያቅርብዎሙ፤ ወይቤሎ ለአቡነ ቅዱስ ስግድ ለንጉሥ፤ ወይቤሎ ብፁዕ አበይኩከ። ... ምንትኑዝ ትዕቢትከ ወትምክሕትከ፤ ... አኮኑ ቀደምትኒ ገብርዎ ለዝአ፥ ወአብርሃምሰ ሰገደ ለደቂቀ ኤሞርአ፤ ወያዕቆብኒ ለዔሳውአ፤ ወዓዲ ካልአንኒ ብዙኃን ገብርዎ ... ምንትኑዝ ኩሉ ጽድቃሙ ነገርአ፤ ከመሰለ ገብርዎ ብዙኃንአ። እስመ እምግባሮሙ ለብዙኃን ይጌይስ ስምዐ ቃሉ ለእግዚአብሔርአ። ዘይቤ ሰማይ ወምድር የጎልፍ ወቃልየሰ ኢያጎልፍ። በማንስቱ (አባ እስጢፋኖስንና ጓደኛውን) ያቀርቧቸው ዘንድ አዘዘ። አባ እስጢፋኖስንም ለንጉሥ ስገድ አሉት፤ እርሱ ግን አሻፈረኝ አለ። ... ይህ ትዕቢትህ፥ ይህስ ትምክህትህ ምንድር ነው? የድሮ ሰዎች ለሰው ሰግደዋል፤ ይሽውም አብርሃም ለኤሞር ልጆች፥ (የኪጢ ልጆች ዘፍ. 23፥7፤ 12) ያዕቆብም ለዔሳው (ዘፍ. 33፥3) ሰግደዋል ...። እያለ ንጉሡ በተናገረ ጊዜ እስጢፋኖስ ሲመልስ፥ ብዙ ሰዎች ለሰው ሰግደዋል የሚለው የነገር ጋጋታ ምንድር ነው? የብዙዎችን ሥራ ከመጥቀስ ይልቅ፥ ሰማይና ምድር ያልፋል፤ ቃሌ ግን አያልፍም ሲል የተናገረውን የእግዚአብሔርን የቃሉን ምስክርነት መስማትና መታዘዝ ይበልጣልኮ» ሲል መሰከረለት።

አባ እስጢፋኖስ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ለቃሉም ከፍተኛ የሆነ ልባዊ አክብሮትን የሰጠ ትሑት አገልጋይ መሆኑን ከሚሰጣቸው መልሶች መረዳት ይቻላል። እዝነ ልቡናው ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ የተከፈተ፥ ለሰማውም ድምፁ ሁለንተናውን ያስገዛ አገልጋይ ነበር።

እንደ አባ እስጢፋኖስ መረዳት፥ እግዚአብሔር አምላክ «ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል» ብሎ ከማለ በሰማይም ሆነ በምድር ላለ ፍጥረት፥ እንደዚሁም በሰው ለተሠራ ሥዕልም ሆነ ምስል፥ በተጨማሪም እነዚህን ለሚሠራ ሰው አይሰገድም፤ ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ማለት ነበረ። ኢሳ. 45፥23፤ ሉቃ. 4፥8፤ ሮሚ 14፥11።

አማኝም ሆነ አረማዊ፥ እግዚአብሔር ለእኔ ብቻ ይገባኛል ያለውን ስግደት ለፍጡራን ቢሰጥ የእግዚአብሔርን ሕግ እንደ ጣሰ ይቈጠራል እንጂ፥ የሰዎች ሕግ አፍራሽነት የእግዚአብሔርን ሕግ ለመሻር እንደ ተፈቀደ አብነት ተደርጎ አይወሰድም። በሥራ ላይ የዋለ ሕግ፥ ሕግን የማውጣት ሥልጣን ያለው አካል በሚያወጣው ተለዋጭ ሕግ ብቻ ይሻራል። በምድራዊ መንግሥት የወጣውን ሕግ፥ ለሕጉ መገዛት የሚገባው አንድ ባለሥልጣን በድርጊት ሽሮት ቢገኝ፥ ሕጉ በተለዋጭ ሕግ እንደ ተሻረ አይቈጠርም። የባለሥልጣኑ ሕግ

ወደ 7ጽ31 ዞሯል

ነህምያና የሐድሶ አገልግሎቱ

እንደ ሜዳ ውሃ ሁሉ ጸጥ ብሎ የሚጓዝ ምንም ቢመስል፥ ሁኔታው መምሰል እንጂ እውነታነት የለውም። እርሻ ሲያረጅ መጭ ይበቅልበታል፤ ቤተ ክርስቲያን ስታረጅ ድንዛዜ ይሠለጥንባታል፥ አምልኮዋ ወግ ብቻ፥ ኃይል አልባም ይሆናል፥ ኑፋቄም ሲወርሳት የግትከላከል አሮጊት ትሆናለች። የምእመን ሕይወትም ሲያረጅ ኃጢአትን የማይቃወም፥ በዝንቦች የሚጠቃ አንበሳን ይመስላል። ይህ እንዳይሆን ከእያንዳንዱ ምእመን ጀምሮ እስከ ታላቁ ጉባኤ ምእመናን (ቤተ ክርስቲያን) ድረስ ያለው ሁሉ በየደረጃው በየጊዜው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሚሰበክ ሕያው ቃለ ወንጌል ሊቀሰቀስ፥ በድካምና በስሕተት ትምህርት፥ እንዲሁም በኀጢአት ምክንያት ከሚመጣ እድፈትና እርጅና ሊታጠብና ሊታደስ ያስፈልገዋል።

ክርስትናን «ተጠምቀህ ነበር»። በመባሉ ብቻ የሚያውቅ አንድ ሰው «ቤተ ክርስቲያንህን ለምን እንደምትወዳት ግለጽ» ተብሎ ተጠየቀ፤ ሲመልስም «አገልጋዮቿ (ካህናት) እኔ የማደርገውን ሁሉ ሰለሚያደርጉና ተው ስለማይሉኝ ነው» አለ። የተራ ምእመንና የካህናት ሕይወት እኩል ዐረም በትሉበታል ማለት ነው። ኀጢአት ባለበት ሞት አለና፥ ጠቅላላው ጉባኤ ምእመናን (ቤተ ክርስቲያን) ሞት አንጎርፀበታል ማለት ይቻላል። ይህ እንዳይሆን የእግዚአብሔር ቃል «ወግበሩ ለክሙ ልበ ሐዲሰ፥ ወመንፈሰ ሐዲሰ! ወለምንት ትመውቱ ቤተ እስራኤል። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በንስሐ መታደስ እያለ ለምን በኀጢአት የተበከለ ሕይወት ይዛችሁ ትሞታላችሁ? ዐዲስ ልብና ዐዲስ መንፈስ ይኑራችሁ»(ሕዝ. 18፥31፤ መዝ. 51፥10፤ ኤፌ. 4፥22-24) ይላልና ለግልም ሆነ ለወል የሕይወትን ተሐድሶ አስፈላጊነት ከነህምያ አገልግሎት መረዳት ይቻላል።

ነህምያ ጠንካራ መሪ

ነህምያ ኩበሉይ ኪዳን ታላላቅ ሰዎች አንዱ ነው። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ አምልኮትና ጉበረተሰብ መመሥረቱ ይታመታል፤ ቀደም ሲል የነበረው ሁሉ ከፈራረሰ በኋላ ነህምያ እንደገና አደሰው።

ስለ ነህምያ የምናውቀውን ሁሉ የምናገኘው ነህምያ ራሱ ከጻፈው መጽሐፍ ብቻ ነው። ቅድመ አያቱ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን የተማረከ፥ አባቱም ሐኖልያ ከባቢሎን ወደ ሱሳ የሔደ ይመስላል። በዚያም ነህምያ ከአናኒና ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር አድጎ የንጉሥ አርጤክስስ ጠጅ አሳላፊ ሆነ።

ነህምያም ይህን ሥራ እንዴት እንዳገኘ ባናውቅም ሥራው የንጉሡ ጠጅ ጣፋጭና መርዝ የሌለበት መሆኑን ግረጋገጥ ነበረ፤ ምክንያቱም በዚያ ዘመን ሰዎች ጠላቶቻቸውን ለመግደል የሚጠቀሙት ብዙውን ጊዜ መርዝ በመጠጥ ውስጥ በመጨመር ስለነበረ ነው። ስለዚህ ነገሥታት ለዚህ ሥራ ፍጹም ታማኝና ታዛዥ ሰዎች መፈለግ ነበረባቸው። ምናልባት ነህምያ ለዚህ ተግባር የተመረጠው የሰው አገር ሰው ስለነበረ ሳይሆን አይቀርም።

ምግብ፥ ልብስና ሌላ ነገር እንደ ልብ ስለሚገኝ ጠጅ አሳላፊ መሆን ጥሩ ሥራ ነበረ። ይህ ዓይነቱ ተግባር አደገኝነትም አለው፤ ምክንያቱም ሠራተኛው ንጉሡን ቢያሳዝን እንደ ፈርዖን ጠጅ አሳላፊና እንጀራ አበዛ ወዲያው ሊታሰርና ሊገደል ይችላልና ነው። በብዙ ረገድ ሲታይ ዋስትና ያለው ጎላፊነት አልነበረም፤ ዘፍ. 40።

ነህምያ በዚህ ሥራ ሲኖር ምን ተሰምቶት ይሆን? ከአይሁድ ወገን በመወለዱ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ መሆኑንና ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ዐውቆ አመለከው። በፋርስ መንግሥት ግን ብዙ አማልክት ስለሚመለኩ፥ በግብዣ የሚበላ ምግብና መጠጥ ለእነዚህ አማልክት ይቀርብ ነበር። ነህምያ በዚህ ዓይነቱ ግብዣ ባይሳተፍም ባዕድ አምልኮት በሚካሔድበት አገር ውስጥ በመኖሩ አዘነ፤ ሆኖም ሁኔታውን የመለወጥ ችሎታ አልነበረውም።

የነህምያ ልብ በሱሳ አልነበረም። የእስራኤል ሕዝብ በኀጢአት ምክንያት እንደተማረከ አስተዋለ፤ ደግሞም ስለ ዘሩባቤል፥ ስለ ንግሥት አስቴርና እንደዚሁም ከ13 ዓመት በፊት እነዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት እንደሄዱ የሚያስረዳውን ታሪክ ዐወቀ። ከዚህም የተነሣ ወንድሙ አናኒና ሌሎች ወንድሞቹ ከኢየሩሳሌም መምጣታቸውን ሲሰማና ከቤት ወጥቶ ሲቀበላቸው፥ ቤት ከመግባታቸው በፊት ገና ከእነርሱ ጋር ሲገናኝ ወዲያውኑ «የዳኑት ከምርኮ የተረፉት አይሁድና የኢየሩሳሌምም ነገር እንዴት ነው?» ብሎ በመጠየቁ በልቡ ውስጥ ይብላላ የነበረውን ዋና አሳብ ገለጠ። ከእነርሱም በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ በችግርና በኀፍረት ላይ መሆናቸውን፥ የከተማይቱ ቅጥሮች ፈራርሰው መውደቃቸውንና የቅጥሮችም በሮች መቃጠላቸውን ሲሰማ ወደ ቤቱ ገብቶ ተቀመጠ፤ አለቀሰም። ይህ ድንገተኛና ጊዜያዊ ሐዘን ሳይሆን ሕይወቱን ሁሉ የነካ በመሆኑ ለብዙ ቀናት ጸመ፥ ጸለየም፤ ነህ. 1፥1-4።

1. ነህምያ ጥሪውን ተቀበለ።

ሲጾምና ሲጸልይ ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ይሁዳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከበፊቱ ይልቅ የበለጠ ተረዳ። በዚህም ሂደት ውስጥ ለእርሱ የተመደበው የግል ድርሻ ተገለጠለት። ሰው በራሱ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲያስተውል በዚህ ውስጥ ሦስት ክፍሎች እንዳሉ መረዳት ይችላል።

1ኛው በአንድ ነገር ላይ ከባድ ሸክም መኖሩ

2ኛው ይህን ሸክም ለማቃለል የራሱን ጥሪና ድርሻ መቀበሉ

3ኛው በሥራው ሂደት ሊደርስበት የሚፈልገው ግብ መኖሩ ናቸው።

ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እነዚህን ነገሮች አጠቃልለው ለመግለጽ ሲፈልጉ «ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል» ከሚለው በመነሣት «ራእይ» ብለው ይጠሩአቸዋል፤ ምሳ. 29፥18። አሳባቸው የሚደገፍ ቢሆንም ራእይ «እይታ» የሚል ትርጉም ስላለው ይህን አሳብ አሟልቶ ለመግለጽ ብቃት ያለው ቃል አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ። የነህምያን ታሪክ ስንፈትሽ በእርሱ ላይ ከባድ ሸክም እንደነበረበት አይተናል፤ የራሱን ጥሪና ድርሻ በሕይወቱ ሲገልጥና በሥራውም ያቀደውን ውጤት ለማግኘት ጥረት ሲያደርግ እንመለከታለን።

ነህምያ ስለ ጥሪው ሲያሰላስል በተለይ ሁለት ታላላቅ ችግሮች ሳያስጨንቁት አልቀሩም። አንደኛው ከጥቂት ዓመታት በፊት ንጉሥ አርጤክስስ የኢየሩሳሌም ቅጥር እንዳይጠገን በጥብቅ መከልከሉ ነበር፤ ዕዝ. 4፥7-23። ሁለተኛው ደግሞ እርሱ የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ ቢሆንም ስለ ኢየሩሳሌም ይቅርና ስለ ማናቸውም ነገር ለንጉሥ መናገር ሙብት ያልነበረው ሰው መሆኑ ነው፤ ምክንያቱም ጥብቅ በነበረው የፋርስ ባህልና ሕግ መሠረት ንጉሡ ካልፈቀደ በስተቀር ማንም ሰው ለንጉሥ አቤቱታ ማቅረብ አይችልም ነበር። ንግሥት አስቴር እንኳን ለአርጤክስስ አባት ለመናገር። «ብጠፋም እጠፋለሁ» ብላ በመሄድ ሕይወቷን በሞት አደጋ ላይ ጥላ እንደነበረ ስንመለከት (አስ. 4፥11-16)፥ ለጠጅ አሳላፊው ነህምያ ንጉሡን ማነጋገር ምን ያህል ሊከብድበት እንደሚችል መገመት አዳጋች አይደለም። ሆኖም በጉዳዩ ላይ ሲያሰላስልበትና ሲጸልይበት ሳለ፥ ለንጉሡ መናገር እንደሚችል በልቡ ወሰቀ፤ ለእምነት ጓደኞቹም መንገድ ይከፈትለት ዘንድ አብረው እንዲጸልዩ ጥሪውን በስውር ነገራቸው።

ነህምያ ከካሴሉ (ከታሕሣሥ) ወር እስከ ኒሳን (ሚያዝያ) ወር ጸለየ። በዚህ ጊዜ ያቀረበው ጸሎት ዋና ይዘትና መንፈስ በ1፥4-11 ተገልጧል። ይህም ጸሎት ስለ አንድ ከባድ ነገር ለሚጸልይ ሰው ሁሉ ጥሩ መመሪያ ነው። የነህምያን ጸሎት በአራት ክፍሎች ልንመረምረው እንችላለን።

ሀ) ውዳሴ፤ ቍ. 5። መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ስፍራ፥ ባሕርይና ሕዝብ ከፍ ከፍ አደረገ። እግዚአብሔር «በሰማይ» በመሆኑ ከሁሉ በላይ ነው፤ ስለሆነም ታላቅና የተፈራ ቃል ኪዳንን የሚጠብቅና መሐሪ ነው፤ ሕዝቡም የሚወዱትና ትእዛዙን የሚጠብቁ ናቸው።

ለ) ንስሐ ቍ. 6-7። ንስሐ ቀላል ነገር አይደለም። ነህምያም ይህን በሚገባ በመረዳት እግዚአብሔር ጸሎቱን እንዲቀበል «አምላክ ሆይ» (ቍ. 5) «ትሰማ ዘንድ ጆሮህ ያድምጥ፥ ዓይናችህም ይከፈቱ» (6)፥ «እባክህ አስብ» (9)፥ «ጌታ ሆይ፥ ጆሮህ ... ያድምጥ» (11) እና ዛሬም አከናውንለት ... ምሕረትን ሰጠው» (11) በማለት እየነዘነዘ ለመነ። ንስሐም ሲገባ «እኔና የአባቴ ቤት»፥ «እኛ» በማለቱ ራሱን ከሕዝቡ ጋር አንድ አደረገ፤

ደግሞም በአጠቃላይ አቀራረብ «ጎጢአትን ሠርተናል» ብሎ ንስሐውን በመቀጠል «ለሙሴ ያዘዝኸውን ትእዛዝና ሥርዓት ሕግም» በማለቱ ድርጊታቸውን አንድ በአንድ ዘረዘረ። ነህምያ የሕዝቡ ኃጢአት ከባድ መሆኑን መረዳቱ በሦስት ተጨማሪ ነጥቦች ይታያል።

1ኛ እርሱና የአስራኤል ልጆች የእግዚአብሔር ባሪያዎች መሆናቸውን ተገነዘበ። እውነተኛ ባሪያ ወደ ሌላ ሳይመለከት ሁሉን ከጌታው ይቀበላል፤ ሁልንተናውንም ለጌታው ይሰጣል፤ ስለዚህ ጎጢአታቸው ከፍ ያለ ጎጢአት ነበረ።

2ኛ ክፋትን የሠሩት «በአንተ ላይ» ነው በማለት በእግዚአብሔር ላይ መሆኑን ተረዳ። በደላቸው በሌሎች ሰዎች ላይ ወይም ራሳቸውን ለመጉዳት ሳይሆን ቃል ኪዳን በሰጣቸው፥ ምሕረት ባሳያቸውና በወደዳቸው እምላክ ላይ የተፈጸመ በደል ነበረ፤ ይህም ጎጢአት ታላቅ ጠንቅ ነው።

3ኛ ነህምያ የሕዝቡንና የራሱን ጎጢአት ሲናዘዝ በምንም ለማመካኘት አልሞከረም።

ሐ. የልመናው ምክንያት ቁ. 8-11። ነህምያ፥ እግዚአብሔር ጸሎቱን እንዲሰማው ሦስት ምክንያቶችን አቅርቧል።

1ኛ. እግዚአብሔር ትልቅ የተስፋ ቃል ለሕዝቡ ሰጥቶ ነበር፤ ይኸውም የተስፋ ቃል የእስራኤልን ሕዝብ በጎጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ሲበትናቸው፥ እነርሱ ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱና ትእዛዙን ቢጠብቁ እርሱ ወደ መረጠው ስፍራ (ወደ ኢየሩሳሌም) እንደሚሰበስባቸው የገባላቸው ተስፋ ነበር። የተስፋ ቃል በጸሎታችን ውስጥ ሊጠቀስ የሚገባው ትልቅ ምክንያት ነው፤ በተለይም የተስፋው ቃል የተመረኰዘበት ነገር በመፈጸም ላይ ሲገኝ ይህ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

2ኛ. በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ እግዚአብሔር ቢታላት ኃይልና በብርቱ እጅ ከምርኩ የዋጃቸው የራሱ ሕዝብ ነበሩ። እነርሱም ከዓለም ሕዝቦች መካከል እንደ አንድ ተራ ሕዝብ ሳይሆኑ፥ ልዩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸው፤ እግዚአብሔር ከዓለም ሕዝቦች ሁሉ ለራሱ መረጣቸው፤ ቃል ኪዳንን ሰጣቸው፤ አሁንም ከባርነት አወጣቸው፤ ስለዚህ በመከራና በውርደት ላይ ሆነው እንዴት ይተዋቸዋል?

3ኛ. አሁን የሚጸልዩት እግዚአብሔርን የሚፈሩና የሚወዱ ናቸው፤ ስለዚህ የጸሎታቸውን መልስ ይጠባበቃሉ።

መ. የጸሎቱ ዋና ዓላማ፤ ቁ. 11 ነህምያ ለንጉሡ ለመናገር በር እንዲከፈትለትና ንጉሡም አቤቱታውን እንዲቀበለው ምሕረት ጠየቀ። እግዚአብሔርን እያሰበ ታላቁ ንጉሥ አርጤክስስ በአምላኩ ፊት «ሰው» ብቻ መሆኑን ተረዳ። እንደዚሁም ለጸሎቱ መልስ በቶሎ እንዲሰጠው «ዛሬም» ብሎ ለመነ።

ከጸለየ በኋላም እንደልማዱ ወደ ሥራው ሄደ፤ እስከ አራት ወር ድረስ መልስ አላገኘም። ልመናውን ግን አልተወም፤ ይዘቱንም አልለወጠውም። እግዚአብሔር ከመጀመሪያ ጀምሮ እውነተኛ ጸሎትን ይሰማል፤ መልስ የሚዘገይበት ምክንያት ግን በእርሱ ምስጢርና ጥበብ ውስጥ ተሰውሯል።

የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ ነህምያ ጠጅ ሲያቀርብ ሳለ ንጉሡ በነህምያ ፊት ላይ ለውጥ አየ። ሠራተኞች ሁሉ ንጉሡን በደስታ መልክ ማገልገል ነበረባቸው። ምንም እንኳን ነህምያ ጢም ሊኖረው የሚችል ሰው ቢሆንም ከሐዘኑና ከጸሙ ብዛት የተነሣ ፊቱ የልቡን ስሜት ገለጠበት። ንጉሡ «ሳትታመም ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብ ሐዘን ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም» ሲለው ነህምያ እጅግ ፈራ። ፍርሃቱም ስለራሱ ብቻ ሳይሆን ስለ ተልእኮው ከንግዴ ነበረ። ቢፈራም «ንጉሥ ሺህ ዓመት ይንገሥ፤ የአባቶቼ መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለችና፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለምን አይዘን?» ብሎ በአክብሮትና በድፍረት ለንጉሡ መልስ ሰጠ። ከዚህም ቀጥሎ ንጉሡ «ምን ትለምነኛለህ?» ብሎ በመጠየቁ አራት ወር ሙሉ ያቀረበው የጸሎቱ ውጤት ታየ። ነህምያ መልስ ከመስጠቱ በፊት ልቡን ወደ አምላኩ አነሣ። በኋላም እንደገና አቤቱታውን አቀረበ፤ «ንጉሡን ደስ ቢያሰኘህ ባሪያህም በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ እሠራው ዘንድ ወደ ይሁዳ ወደ አባቶቼ መቃብር ከተማ ስደደኝ» በማለት አቤቱታውን በአክብሮት አቀረበ።

ንጉሥ አርጤክስስ ከሰባቱ አማካሪዎች ጋር ከተነጋገረ በኋላ ከንግሥቲቱ ጋር በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ። እንዳንዶች የዓለምን ታሪክ ከመመርመር የተነሣ ይህች ንግሥት የአርጤክስስ እናት አስጢን እንደነበረችው ያምናሉ። የእርሷ መገኘት ለነህምያ ጥሩ ምልክት ነበርና ንጉሡ «መንገድህ እስከ መቼ ድረስ ይሆናል? መቼስ ትመለሳለህ?» ብሎ ጠየቀው። ነህምያ ቀጠረለት፤ ለሥራውም አስፈላጊ ደብዳቤዎች እንዲጻፉለት ጠየቀ። የእግዚአብሔር እጅ በነህምያ ላይ ስለነበረ ከንጉሡ የፈለገውን አገኘ። ከዚህም ላይ ነህምያ ስለ ሥራው በዝርዝር ያስብ እንደነበረ ይታያል፤ በዚህም፥ እምነቱ ተገልጧል፤ ነህ. 2፥1-8።

ከዚህ ታሪክ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ስለግወቅና በዕቅዱ ውስጥ የእኛን ሥራ ስለግስተዋል ምን እንግራለን? በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጧል። ሆኖም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ሁኔታ ወይም ከዓለም ሁኔታ የተነሣ ከአጠቃላይ የእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር የሚስማማ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን፥ ለአገራችንና ለዘመናችን አሳብ ሊሰጠን ይችላል። የነህምያ አሳብና ምኞት በኢየሩሳሌም የሚያተኩር ነበር፤ ስለዚህ ወንድሙ ከይሁዳ ሲመጣ ልዩ ሸክም አደረበት፤ ጥሪውን ተቀብሎ ድርሻውን በማወቁ ሥራውን ለመጀመር ተነሣ።

ክርስቲያን «ራእዩንና በራእዩ ውስጥ» ሊኖረው የሚገባውን የራሱን ድርሻ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? አንድ መኪና ለማሽከርከር ስንፈልግ አደጋ እንዳያጋጥመን ሕጉን ማክበር ያስፈልጋል። በአዲስ አበባ የመኪናዎችን አካሄድ የሚቈጣጠሩ ብዙ መብራቶች አሉ። ቀይ መብራት ሲበራ ነጂው መኪናውን ማቆም አለበት፤ አረንጓዴ መብራት ሲታይ ግን መኪናውን ወደ ፊት ያለ ፍርሃት መንዳት ይችላል። ስለ አንድ ትልቅ ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ስንፈልግ በመንገዳችን ላይ አምስት «መብራቶች» ይኖራሉ። **ግናቸውም መብራት «አረንጓዴ» እስኪሆን ድረስ ወደፊት መጓዝ የለብንም።**

አንደኛው «መብራት» የእግዚአብሔር ዕውቀት ነው። ነህምያ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑን ወቀቀ፤ በዚህም ተደስቶ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ፈለገ። መምህር አልነበረም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ያውቅ ነበር፤ የእግዚአብሔርን አጠቃላይ አስተዳደርና አሠራር ከሕዝቡ ታሪክ ተረድቷል። ስለዚህ የኢየሩሳሌም እንደገና መታደስ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንደሚስማማ ወቀቀ። እግዚአብሔር አይለወጥም። በቃሉ አንድ ነገር ከገለጠ፥ ያንኑ በሚቃረን መንገድ ሰውን አይመራም። እንግዲህ ክርስቲያን ስለ ጋብቻ፥ ስለ ሥራ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ወንጌል ሥርጭት ወይም ስለሌላ ታላቅ ነገር አንድ አሳብ ቢያገኝና እንደዚሁም ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ካለው ዕውቀት ጋር ባይስማማ ወደ ሁለተኛው መብራት መሄድ አይገባውም። ቢስማማ ግን መብራቱ አረንጓዴ ነውና በጥንቃቄ ወደፊት መሄድ ይችላል።

ሁለተኛው መብራት የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው። እግዚአብሔር ለነህምያ በራእይ፥ በሕልም፥ በነቢይ፥ በመልአክ ወይም በመገለጥ ቃል አልተናገረም፤ ነገር ግን በልቡ የእግዚአብሔርን ጥሪ ወቀቀ። ምን ማድረግ እንደሚገባውም ተገነዘበ፤ ከባድ ሸክምም አደረበት። ዛሬም ብዙ ጊዜ እንደዚህ ሲሆን ይታያል። መንፈስ ቅዱስ በተለየ መንገድ ፈቃዱን ሊገልጥልን ቢችልም፥ ብዙ ጊዜ የእማኙን አሳብና መንፈስ በመቃኘት የእግዚአብሔርን ሥራና በሥራው ውስጥ ያለንን ድርሻ ያሳየናል። አማኙ በውስጡ ሸክም ይኖረዋል፤ ከሸክሙም አይላቀቅም። ብዙ ነገር ግልጥ ባይሆንለትም የሕይወቱን አቅጣጫ ግን ያውቃል። መብራቱ አረንጓዴ ሲሆን ወደ ሦስተኛው መብራት መሄድ ይችላል።

ሦስተኛው መብራት የምእመናን ስምምነት ነው። ነህምያ ከቅርብ ጓደኞቹ ጋር በአንድነት ሲጸልይ አሳባቸው አንድ ነበረ። የእግዚአብሔር ሰው ብቻውን ሆኖ እንዲሠራ አልተጠራም። ስለዚህ ክርስቲያን ጥሪ የተቀበለ መሆኑን ሲረዳ ከቤተ ክርስቲያን ጋር መማከር ይገባዋል። መንፈሳዊ መሪዎቹ ከአሳቡ ጋር ባይስማሙ መብራቱ ቀይ ነው። ምናልባት አሳቡ ከራሱ የመነጨ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ጊዜ ገና ነው። ሌሎች በአሳቡ ሲስማሙበት ግን መብራቱ አረንጓዴ ስለሚሆን ወደ አራተኛው መብራት መሄድ ይገባዋል።

ወደ 20 ገጽ ዞሯል፤

ጥያቄ አለኝ፣ ይመለስልኝ

በሙሉ መጽሔት ውስጥ በተገለጡ ሐሳቦች ላይ የተመሠረቱ የቤተ ክርስቲያናችንንም አስተምህሮ ለመረዳት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የዝግጅቱ ኮሚቴ በትምህርት ሰጪነታቸው ሲያምንባቸው፣ በዚህ ዓምድ መልስ ያገኛሉ።

¤ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሥራች በመባል የሚታወቀው ዲዮስቆሮስ። ... የእኔ እምነት ቀጥተኛ ወዘተ ብሎ ከመውጣት ለምን ... እዚያው አልቁየም? ዘመኑ ከመርዘሙ የተነሣ የተረሳ መስሎአቸሁ ነው? - አበራ ከበደ

ኦርቶዶክስ ሁለት ቃላት የተገናኙበት በዐጭሩ «ርትዕት ሃይማኖት» ተብሎ በግእዝ የተተረጐመ የግሪክ ቃል ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ቃሉን የተጠቀመበት 318 ሊቃውንት በ325 ዓ.ም. በኒቅያ በተሰበሰቡበት ጊዜ ነው። (መጽሐፈ ሰዋሰው ወግሥ ገጽ 384)።

የኒቅያ ጉባኤ እየተካሔደ ባለበትም ጊዜ መንጌል በኢትዮጵያ በመሰበክ ላይ ነበረ። ሰዉኪው ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ እየተካሔደ ያለውን የወንጌል ሁኔታ ለማስታወቅ እስክንድርያ ሲደርስ፥ ከኒቅያ ጉባኤ መልስ አትናቴዎስ 20ኛ ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ አገኘው።ከእርሱም ኤጲስ ቆጶስነትን ከተቀበለ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን አቋቋመ። ወንድም አበራ እርስዎ የጠቀሱት ዲዮስቆሮስ ግን 25ኛ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ነበረ። ከእርሱ በፊት ግልት 120 ዓመት አስቀድሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተቋቁማ ነበር።

ዲዮስቆሮስም የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ በሚመለከት በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን ወክሎ ተካፈለ፤ ከሲኖዶሱ አባላት መካከልም የእርሱን መግለጫ ያለ መቀበል አዝማሚያ ባሳዩት ጊዜ ዲዮስቆሮስ እኔ በቀደሙት አባቶቼ ከተሰበከው ያልተለወጠ «ኦርቶዶክስ» ነኝ አለ። ጉባኤውም በስምምነት ሊቀጥል ባለመቻሉ በሁለት ተከፈለ፤ ካቶሊክና ኦርቶዶክስ ተብሉ።

ኦርቶዶክሳዊ ዲዮስቆሮስና ሌሎች የሐሳቡ ደጋፊዎች ወደየነበሩበት ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ። አንዲት ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን አመራር ሰጪ የነበረው ሲኖዶስ ከሁለት ላይ ከመከፈሉ በስተቀር የወጣና ያስወጣ አልነበረም። ካቶሊካዊው የሮም መንግሥት የጦር ኃይል በመጠቀም ዲዮስቆሮስንና ተከታዮቹን ከየመንበራቸው ለማስወገድ ሞክሮ ብዙ ደም ቢያስፈስስም የዲዮስቆሮስን የእምነት መግለጫ የተቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉም ያን ጊዜ እንደነበሩ ዛሬም አሉ።

እርስዎ ስላነሡት እውነቱን መናገር ግዴታ ሆነና ነው እንጂ በበኩላችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ዐዲስ ፍጥረት ከተደረግንበት መንፈሳዊ ታሪክ ጋር ያልተያያዘውን ልናነሣው ባልፈቀድን ነበር። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ እርስዎ ይበልጣሉ ካሏቸው ባዕዳን በታሪክ የሚያስበልጠንን በተረከን ነበር።

¤ የጥምቀት ሥርዓት ጎጢአትን ከማስተስረይ ጋር የተያያዘ ነው ብላችኋል፤ እንድታብራሩልኝ። ስሜ ታደሰ

በክርስቶስ ቤዛ መሆንና በእግዚአብሔር ጸጋ የተገኘውን ሰውም በእምነት የሚቀበለውን የኀጢአት ስርየት ጥምቀት ይተካዋል አልተባለም፤ ግን «የተያያዘ ነው» ተብሏል። ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳውም፤

- የዮሐንስ ጥምቀት ከኀጢአት ስርየት ጋር ተያይዞ ተሰብኮ ነበር። ሉቃ. 3፥3-6
- ጥምቀተ ክርስትናም እንደዚሁ ከኀጢአት ስርየት ጋር ተያይዞ ተሰብኳል። ሐዋ. 2፥38፤ 22፥16። እንዲት እንደሚያያዝም በሮሬ ቍ. 18 ከገጽ 28 ጀምሮ ያለውን ይመልከቱ።

¤ እዚያ ያለውስ ቁስ ዳግም ለመወለዱ ምን ማረጋገጫ አለው? ላላችሁት፥ ዳግም ቢወለድ እኮ ነው ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የወጣው። አበራ ከበደ

ይህ መስፈሪያ የርስዎ ብቻ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ከቤተ ክርስቲያናችን ፈልሰው ወደ እስልምና፥ ወደ አርዮሳዊነት ወዘተ. ካምፕ የገቡም በስነ ሥርዓት ጉድለትም የሚወገዱ አሉኮ፤ ፍልሰት የዳግም ልደት ምልክት ነው ያለች ቤተ ክርስቲያን እስካሁን የለችም። ከብዙ ነባር አብያተ ክርስቲያናት እየፈለሱ ዐዲስ ወደ ተከፈቱ አብያተ ክርስቲያናት የገቡትንና የሚገቡትን እስኪ በልብዎ ይቍጠሯቸው። ጉዳዩ ከተነሣም ስለፍልሰት በሮሬ ቍጥር 14 ገጽ 22 እና 23 የተጻፈውን ያንብቡ።

¤ ጮራዎች በእውነት ትቀልዳላችሁ እንዴ? አሁን ማን ይሙት፥ የሕይወት ጌታ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ዐውቆ የዳነ ክርስቲያን በኦርቶዶክስ ውስጥ መቈየት ወይም መቀጠል ይችላል? ... እምነቱን ቢናገር የሚጨበጨብለት አይመስለኝም። አበራ ከበደ

እንግዲህ ፍልሰት ያስፈለገው ለማስጨብጨብ ነው ብለው ያምናሉን? እንደ እኛ እምነት፥ ዳንኩ የሚል ሰው፥ እንደ ተናገረው በእውነት የዳነ ከሆነ ግዴታ አለበት፤ ግዴታውም አበጀህ በሚሉ አጨብጫቢዎች መካከል ሆኖ መመስከር ሳይሆን በተቃዋሚዎች መካከል ተገኝቶ መመስከር ነው። ጌታም ያጨበጭቡላችኋል የሚል ተስፋ አልሰጠም፤ (ማቴ. 10፥16-39)። እኛም የምንለው አጨብጫቢ ፍለጋ ፍልሰት ይቅር ነው።

¤ ከመከፋፈላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ። አበራ ከበደ

ጥቅሱ ያለበት ዐውድ በሙሉ ሲነበብ ከማያምኑ ተለዩ የሚል ነው። (2ቆሮ. 6፥14-18) መቼም ቤተ ክርስቲያናችንን በደብዳቤዎ መጀመሪያ ገጽ ላይ እኅት ቤተ ክርስቲያን ነች ብለው አምነዋልና ቃልዎን አጥፈው የማያምኑ የሚለው ጎይለ ቃል ይወክላታል እንደማይሉ ተስፋ አለን። ታዲያ ወንድም አበራ በየትም ቤተ ክርስቲያን ቢሆንኮ ከጅምላው መካከል የዳኑና ያልዳኑ አባላት እንደሚገኙ ልብ ሊሉ ይገባል፤ በምድር ያለችው የእግዚአብሔር መንግሥት በስንዴና በእንክርዳድ የተመሰሉትን ይዛ እስከ መከር (የጌታ መገለጥ) ድረስ ተቋያለችና። አንዳንድ ጊዜ በሰው አመለካከት በእንዳንድ ቦታ እንክርዳዱ የበዛ የሚመስልበት ሁኔታ ያጋጥማል። ቢሆንም የጌታ የሆኑት ትሩፋን (ቅሬታዎች) ያላቸውን መልካም ነገር ይዘው ጌታ እስኪመጣ ድረስ እንዲቈዩ ታዘዋል። መፍለስ ቢያስፈልግማ ኖሮ የትያጥሮንና የሰርዴስ ትሩፋን (ራእ. 2፥24-25፤ 3፥4) የነበሩባቸውን አብያተ ክርስቲያናት እየለቀቁ የተሻሉ መስለው ወደሚታዩ ወደ ኤፌሶን፥ ሰምርኔስ፥ ፊልድልፍያ አብያተ ክርስቲያናት እንዲፈልሱ በታዘዙ (በተመከሩ) ነበር።

¤ መምህርት ሲያዩ ከወጡበት ዘር በዚህች ቤተ ክርስቲያን በአገልጋይነት ሲመረጥ ዐዲስ ነገር ስለመሰለኝ ... እስካሁን ድረስ ከሁለት ዘር በስተቀር ለአገልግሎትም ሆነ ለሹመት ከሌላ ዘር ሲመረጥ ስለአላየን። ... አበራ ከበደ

ወንድም አበራ፥ እስካሁን ድረስ ዳር ዳሩን ሲዞሩ ቈዩ እንጂ ሊሉ የፈለጉት ዋና ነጥብ ይህ ሳይሆን አልቀረም። አዩ! በአሁን ጊዜ ስም ዘርን፥ ጐሣን ያስለያል ተብሎ አይታመንም። ኪኔዲ፥ ቾምቢ፥ ሚካኤል፥ ሣሞራ፥ ኤልሳቤጥ፥ ሜሪ፥ ማሪያ፥ ፍራንሲስ፥ ወዘተ. የሚባሉ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እንዳሉ ሁሉ፥ በሀገር ውስጥም እያንዳንዱ ጐሣ ከሌላው ጐሣ ስም አልወረሰም ለማለት አያስደፍርም። ለመዘርዘር ስፍራ አይበቃምና እንዲያው አካባቢዎች ይመልሱልዎ። ከዚህም በቀር ብዙ አገልጋዮች በክርስትና ወይም በሹመት መጠሪያ ስም ስለሚጠሩ ሁሉም ከአንድ ጐሣ የመጡ መሰለዎ። ሆኖም ቤተ ክርስቲያናችን ዘርንና ነገድን ሁሉ ያቀፈች ናት እንጂ በአንድ ወይም በሁለት ዘሮች፥ ወይም ጐሣዎች የተወሰነች አይደለችም። ግን ይህን የመከፋፈያ ነጥብ ባይጠቀሙበትስ?

¤ ፈረንጆች በሁሉም መስክ ከእኛ የተሻሉ ሕዝቦች እንደሆኑ አታውቁም እንዴ? አበራ ከበደ።

እኛ የሚለውን ቃል አውጥተው ስለራስዎ ብቻ ቢናገሩ እንኳ እንቃወማለን፤ ምንም እርስዎ የገለጿቸው ውሾች ላበሷቸው መጮኻቸው እውነት ቢሆንም፥ የምንነጋገረው ስለመንፈሳዊው ጉዳይ ነውና፥ ሰው ሁሉ፥ ከጥንትም የአንዱ የቀዳማዊ አዳም ልጅ ነው። አሁንም በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ ዐዲስ ፍጥረት ለመሆን በወንጌል ያልተጠራ ዘር፥ ነገድና ቋንቋ የለም ብለን እናምናለን።

ክርስቲያናዊ ምግባር

ከደምፀ ቃለ አብ

(ካለፈው የቀጠለ)

በዘመነ ሐዋርያት እንደነበሩት አይሁድ፥ ዛሬም በጽድቀ አሪትና በጽድቀ እግዚአብሔር መካከል ያለውን ልዩነት የማይረዱ ብዙ ናቸው። እነዚህ ሰዎች፥ ሕገ አሪት በታወጀበት ጊዜ የነበረውን የሰውን የመንፈስ ውድቀት፥ እንዲሁም የታወጀው ሕገ አሪት የወደቀውን ሰው ለማንሣት የፈጸመው ርዳታና በጎ አድራጎት አለመኖሩን የመረዳት ችሎታና ፈቃድ አይታይባቸውም። ባለፈው እትም «በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል» (ሮሜ 3፥21) በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንዴት እንደተገለጠና ኃጢአተኛውም ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ የተገለጠውን **የእግዚአብሔር ጽድቅ እንዴት እንደሚተበለው** ተመልክተናል። **በዛሬው እትምም «በእግዚአብሔር ጽድቅ»** ተጠቃሚ የመሆን ዕድልን ያገኘው ምእመን የወደፊት ኑሮው እንዴት መመራት እንዳለበት ይገልጻል።

ሕገ አሪት በታወጀበት ጊዜ የሰው ሁኔታ

ሕገ አሪት በታወጀበት ጊዜ የሰው ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበረ ማወቅ ሕጉ ለሰው ያበረከተው መልካም ነገር መኖር አለመኖሩን እንድንረዳ መንገድ ይከፍትልናል። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስጨብጠን እውነት፥ ሰው ከነትውልዱ፥ ከነዘር-ማንዘሩ በኀጢአት ዐዘቅት ውስጥ ከወደቀ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ሕገ አሪት መታወጁን እናውቃለን። የታወጀው ሕገ አሪትም ሰውን ከወደቀበት የኃጢአት ዐዘቅት አውጥቶና ጤነኛ ሰው አድርጎ ከዚህ በኋላ በዚህ መንገድ ተራመድ፥ ይህንንም ሥራ የሚል አልነበረም፤ እንዲያውም በዚያው በነበረበት ዐዘቅት ውስጥ እንዳለ ይህን አድርግ፥ ያንንም አታድርግ በማለት ሕግ ተላላፊውን ሰው የሚከስና እንዲፈረድበት የሚጠይቅ ነበረ። ለምሳሌ ፦-

- ሰው በዔድን ገነት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔርን ብቻ መስማትን፥ ለእርሱም ብቻ መታዘዝን አቋርጦ፥ በባሕርዩ እግዚአብሔር ላልሆነ ለሰይጣን መታዘዝን መረጠ። በዚህም ኃጢአት ተቈጠረበትና ወደቀ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሰው በሚገኝበት ጊዜ የታወጀው ሕገ አሪት ከእግዚአብሔር በቀር ሌሎችን አማልክት እንዳያመልክ፤ አንዱን እግዚአብሔርን ብቻ በፍጹም ልቡ፥ በፍጹም ነፍሱ፥ በፍጹም ኃይሉ እንዲወድ ያዛል፤ ዘጸ. 20፥3፤ ዘዳ. 6፥4-5። ዳሩ ግን ሕገ አሪት ከመታወጁ በፊት ሰው ሕጉን የጣሰ በመሆኑ ከነዘር ማንዘሩ በኃጢአት ዐዘቅት ውስጥ ወድቆ ከፍርድ በታች ሆኖ ነበር።
- ሌላው የሕግ አንቀጽ «አትስረቅ» ይላል። ሰው ግን ገና በዔድን ገነት በነበረበት ጊዜ ካልተፈቀደለት ዛፍ ሰርቆ በልቷል፤ በዚህም ኃጢአት ተቈጠረበትና እርሱና ዘሩ ሁሉ በኃጢአት ተበክለው ከፍርድ በታች ሆነዋል።
- «አትግደል» የሚል አንቀጽም በሕጉ ውስጥ አለ። ሰው ግን ገና በዔድን ገነት በነበረበት ጊዜ ከእርሱ በበላህ ቀን ትሞታለህና ከእርሱ አትብላ የሚለውን ትእዛዝ በመተላለፍ ከተከለከለው ዛፍ ሰርቆ በላ፥ በዚህም ሕግ ተላላፊነቱ ራሱን ገደለ፤ ዘር ማንዘሩንም ገደለ። ስለዚህም ከሞት ፍርድ በታች ሆነ።
- ከተከለከለው ዛፍ ብትበሉ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ያስችላችኋል የሚለውን የሰይጣንን ምክር ሔዋንና አዳም በመቀበላቸውና እንደ እግዚአብሔር ለመሆን በመመኘታቸው ከተከለከለው ዛፍ በሉ። ስለዚህም ገና ከጥንቱ ከጧቱ ምኞትን በልባቸው አስተናግደዋልና ከሞት ፍርድ በታች ሆነዋል።

እንግዲያውስ ሕገ አሪት በታወጀበት ጊዜ የሰው ሁኔታ ይህን ስለሚመስል፥ ሰው ቀደም ሲል **ሕግ አታድርግ ያለውን ስላደረገ ተፈርዶበት ይገኛልና፤** በኃጢአት ዐዘቅት ውስጥ ያለው የሰው ዘር ያደረገውን ኃጢአት «አታድርግ» ቢለው ከሰሰው እንጂ ምንም አልረዳውም። እንዲሁም ባላደረገው መልካም ነገር ኃጢአት ተቈጥሮበት ከፍርድ በታች የሆነውን ሰው «አድርግ» ቢለው ምን ጠቀመው!! ባለማየትም ሆነ ባለመጠንቀቅ ገደል ውስጥ ለገባው ሰው፥ አፋፍ ላይ ቆሞ ዋ! ገደል ውስጥ እንዳትወድቅ፤ እያየህ፥ እየተጠነቀቅህ ሒድ፤ ያህን ባታደርግ ግን ትሰበራለህ፥ አካለ ጐደሎ ትሆናለህ፥ ከገደሉ ውስጥ ወጥተህም ይህንና ያንን ባትሠቃ ትቀጣለህ፤ በመጨረሻም ትሞታለህ ተብሎ ቢነገረው የተባለው ሁሉ እስኪፈጸምበት ከመጠበቅ በቀር በራሱ ምን ሊያደርግ ይችላል?

እንደ እውነቱ ከሆነ ሕገ አሪት የታወጀው ኃጢአት ወደ ዓለም ገብቶ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ በሆነበት ጊዜ እንጂ ሰዎች ገና ቅዱሳን በነበሩበት ጊዜ አልነበረም። ጥፋቱ የሕጉ አይደለም፥ ሕጉ ቅዱስ ቢሆንም ሰዎቹ ርኩሳን ሆነው ከፍርድ በታች ነበሩና እርሱን ሊታዘዙ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ነበሩ። መጽሐፍም «ነአምር ከመ ሠናይ ውእቱ አሪት ለዘይገብሮ በሕጉ ወነአምር ዘኒ ከመ አኮ ለጻድቃን ዘይሠራዕ ዘእንበለ ለኃጥአን፥ ወጽልሕዋን፥ ወለዝሉፋን፥ ወለውፀአን እምጽድቅ፥ ወለርኩሳነ ልብ፥ ወቀተልተ አበዊሆሙ ወእሞሙ፥ ወቀተልተ ነፍስ። ዘማውያን ወእለ የሐውሩ ዲበ ብእሲ፥ ሰረቅተ ሰብእ፥ ሐሳውያን፥ ወእለ ይምሕሉ በሐሰት። ወቦ ባዕድኒ ዓዲ በዘይትቃወምዋ ለትምህርተ ሕይወት። - ሰው በሚገባ ከሠራበት ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን። ሕግ የተሠራው ለደጋግ ሰዎች እንዳልሆነ እናውቃለን። ሕግ የተሠራው ለዐመፀኞችና ለወንጀለኞች፥ ለክሐዲዎችና ለኃጢአተኞች፥ ቅድስና ለሌላቸውና መንፈሳዊ ነገርን ለሚንቁ፥ አባትንና እናትን

ለሚገድሉና ለነፍሰ ገዳዮች፥ ለአመንዝሮችና ግብረ ሥጋን ከወንዶች ጋር ለሚያደርጉ ወንዶች፥ ሰውን ለሚሸጡ ነጋዴዎችና፥ ለውሸተኞች፥ በሐሰት ለሚምሉና የአውነተኛ ትምህርት ተቃራኒ የሆነውን ነገር ሁሉ ለሚያደርጉ ነው» (1ጢሞ. 1፥8-10። የ1980 ትርጉም)።

እንኪያስ ሕግን ማወጅ ለምን አስፈለገ?

ሐኪሙ ዘመዱን ለመጠየቅ ወደ አንድ መንደር ሲገባ፥ በአንጀት ተስቦ የተጠቃ ሰውን አገኘ። መረመረው፥ በሽታው በታማሚው ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ከምርመራው ውጤት ተረዳ። ይህንኑ ለበሽተኛው በዝርዝር አስረዳው፤ ለምን? የበሽታውን ምንነትና የጉዳቱን መጠን ለበሽተኛው እንዲነግረው ያስፈለገበት ምክንያት፥ መጀመሪያ ከደረሰበት አደጋ የመውጣት ፍላጎት እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ቀጥሎም ለመዳን የሚታዘዝለትን መድኃኒት በሙሉ ፈቃደኝነት እንዲወስድ፥ ሦስተኛም ለቀጣይ ሕይወቱ የሚነገረውን ምክር በጥንቃቄ እንዲተበቅ ለማድረግ ነው። እንደዚሁም ሁሉ የሰው ተፈጥሮ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በተበላሸበትና በመረዘው የኃጢአት ቸሽታ ከሞት አፋፍ ላይ በተገኘበት ጊዜ ሕገ አሪትን ያወጀ እግዚአብሔር ሰው በሕገ አሪት እንዲድን ሳይሆን የሚገኝበትን አደገኛ ሁኔታ በትክክል በመረዳት የመዳን ፍላጎትን በሰው ውስጥ ለመፍጠር ነው። መጽሐፍም እንደሚክተለው ይህን ያስረዳል።

«እስመ እምኦሪት ተዐውቀት ኃጢአት። በሕገ ኦሪት ኃጢአት ትታወቃለች» ሮሜ 3፥20።

«እስከ አመ መጽአት ኦሪት ሀለወት ኃጢአት ውስተ ዓለም፤ እንዘ ኢትዐወቅ ምንት ይእቲ፤ እስመ ኢትትኃለቀ ኃጢአት፥ እስመ ዓዲሁ ኢመጽአ ውእተ አሚረ ሕገ ኦሪት። - ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ኃጢአት በዓለም ነበር፤ ይሁን እንጂ ሕግ በሌለበት ኃጢአት ሁሉ እንደ ኃጢአት አይቈጠርም ነበር» ሮሜ 5፥13።

«ለምንት እንከ መጽአት ኦሪት፤ ከመ ታብዝኃ ለኃጢአት»

«ኦሪት ለምን መጣች?» ካለ በኋላ ኃጢአትን በዝርዝር ልታሳውቅ ነው በማለት መልሱን ይሰጣል፤ ገላ. 3፥19፤ ሮሜ 7፥13።

ታዲያ የሚያድነው ማነው?

ይህን ርእስ ባለፈው እትም ሰፋ ባለ ሁኔታ የተመለከትነው መሆኑን እናስታውሳለን፤ በዚህ ቦታ ከሕገ ኦሪት ጥቅም ጋር በማገናዘብ እንድንመረምረው እንደገና ማንሣት አስፈለገ።

ቀደም ሲል የተጠቀምንበትን ምሳሌ ደግመን ብናወሳው፥ በጉድጓድ ውስጥ የገባውን ሰው ለመርዳት ወደ ገባበት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ወይም መሣሪያ በመስደድ ማውጣት፥ ተሰብሮ እንደሆነም መጠገን፥ ቁስሉን ማከም፥ ማጠብና ማንጻት፥ አዲስ ልብስ ማልበስ፥ ወደፊት እንዴት መኖር እንዳለበትም ምክር መለገስ ወዘተ እንደሚያስፈልግ ይታወቃል። ሕገ ኦሪት ግን ይህን ዓይነት ርኅራኄንና በጎነትን ማድረግ አልቻለም። አልቻለምና፥ ለሕገ ኦሪት ያልተቻለውን በማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ለሰው ያከናወነለት የእግዚአብሔር ልጅ ነው። «ወሶበ ተስእኖ ለሕገ ኦሪት ላዕለ ሞት በእንተ ድካመ ሥጋ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ በአምሳለ ነፍስተ ኃጢአት፥ ወኩንና ለይእቲ ኃጢአት በነፍስቱ» ከሰው ባሕርይ ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በመላክ አደረገው፤ ያቺንም ኃጢአት (ሰውን ደካማ ያደረገችውን) በሥጋው ቀጣት በማለት ሐዋርያው ያብራራልናል፤ ሮሜ 8፥3።

የእግዚአብሔር ልጅ አሠራር ከሕገ ኦሪት አሠራር እጅግ የበለጠና የተለየ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ሕገ ኦሪት ወድቆ በጉድጓድ ውስጥ ለሚገኘው ሰው፥ በጉድጓድ አፋፍ ላይ ቆሞ፥ በጥንቃቄ አለመራመድ ወደ ጉድጓድ ውስጥ መውደቅን፥ መሰባበርን፥ መቁሰል መድማትን፥ ከዚያም ሞትን ያስከትላል፥ ከዚያም ከጉድጓድ ወጥቶ ይህንና ያንን አለማድረግ በብርቱ ያስቀጣል የሚል ሰውን ሲመስል፥ የእግዚአብሔር ልጅ አሠራር ግን ከዚህ እጅግ የተለየ ነው። እመር ብሎ ወደ ጉድጓዱ ገብቶ በመቁሰልና በመድማት፥ ሌላውንም ጉዳት ሁሉ እንደተጐጂው ሆኖ ስለ እርሱ በመጐዳት ርዳታ ፈላጊውን ከገባበት ጉድጓድ ማውጣትን፥ ማከምና መፈወስን፥ ለወደፊቱ እንዴት ሆኖ መኖር እንዳለበት መመሪያ መስጠትን አካትቶ የያዘ ነው።

እንደተጻፈውም የእግዚአብሔር ልጅ ርዳታ ፈላጊውን ሰው ለመርዳት ወደሚገኝበት ጉድጓድ ሲመጣ ከኃጢአት በስተቀር ፍጹም ሰው ሆነ (ዕብ. 4፥15)። ፍጹም ሰው በመሆኑም የሰው ተለዋጭ ሆኖ ኃጢአቱን ተሸከመለትና በምትኩ ተቀጣለት (ዮሐ. 1፥29፤ 1ጴጥ. 2፥24)። ለኃጢአቱም ተገቢ መሥዋዕት ሆኖ በመሠዋቱ ኃጢአትን ተከትሎ የመጣውን ዕዳ ሞቱን በሞቱ ከፈለለት፤ በሞት ላይ ሥልጣን ካለው ከዲያብሎስ አገዛዝም ነጻ አወጣው፤ ዕብ. 2፥14-17።

የዳነውን ሰው ከእንግዲህ ሕገ ኦሪት ይገዛዋልን?

በሕገ ኦሪት ኃጢአተኛ ነህ ተብሎ የተከሰሰውን የሰው ዘር ሁሉ ይታደግ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ፤ የሰውን ኃጢአት ተሸክሞም በሰው ቦታ በመተካት ተቀጣ፤ ዕዳ-ሞቱንም ለሰው ከፈለለት። እንግዲያውስ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት ከኃጢአትና ከሞት ነጻ የወጣ ምእመን በቀሪ የሕይወት ዘመኑ ወደ ኋላ ተመልሶ በሕገ ኦሪት አገዛዝ ሥር ይኖራልን? ቢባል፥ መልሱ፥ «እንዴት ተደርጎ!» የሚል ይሆናል። ሰው በላዩ ለታወጀበት ሕግ የመገዛት ግዴታ የሚኖርበት በሕይወተ ሥጋ ባለበት ጊዜ ብቻ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ይገልጻል። ሰው ሲሞት ቀደም ሲል በሕይወተ ሥጋው እንዲታዘዝለት ለታወጀበት ሕግ የመገዛት ግዴታው በሞት ተቋርጧል ይለናል። «ኢተአምኑኑ አኀዊነ ሕገ፤ ንነግረክሙ ትሰብው፤ እስመ ሕገ ኦሪት ይቀንዮ ለሰብእ እምጊዜ ሕያው ውእቱ።»

ወንድሞቼ ሆይ ሕግን አታውቁምን? ሕግ ሰውን የሚገዛው በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ ነው ይላል። ከዚያም ሐሳቡን በግጥበብ ወደ ጋብቻ ሕግ ይመለስና፥ ባልና ሚስት የተጣመሩበት የጋብቻ ሕግ በተጋቢዎቹ ላይ

ሥልጣን የሚኖረው ሁለቱም በሕይወት እስካሉ ድረስ እንደሆነ ሐዋርያው ይናገራል፤ ከሁለት አንዱ ከሞተ ግን የጋብቻው ሕግ በግንኙነታቸው ወገን ላይ ሥልጣን ስለማይኖረው በሕይወት የቀረው ወገን በሌላ የጋብቻ ሕግ ከሌላ ጋር የመጣመር መብት አለው ይለናል። እንደዚሁም ሁሉ በሕገ ኦሪት አገዛዝ ሥር የነበረው ሰው በሕጉ ከላሸነት የተፈረደበትን ሞት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሞተለት፥ በእርሱ ቦታ ተለውጦ መሞቱን ለሚያምን ሰው የሚኖረው ኑሮ ከሞት በኋላ እንዳለ የሚቆጠር ኑሮ ነው። ስለሆነም ከሞት በኋላ ባለ በዚህ ዓይነት ሕይወት ላይ ሕገ ኦሪት ሥልጣን የለውም ሲል ሐዋርያው ጨምሮ ያስረዳናል፤ ሮሜ 7፥1-4።

ሕገ ኦሪት የማይገዛው ምእመን በምን ይመራል?

ምእመኑ ሕግን ባለመጠበቅ የተፈረደበትን ሞት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በመሞቱ ከሕገ ኦሪት ጋር የነበረው ቍርኝትና ትስስር ተበጥሷል። ከሞት በኋላ ያለ ሕይወት ማለትም ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገረ አዲስ ሕይወት ማለት ነው (ዮሐ. 5፥24-25)። ከሞት በኋላ ባለ በዚህ አዲስ ሕይወት ላይ ሕገ ኦሪት የመግዛት ሥልጣን ከሌለው፥ ምእመኑ በማን ይመራል? ቢባል አዲሱ መሪ ሞቱን የሞተለትና በሞቱ ሕያው ያደረገው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ያረጋግጣል። ስለሆነም እንደ ቀድሞ ባል ከሚቆጠረው ከሕገ ኦሪት ቍጥጥር ውጪ የሆነው ምእመን ሞትን ምክንያት ያደረገ ፍቺን በሚመስል መለያየት ከሕገ ኦሪት ጋር ተለያይቷል፤ ከሌላ ባል ጋር መጋባትን በሚመስል መጣመር ከክርስቶስ ጋር ተቈራኝቷል። በዚህ ሁኔታ ምእመኑ ከክርስቶስ ጋር የተጣመረበትንና ለወደፊቱ የሚመራበትን ሥርዓት «ሕገ መንፈስ፥ ዘአኮ ብሉይ መጽሐፍ። በአሮጌው ፊደል የተጻፈ ያይደለ የመንፈስ ቅዱስ ሕግ» ብሎታል፤ ሮሜ 7፥5-6።

ለሕገ ኦሪት በክርስቶስ ሥጋ የተገደለውና ትንሣኤ መንፈስን አግኝቶ ሕያው የሆነው ከክርስቶስም ጋር የመጣመር ሌላ ቃል ኪዳን የተዋዋለው ምእመን የሚመራበትን ሥርዓት፥ ሐዋርያው በሌላ ስፍራ «ሕገ መንፈስ ዘሕይወት - ሕይወት ሰጪ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሕግ» ብሎታል (ሮሜ 8፥2)። «የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ»ም ብሎታል (8፥4፤ 5-9)።

በሐዋርያው የተገለጸው ይህ አባባል፥ በትንቢተ ሕዝቅኤል 36፥27። «መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ በትእዛዜም አስሔዳችኋለሁ፤ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ፥ ታደርጉትማላችሁ» ተብሎ በትንቢት የተሰጠው ተስፋ መፈጸሙን የሚያበሥር ነው።

«ነገርን ነገር ያነሣዋል» እንዲሉ በትንቢተ ሕዝቅኤል ከተጠቀሰው ተስፋ፥ የመጀመሪያው ክፍል መንፈስ ቅዱስ ጥሩ ውሃን መርጨትንና ማንጻትን በመሰለው አገልግሎቱ ከርኩሰት የሚያነጻና የሚያጠራ ሲሆን፤ በቀጣይ አገልግሎቱ ለምእመኑ ዘላቂ ሕይወት አዲስ ልብንና አዲስ መንፈስን በመስጠት «አዲስ ፍጥረት» ለመሆን ያበቃዋል። በሦስተኛ ደረጃም በአዲሱ መንፈስና ልብ ውስጥ በማደር ምእመኑን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችለውን ኃይል እንደሚያመነጭለት ያመለክታል (36፥25-27)።

መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሚሠርጽ፥ (ዮሐ. 15፥26) ከወልድ የሚነሣ፥ (ዮሐ. 16፥14-15) የአብና የወልድ መንፈስ፥ (ሐ.ሥ. 16፥6-10) ስለሆነ፥ የልባችንን ዙፋን በመያዝ ሙሉ ባለሥልጣን ሆኖ አመራር ሰጪ ሲሆን፥ በእርሱ መሪነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናስተውል፥ የምናደርግም እንሆናለን። ስለዚህም በመንፈስ ቅዱስ የሚታወቀው የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገር እንኳ ለእኛ እንደሚገለጥ ጳውሎስ ይናገራል። ከዚህም የተነሣ በፍጥረታዊ ሰው የማይታወቀው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ልብ በእኛ ውስጥ አለንና እንናርበታለን፥ እንመራበታለንም፤ 1ቆሮ. 2፥6-16። ይህም ሁኔታ ጳውሎስ፥ «በፊደል ያልተጻፈ የመንፈስ ቅዱስ ሕግ» ያለው ነው፤ ሮሜ 7፥6፤ 8፥10፤ 2ቆሮ. 3፥4-6።

ይህም ሕግ ፦

1) በእንስሳ ደም ጸንቶ የነበረውን ቃል ኪዳን ያስረጀና የተካ፥ በክርስቶስም ደም የጸና ዐዲስ ቃል ኪዳን ነው። ዘጸ. 24፥3-8፤ ሉቃ. 22፥20፤

2) በድንጋይ ሰሌዳ (ጽሌ፥ ጽላት) ላይ እንደ ተጻፈው ሕገ ኦሪት ያይደለ፥ በሰው ውስጠኛ የመንፈሱ ክፍል ማለት የነፍሱ፥ የአእምሮው፥ የፈቃዱና የስሜቱ አጠቃላይ መጠሪያ በሆነው በልቡናውና በልቡ ላይ ራሱ እግዚአብሔር የጻፈው ነው። ኤር. 31፥31-33፤ ዕብ. 8፥6-13፤ 10፥15-18። እንግዲህ የሕይወት መንፈስ ሕግ፥ ወይም ሕይወት ሰጪ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሕግ የተባለው ይህ ነው።

በሕገ ኦሪትና በሕገ መንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድር ነው? ቢባል ሕገ ኦሪት በጉድጓድ ውስጥ የወደቀውን ሰው «እንዲህ ሥራ፤ እንዲህም አታድርግ» በማለት ከማዘዝ በቀር ትእዛዙ በሰው ይፈጸም ዘንድ ምንም ዓይነት ርዳታ ለሰው አይሰጥም። እንዲያውም ትእዛዙ ባለመፈጸሙ ሰውን በመክሰስ ከፍርድ በታች ያውላል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰውን ከወደቀበት ጉድጓድ ካወጣ፥ አክሞና ጤናውን መልሶ ከሰጠ በኋላ መንፈሱን በሰው ልብ ውስጥ በማኖር ምእመኑን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይመራዋል፤ መመሪያውንም ይፈጽም ዘንድ ለምእመኑ ኃይል ይሰጠዋል (እንደገና ትንቢተ ሕዝቅኤል 36፥27ን ያንብቡ)። መንፈስ ቅዱስ የምእመኑን ድካም እንኳ ይጋራዋል (ሮሜ 8፥26-27)፤ በጎዘኑ ያጽናናዋል (ዮሐ. 14፥15-17፤ 15፥26፤ 16፥7)። ርኅሩኅና ደግ አስተማሪ ስለሆነ ለምእመኑ ያላስተዋለውን ያስተምረዋል (ዮሐ. 14፥26)።



አፍራሽነትም ለሌሎች ዜጎች እንደ ተለዋጭ ሕግ ሆኖ አይጠቀስም። እንደ ባለ አእምሮ የሚያስቡ ሁሉ ይህን እውነታ ሊቀበሉ ይገባል። «የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ» እንደተባለው መናፍቃን የሆኑት የዘርዐ ያዕቆብ የመንፈስ ልጆች፥ ዛሬም ሕግን ሲያፈርሱ የቀደሙ ሰዎችን የሕግ አፍራሽነት አርአያ እንደተገቢ አብነት ይጠቅሱታል።

አባ እስጢፋኖስ ግን፥ አብርሃም፥ ያዕቆብና ሌሎችም ለሰዎች ቢሰግዱ ለሰው መስገድ ተፈቅዷል ማለት አይቻልም፤ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚሽረው፥ የሰዎች ድርጊት ሳይሆን ያው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

የአባቶች አለቃ አብርሃም ስለዋሸ መዋሸት ተፈቅዷል ማለት አይቻልም፤ (ዘፍ. 12፥10-19)። ነቢይና ንጉሥ የነበረው ዳዊት፥ ስለ ተመኘ፥ ስለ ሰረቀ፥ ስለ አመነዘረና፥ ስለ ገደለ፤ አትመኝ፥ አትስረቅ፥ አታመንዝር፥ አትግደል የተባሉት የሕግ አናቅጽ ተሽረው ኃጢአት ተፈቅዷል ሊባል አይቻልም። (2ሳሙ. 11 እና 12)። «ይዲድያ፥ በእግዚአብሔር የተወደደ)። የተባለው ሰሎሞን (2ሳሙ. 12፥24፤25) «ለሞዓብ ርኵሰት ለካሞሽ፥ ለአሞንም ልጆች ርኵሰት ለሞሎክ በኢየሩሳሌም ፊት ለፊት ባለው ተራራ ላይ መስገጃ ሠራ።» ተብሏል። ይህ ርኵሰት በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ በሆነው በሰሎሞን ስለ ተሠራ «ቅድስና» አልተባለም። 1ነገ. 11፥7

5. ዘርዐ ያዕቆብ እውነትን ማሸነፍ አልቻለም

አባ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አባ እስጢፋኖስን አስደብድቦ ሲያስገድል፥ 107 ደቀ መዛሙርቱን ሲያስጨፈጭፍ፥ ሌሎቹንም ባወጀባቸው ጦርነት ከትግራይና ከሌሎቹም የግዛቱ ክፍሎች እያስያዘ ሲያስገድል፥ የክርስቶስን ወንጌል ለሁልጊዜ ከኢትዮጵያ ምድር ሊያጠፋ የሚችል መስሎት ይሆናል፤ በውጤቱም በክርስቶስ ስም ፈንታ የመናፍስት ስም ብቻ ይጠራል ብሎ ዐስቦ ይሆናል። ነገር ግን እስጢፋኖስ የወንጌል አገልግሎቱን በመሠረተባቸው በትግራይ አውራጃዎችና ደቀ መዛሙርቱ ቃለ ወንጌልን ባሠራጩባቸው ሌሎች ግዛቶች ገና ብዙ ደቀ መዛሙርት መኖራቸውን ሲሰማ ተበሳጨ፤ «የእስጢፋኖስና የደቀ መዛሙርቱ አንገት ለምን አንድ አልሆነልኝም?» ሳይል አልቀረም። ይህን ሁኔታም ዜና ገድሉ እንዲህ በማለት ይተርከዋል። «ወእምዝ ፈነወ ንጉሥ ሐራሁ ውስተ በሐውርተ ትግራይ ወውስተ ካልአትሂ፥ ወአዘዞሙ ከመ ያስተጋብኡ ኵሉ ደቂቁ ለቅዱስ እምኀበ ኵሉ ዘረከቡ። ወኮኑ ያመጽኡ ሎቱ ሐራሁ በከመ አዘዞሙ። ወሰርጎ ንጉሥ በኲንኖቶሙ ለለ ዘመን

ዘመን። ከዚህ በኋላም ንጉሥ ሠራዊቱን ወደ ትግራይ አውራጃዎችና ወደ ሌሎቹም ላከና የእስጢፋኖስን ደቀ መዛሙርት በሙሉ ይሰበስቡ ዘንድ አዘዛቸው። ሠራዊቱም እንደ ታዘዙት እየሰበሰቡ ያመጡለት ነበር። ንጉሡም ከዘመን ዘመን (በየዘመኑ) በእነርሱ ላይ መፍረድ ደከመው፤ ሰለቸው።

6. ደብረ ጽዮን አለች፤ የለችም።

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የእስጢፋኖስን መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰማበት የመንፈስ ጆሮው አልተከፈተም፤ ትምህርቱን የሚረዳው በሥጋዊ ትርጉሙ ነበር። አንድ ጊዜ ምድራዊት ጽዮንን (ኢየሩሳሌምን የምትተካ ታሪኳን የምትሻማ) በኢትዮጵያ ምድራዊት ጽዮንን ለማቋቋም ደፋ ቀና ይል በነበረበት ጊዜ፥ እስጢፋኖስ «ወአንትሙሰ በጻሕክሙ ኀበ ጽዮን ሀገረ እግዚአብሔር ሕያው፥ ኢየሩሳሌም እንተ በሰማያት። እናንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ ደርሳችኋል፤ እርሷም የሕያው እግዚአብሔር ከተማ የሆነችው ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ናት።» ተብለን ሳለ (ዕብ. 12፥22) በመንፈስ ከደረስንባት ሰማያዊት ከተማ በመንፈስ ወደ ምድር ተመልሰን **ለታሪክ ሽሚያ የምትቋቋም ምድራዊት ጽዮን ለምን ታስፈልገናለች? አታስፈልገንም።** ማለቱ በንጉሡ ዘንድ ቅሰም ቀበት ሆነ። እርሱም ሊቃነ ደብተራ የተባሉትን ግብረ በላ ካህናት ወደ እስረኛው ልኮ ጠየቀው። «ወለአከ ንጉሥ ኀበ ቅዱስ ሊቃነ ደብተራ እንዘ ይብል ሰማእኩአ፤ ነገሩኒ ከመ አንተ ትብል አልቦ ደብረ ጽዮንአ። ... ወይቤሎሙ ቅዱስ ለላእካን፥ በልዎኬ አንሰ ኢይብል አልቦ ደብረ ጽዮንአ፤ እስመ እለ አንጽሑ አልባቢሆሙ ወጸሩ አርዑተ መንፈሱ ለክርስቶስ ይረክብዎአ። እኔ ደብረ ጽዮንኳለም አላልኩምኮ፥ ንጹሕ ልብ ያላቸውና የክርስቶስን የወንጌሉን ቀንበር የተሸከሙት ደብረ ጽዮንን ያገኙታል፥ ይገቡበታልና» ሲል መለሰ።

ዘርዐ ያዕቆብ የወንጌልን እውነት ደብዛ ለማጥፋት የእስጢፋኖስንና የደቀ መዛሙርቱን የሚታይ አካል በመቁራረጥ ብዙ ደከመ፤ በመጨረሻም ሞተ። ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ግን ዛሬም በቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እየተሰበከ ነው።

«ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር፥ ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል፥ አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።» 1ጴጥ. 1፥24-25።

ከዓለመ መጻሕፍት




በጮራ ቁጥር 16 ስለ አዕማድ መጻሕፍት ጠቅላላ ይዘትና ጥቅም ጽፈናል፤ ከታሰቡት 48 አርእስት መካከል 18ቱ ስለመታተማቸው፥ አንዳንዶች ደግሞ ተሻሽለው ለሁለተኛ ጊዜ ስለ መቅረባቸው ገልጠናል። አሁንም «ከባቢሎን ምርኮ መልስ» የሚለው 19ኛው መጽሐፍ በመታተሙ ጮራ ደስታዋን ለአንባቢዎቿ መግለጥ ትፈልጋለች። መጽሐፉ ታትሞ እጃችን ውስጥ ከመግባቱ በፊት ረቂቁን ከአዘጋጁ ተቀብለን በተለይ ስለ ዘሩባቤልና ስለ ዕዝራ፥ አሁን ደግሞ ስለ ነህምያ አንዳንድ አሳብና አስተያየት ጨምረን በመጽሔታችን አቅርበናል። ሁሉም አዕማድ መጻሕፍት እጅግ ጠቃሚ መሆናቸውን አስቀድመን ገልጠናል። ይልቁንም ይህ መጽሐፍ ከጮራ ዓላማ ጋር የሚጣጣምና ጐን ለጐን የሚሄድ በመሆኑ በሦስት ምክንያቶች ከፍ ያለ ትኩረት ልንሰጠው እንፈልጋለን።


1. የመጽሐፈ ዕዝራንና የመጽሐፈ ነህምያን ታሪክ ያብራራል፤ ሕያውም ያደርገዋል። ለምሳሌ ተንትናይ ለፋርስ ንጉሥ ለጻፈው ደብዳቤ መልስ እስኪገኝ ድረስ ብዙ ጊዜ የዘገየበትን ምክንያት ሲገልጥ፥ የዘመኑን «ቢሮክራሲ» በማሳየት የዘሩባቤልን ጭንቀት ያብራራል። በነህምያ ዘመንም አይሁድ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሲያድሱ፥ አካላዊ ድካማቸው ምን ያህል እንደነበረ ይገልጣል። ከዚህም በላይ መጽሐፉ ከባቢሎን ምርኮ የመመለስን ታሪክ በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክና በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ያለውን ሰፍራ ጠቅለል ባለ መልኩ ያሳያል፤ እኛም በእግዚአብሔር ጸጋ በዚህ ሕዝብ መካከል በመቈጠራችን ወደዚህ ታሪክ ገብተናል።
2. መጽሐፉ የዘሩባቤልን፥ የዕዝራንና የነህምያን ጠባይ በመግለጥ እነዚህ ሦስት ሰዎች በተፈጥሮ ጠባያቸውና በቤተሰባዊ ሁኔታቸው ለእግዚአብሔር ሥራ በተጠሩባቸው መንገዶች እጅግ የተለያዩ እንደነበሩ እናስታውሳለን። ቢሆንም እግዚአብሔር በሦስቱ አገልጋዮች እንደየጠባያቸውና እንደየሁኔታው ለሕዝቡ አመራር ተጠቀመባቸው። እግዚአብሔር ዘሩባቤልን ለጥሪው እንዲወጣ በነቢያት አማካኝነት አደፋፈረው። ዕዝራ እያለቀሰ በጭንቅ ሕዝቡን ከኃጢአቱ እንዲመለስ አደረገ። ከሦስቱ እጅግ ታዋቂ የነበረው ነህምያ እንኳን ሥራውን ሲጨርስ ጥረቱ ከንቱ እንዳይሆን ፈራ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእነዚህ ሦስት የተለያዩ ሰዎች ከተጠቀመ፥ እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ሊጠቀም እንደሚችል መጽሐፉ ያሳየናል።
3. ሰው ቤት ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ እፎይ ብሎ ለረጅም ጊዜ ሊያርፍ የሚችል ይመስለዋል። በጥንቃቄ ካልጠበቀው ግን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቤቱን ማሳደስ ከባድ ሥራ ይሆንበታል። የእግዚአብሔርንም ቤት በየጊዜው ማደስ፥ ማሳደስ አስፈላጊ ነው። በማንኛይቱም ቤተ ክርስቲያን በየትውልዱ አዲስ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ካልኖረ ስሕተት ይገባል፤ አምልኮም ልማዳዊ ይሆናል፤ ወንጌልም ለአዲሱ ትውልድ በሚያስተውለው መንገድ አይሰበክም። ይህም ሁኔታ ለሁለት ወይም ለሦስት ትውልድ ጸንቶ ቢቆይ ደግሞ፥ ቤተ ክርስቲያኗን ወደ ጥንት መሠረቷ መልሶ ማቆም ከባድ ሥራ ይሆናል፤ እንዲያውም ቤተ ክርስቲያንን በመጀመሪያ ከመትከል የበለጠ ማደሱ ከባድ ትግል ሊጠይቅ ይችላል።

የዚያ ጊዜና የአሁኑ ዘመን ሁኔታ የተለያየ ቢሆንም፥ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሱን እንደገና መሥራትና ሥነ ሥርዓቱን ማቋቋም፥ የከተማይቱን ቅጥር መገንባትና ኅብረተሰቧን ማደራጀት ለእኛ ከፍ ያለ ምሳሌ ነው። በዚያ ዘመን የደከሙትን ሰዎች ፈለግ ብንከተል እግዚአብሔር በጥሪአችን እንድንወጣ፥ ሥራችንን በአግባቡ እንድንፈጽምና መከናወንን እንድናገኝ ያደርጋል።

ከአዕማድ መጻሕፍት

«ከባቢሎን ምርኮ መልስ» (72 ገጽ) ዋጋው ብር 3.50





ዋጋው ብር 2.50